# ላንዳፍታ

ኢትዮጵያዊ የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት በአማርኛ

በየሁለት ወር የሚታተም | ፬ኛ ዓመት ቁጥር ፩ | ሐምሌ ፲፱፻፹፯

LANDAFTA



በፍቅር፥በሰላም፥በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ፥
መቻቻል

# ስፖርት
# ለፍቅር! ለሰላም!
# ለአንድነት!

- ❖ ልብ ወለድ
  የኮለምበስ ጉዞ
- ❖ ኑሮ በአሜሪካ
  "እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ!"
- ❖ አዳምና ሔዋን
  ሰጣዬ
  ፖለቲካና ባላገር
- ❖ በቅርብ ከኢትዮጵያ የደረሱን ዜናዎች

An Ethiopian Cultural Bi-monthly Amharic Magazine
(Amharic is the official language of Ethiopia)
July 1995 Vol. 4. No. 1

$2.75

# የኢትዮጵያ መንደር






## ETHIO VILLAGE
### CAFE & RESTAURANT

**3462 N. Clark St.**
**Chicago, IL 60657**
**(312) 929-8300**

CATERING AND CARRY OUT AVAILABLE



ቀይ ወጥና ዝግኑ ዶሮ ወጥ አልጫው፤
አትክልት ከሥጋ ጋር ምንቸት አብሽ ክትፎው።
የአበሻ ዳቦና ቆንጆ የማር ጠጅ፤
ሽታው ግቡ ይላል ሳይገቡ ከደጅ።
ቆርጠው በሩን ከፍተው ገባ ሲሉ ገና፤
አገር ቤት የገቡ ያስመስላልና።
የሰኞ ዕለት ዱለት የበግ ወጥ ፍትፍቱ፤
ረቡና ዓርብ ዕለት የጾም በያይነቱ።
በስምንት ዓመት ልምድ የሙያ ክምችት፤
ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነ ዝግጅት፤
ኢትዮ ቪሌጅ ይምጡ ሲያሻዎት መደሰት።

# ማ ውጫ CONTENTS


2 ከአዘጋጁ

3 ሰላምታ ከአገር ቤት (ወርቃየሁ)

8 ሰላምታ ከባህር ማዶ (ይግለጡ)

11 እንዲህ ሆነ (ዜና ከአገር ቤት)

13 አንድ ጥያቄ አለኝ

23 የግጥም ጉባኤ
“ፖስተኛ ቡታን ኣታምጣ” መሪጌታ ልሳኑ)

15 ልብ ወለድ
“የኮለምበስ ጉዞ” ክፍል 3 (አብዩ)

24 ኑሮ በአሜሪካ
“እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ!” (አትናትዮስ)

28 ልዩ አምድ
እስፖርት
የዓለም ዋንጫ (መኮንን ጉርሙ)

35 አዳምና ሔዋን
ዕጣዬ (አብርኸት)

የጳውሎስ ኞኞ “አንድ ጥያቄ አለኝ”


38 ፖለቲካና ባላገር (ሂርጳሳ አንዱዓለም)

46 ቢስቁም ባይስቁም


47 ሰንጠረዥና ጨዋታ




ምርጫ በአገር ቤት



## እግር ኳስ ውድድር



| ሽፋን | “ስፖርት ለሰላም፣ ስፖርት ለፍቅር፣ ስፖርት ለአንድነት” |
|---|---|


“ላንዳፍታ” የግል መጽሄት ናት። የሚወጡ ጽሁፎች በሙሉ የአዘጋጆቹን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሁፎቹን በሬዲዮ፣ በቴሌቪ ዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የጸሃፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። በተለይ የግጠመኝና የፈጠራ ድርሰት ጽሁፎች ህጋዊ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን እንገልጻለን።

© COPYRIGHT LANDAFTA 1995

ላንዳፍታ
ሐምሌ ፲፱፻፹፯
፬ኛ ዓመት ቁጥር ፩
LANDAFTA
July 1995 V. IV- No. 1

አዘጋጅና አሳታሚ
መኮንን ገሠሠ
**Publisher/Editor**
*Mekonnen Gessesse*

**Editorial Advisors**
*Dr. Abera Molla*
*Seifu Mekuria*
*Solomon Melesse*
*Dawit Deres*
*Zelleke Nigatu*
*Girma Zegeye*

**Distribution**
Atlanta, GA
California Mart
Sweet Auburn Grocery
H & B Tailoring
Chicago, IL
Ethio-Village Rest.
Dayton, OH
Rainbow Cafe
Dallas, TX
Maru Grocery
ET. Beauty Supply
L.A., CA
Merkato
Damera
Oak Land, CA
Albo-African Shop
San Jose, CA
St. Claire news Stand
Seatle, WA
Addis Cafe
St. Louis, MO
A & Z Liquor
St. Paul, MN
Merkato
Tampa, FL
Ibex Ethiopian restaurant
Washington D.C.
Addisu Gebeya
Family Food Market
Merkato Market
Nini Market (Alex.)
Tana (Silver Spring)
Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu

Landafta
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359
Phone/Fax
(404)728-9122
E-MAIL
mgessesse@aol.com

# ከአዘጋጁ

**እንኳን ለ12ኛው የሰሜን አሜሪካ ኢትዮጵያውያን እግር ኳስ ውድድር በሰላም አደረሳችሁ በማለት የላንዳፍታ መጽሄት ዝግጅት ክፍል መልካም ምኞቱን ይገልጻል።**

በአራት ቡድኖች የተጀመረው ይህ ዝግጅት በ12 ዓመት ጊዜ ውስጥ 26 ቡድኖችን አሰልፎ ማጫወቱ ብቻ ሳይሆን ለብዙ ኢትዮጵያውያን መገናኛ፤ መተዋወቂያና መዝናኛ እየሆነ መምጣቱን ተመልክተናል። ስለዚህም ሁለገብ የኢትዮጵያውያን በዓል ሆኗል ማለት ነው ። አገሩና ወገኑ ለሚናፍቀው ህዝብ ይህን የመሰለ በዓል በናፍቆት የሚጠብቀው መሆኑ የታወቀ ነው። ከጥንስሱ ጀምሮ በተለያዩ ዓመታት ይህን ዝግጅት የሚያቀናብረውን የስፖርቱን ፌዴሬሽን ሳናመሰግነው አናልፍም። ውጣ ውርድ በበዛበት በዚህ አታካች አገር ጊዜንና ገንዘብን አስተባብሮ ይህን ዓይነት በዓል ማዘጋጀቱ ቀላል ስላልሆነ የፌዴሬሽኑ ሹማምንት ሊደነቁ ይገባቸዋል።

ዝግጅቱ በስፋት የሚካሄድ በመሆኑ ስህተቶች ሊፈጸሙ ይችላሉ። በዝግጅት በኩል የሚታዩ አንዳንድ ስህተቶች የሚታረሙብትን መንገድ መፈለጉ ደግሞ ለዚህ ወገናችንን ለማግኘት ለሚያስችለን በዓል መጎልበት አስተዋጽዖ ይኖረዋልና በየጊዜው የሚጠቆሙት ድክመቶች እርምት ቢደረግባቸው የበለጠ ትልቅ በዓል ይሆናል እንላለን። ስህተቶች ሲደጋገሙ ቅር ከማሰኘት አልፈው ተሳትፎን ይቀንሳሉ። በአለፈው ዓመት የታየው ትልቅ ስህተት እንደሚታረም ተስፋ አለን። ከህዝቡ የሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ካላገኙ ለህሜት በር ይከፍታሉና እስቲ በዚህ በኩልም አንድ ዘዴ ፍጠሩ። በተመልካቾችም በኩል ቢሆን ስህተቶች እንዲታረሙ መጠቆምና ስህተቶቹ እንዲታረሙ ተሳትፎ በማድረግ መተባበር ያስፈልጋል። ስህተቶችን ብቻ በማጉላት ጉልህ የሆኑ በጎ ተግባራትን መሸፈን የሚገባ አይመስለንም። "ስፖርት ለሰላም፣ ስፖርት ለፍቅር፣ ስፖርት ለአንድነት" የሚለውን መርህ በተግባር ለመተርጎም ሁላችንም ተባብረን ይህችን አንድ ላይ የምታሰባስበንን ጤነኛ ዝግጅት እናጎልብታት እንላለን።

የዝግጅት ክፍላችን ይህንኑ በማስመልከት ለስፖርት በዚህ እትም ልዩ አምድ አዘጋጅቷል። ለወደፊቱም በየቦታው ያሉትን እስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ለመዘገብ እንድንችልና ቋሚ አምድ እንድንከፍት ዜናዎችን እንድትልኩልን እንለምናለን።

ላንዳፍታ መጽሄት ይኸው አራት ዓመት ሞላት። ሚቀጥለው የእንቁጣጣሽ እትም ይህንኑ በተመለከተ ሰፊ ዝግጅት ይኖራታልና እባካችሁ አስታያየታችሁን ላኩልን። ደግም ከሰራን ጎሽ! አጥፍተንም ከሆነ ታረሙ በሉን።

## መልዕክት

ይህችን እትም ላነበባችሁ ወገኖቻችን አንዲት መልዕክት አለን። መጽሄታችንን ለማሳደግ፣ ጥራቱን ለመጠበቅ ደምበኛ ይሁንዋት እንላለን። ይህን እትም ያነበቡት ተውሰው ከሆነ የሚቀጥለውን እንደሚገዙን ወይም ደምበኛ ለመሆን ገጽ 48 ላይ ያለውን ቅጽ ሞልተው ከነክፍያው እንደሚልኩልን ተስፋ እናደርጋለን። መጽሄቷ የበለጠ ልታድግ የምትችለው ብዙ ደምበኞች ኖርዋት ለዝግጅቷ የሚወጣውን ወጪ ቢይንስ ቢይንስ መሸፈን ስትችል ነው። ይህን ስንል ያለብንን ችግር ስለሚረዱልን እርሶም፣ ጓደኞችዎንም በማሳሰብ የደምበኝነት ቅጹን ሞልተው ይላኩልን በማለት በወገን በመኩራት ይህን መልዕክት እናስተላልፋለን።

የላንዳፍታ መጽሄት ዝግጅት ክፍል
LANDAFTA
P.O.Box 49301, Atlanta, GA 30359
(404) 728-9122
E-MAIL- mgessesse@aol.com

*Landafta is an independent magazine published bi-monthly in Amharic.*
*Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት

## እንደምን አላችሁ?

እንደምን ከርማችኋል? እንደምን አላችሁ? ቸርነቱ የማያልቀው መድኃኔያለም ክብሩ ይስፋ እኛ ደህና ነን። ረዥሙን የበጋ ወራት ጨርሰን ሰኔ ደርሰናል። ሰኔ ግም ሲል በመስከረም ግድም ከትምህርት ላይ የተጣደ ኩታራ ተማሪ ውጤቱን ይዞ ለሁለት ወራት ዕረፍት ወደቤቱ ይበተናል። ነጋዴው ወንዝ ሞልቶ አላሻግር ከማለቱ በፊት፣ ደለልና ጭቃው እግር ከመያዙ፣ የሐምሌና የነሐሴ ዶፍ ከመውረዱ አስቀድሞ ሸቀጣ ሸቀጥ ገዝቶ ያከማቻል። ገበሬው የሰቀለውን ሞፈርና ቀንበር አውርዶ በሬዎቹን ጠምዶ ሆ! በለው እያለ እርሻ ይጀምራል። በአዝመራ ተጠምዶ ሲያርስ፣ ሲጎለጉል፣ ጋይ ሲያቃጥል፣ ሲዘራ ሲያርም ሐምሌና ነሐሴ ሸው ይሉበታል። አንድ ሰኔ የገደለውን ገበሬ ሁለት ሰኔ አይመልሰውም እንዳይሆንበት ከእርፍና ከማረሻ ከአፈር ጋር ትንቅንቅ አለበት።

ሚያዝያና ግንቦት እንደራሴ ምርጫ ላይ ከረምን። እኔ በርጬማ ነኝ። ተቀመጡብኝ። እኔ ሻማ ነኝ፣ እየነደድኩ አበራላችኋለሁ። ምረጡኝ! እኔ በግ ነኝ። እኔ ብዕር ነኝ፤ ቧንቧ ነኝ። እኔ ንብ ነኝ ማር የምሰራላችሁ! እኔ ጀበና ነኝ ቡና የምታፈሉብኝ። ምረጡኝ! አስመርጡኝ የሚሉ ምልምል ባለጊዜዎች ሲያደነቁሩን ከረሙ። ስለሚያስገቡልን ኮረንቲ፣ ስለሚያስተክሉልን ወፍጮ ቤት፣ ስለሚያሰሩልን ክሊኒክና ሆስፒታል፣ ስለሚከፍቱልን ፋብሪካና ት/ቤት ብዙ ብዙ ነገሩን። እኛ ደግሞ ይህቺ ዓይነቷ የምርጫ ሆያ ሆዬ! ቤተመንግሥት ለመሰንበቻ የምትሰራ ትንሽዬ ድራማ መሆኗን ጠረጠርንና ሲሰርቀኝ የያዝኩትን ሲጨምርልኝ ባየውም አላምነው ሆኖብን ተቸግረን ስናስቸግር ሰነበትን። ሬዲዮው፣ ቴሌቪዥኑና ጋዜጣው ቅስቀሳ ብቻም ሳይሆን የቅጥቀጣ ያህል "በአገሪቷ ታሪክ የመጀመሪያው ዲሞክራሲያዊ ምርጫ" እያለ ሲሰብከን ከረመ። ኢሕአዴግ ከተቃዋሚዎች ጋር ተወዳድሮ ከፉኛ ተፎካክሮ አገር ወዶት፣ አድባር ተቀብሎት በከፍተኛ ድምፅ ማሸነፉ ተነገረን። ብዙ የፈረንጅ ታዛቢ መሰከረ። ለተቀረው አፍሪካ ምሳሌ የሚሆን ተባለ። አቡን ቄስ ናቸው ወይ ቢሉት ተርፎቸው ይናኛሉ አለ አሉ ሰውዬው። በንጉሥ ኃይለሥላሴ ዘመን የእንደራሴ ምርጫ ምልክቱ ትራክተር፣ አውራ ዶሮ፣ ሻማ እንዲህ የመሳሰለው ነበር። "ከስመ–ጥሩውና ከኮራው የዚህ አገር ባላባት ተወልደው በጨዋ ልጆች ደንብ በመልካም ሥነ–ሥርዓት አድገው ዕድሜያቸው ለአገልግሎት በደረሰ ጊዜ ከሹመት ወደ ሹመት ከማዕረግ ወደ ማዕረግ እየተዘዋወሩ አገራቸውንና ንጉሠ ነገሥታቸውን በቅንነት ያገለገሉ" የሚባልላቸው እንደራሴዎች ምረጡን አስመርጡን ይሉን ነበር።

ትራክተሩም ሳያርስ፣ ዶሮውም ጮሆ ሳያነቃን፣ ሻማውም ሳያበራልን፣ ደርግ መጣ። ደርግ ደግሞ በተራው አንበሣ፣ ጎሽ፣ ዝሆን፣ የአራዊት ምስል ሰራና ምረጡ አስመርጡ አለ። ዝሆን ዝሆኑ ተመረጠ፤ የአገር እንደራሴ የሸንጎ አማካሪ ሆነና ጉድ ፈላ። አያ ዝሆን ትልቅ ጆሮ አለው ግን አይሰማም። አካሉ ግዙፍ መራመድ አይችል። ቀና ብሎ አያይ፣ ሲሄድ ጉትት ጉትት፣ ሲሮጥ አያምርበት! ሲበላ እማይጠግብ፤ ሲጠጣ ለአዳር ነው ምንጭ ያደርቃል። ሲራገጥ ድባቅ የሚያስገባ፣ ከያዘ መላቀቂያ የሌለው፣ እቆመበት የሚያንቀላፋ፣ ከወደቀ የማይነሳው ዝሆን በከፍተኛ ድምፅ ተመረጥኩ አለ። አገር ሲራብ ሕዝብ ሲጮህ አይሰማም። ዓለም ሲለወጥ ቀና ብሎ አላየም። እቆመበት አንቀላፋ። እንዳንቀላፋም ወደቀ። አልተነሣም በዚያው ቀረ። ኢሕአዴግ ደግሞ መጣ። እርሱም በተራው ንብ፣ ጀበና፣ ቁልፍ፣ አገልግል፣ ሙቀጫ፣ በርጬማ፣ ቁሳቁስ ምንትስ አደረገና ምረጡ አስመርጡ አለ። ለአማራው ብአሕዴን፣ ለኦሮሞው ኦህዴድ፣ ለደቡብ ብህዴግ፣ ለቤንሻጉል ለአፋሩ ለአደሬው ለጉራጌው ለሁሉም በየፈርጁ አበጃጅቶ ሞከሩ ተፎካከሩ ՝ታንጎ ለመደነስ ሁለት ሰው ያስፈልገዋል′ ብለዋል ፈረንጆቹ ይላቸዋል። ጠጣ ምን ትወጂያለሽ ቢሏት ከዛፍ ላይ ትግል አለች አሉ። ይሄ ወደ ፓርላማ የተመመው ንብ ደግሞ ወለላ የሚሰራ ይሁን ቀጋ ጊዜ ይለየዋል። ካቻምና፣ አምና ያለፉትን አራት ዓመት ተያይተናል። ያለችዋንም ሙጣጭ ማር በልቶ ቀፎውን ደፍቶት በትናም እንዳይሄድ እንሰጋለን። አመንዝራ ካሏት ብትቆርብስ ማን አምኗት ነው ነገሩ!

. . . እንግዲህ ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት አፍጣጭ አግጣጭ ሳይኖርበት ኢሕአዴግ ከቤተመንግሥት ገብቶ ይደላደላል። በእብሪትና በሥልጣን የሚያሳውረው የቤተመንግሥት በሽታ እንዴት ያደርገዋል? ልናየው ነው። መሪዎቻችን ሥልጣን ሲደላደልላቸው ቤተመንግሥቱን ሲለምዱ ብዙም ሳይቆዩ እብሪትና ሥልጣን ለምን እንደሚያሳውራቸው አይገባኝም። ሌላውን ሕዝብ ከቁጫጭ አሳንሰው ለማየት፣ በዚያው ልክ ደግሞ ራሳቸውን ዘላለማዊና መለኮታዊ ለማድረግ ድፍረቱን ከዬት እንደሚያገኙት ይገርመኛል። በሽታ ነው። የእብሪት በሽታ! የሥልጣን በሽታ!!

. . . ንጉሥ ኃይለሥላሴ የሰው ልጅ ሆነው ሳለ ግን መለኮታዊ ባሕሪያቸው ጎልቶ ሲነገርላቸው፣ ቅኔ መወደስ ሲደረደርላቸው፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተፃፉት ትንቢቶች ሳይቀሩ ለእርሳቸው እንደተነገሩ ተደርጎ ሲቀርብላቸው "ተው ይቅርብኝ። አይገባኝም" አላሉም። ይልቅዬ እየጣማቸው፣ ልባቸውን ደስ እያሰኛቸው ከቤተመንግሥት

ወደ አደባባይ፣ ከአደባባይም ወደ መላው የአገሪቱ ምድር ተዳርሶ እንዲነገርላቸው አደረጉ። እሳቸውም አልጠሉትም። ተቀበሉት። ነገር ግን ሰው እንጂ መለኮታዊ ፍጡር እንዳልሆኑ እርሳቸውም ልቦናቸውም ያውቀዋል። የሚያመፃድቋቸውም ያውቁታል።

. . . አንድ ዘመን ለሐምሌ 16 ቀን የንጉሡ የልደት በዓል መታሰቢያ በተወለዱበት ሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት ኤጀርሣ ጎሮ የኪዳነምህረት ቤተክርስቲያን ይመረቅ ነበር። ንጉሡ ከመሳፍንቶቻቸውና ከመኳንንቶቻቸው ጋር በአጀብ ከሥፍራው ሲደርሱ የሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት ጳጳስ ቀሳውስትና ዲያቆናት በአንድነት ወደ ንጉሡ ፊት ቀርበው :-

"እምነጽዮን ይብል ሰብዕ ወብእሲ ተወልደ በውስቴታ ወውዕቱ ልዑል ሣራራ ማለትም ትርጓሜው ሰው ጽዮንን እናታችን ይላታል። በእርስዋም ታላቅ ሰው ተወልዶአልና። የሠራዊትም ልዑል እግዚአብሔር ነው። ይህም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በዚህች ቅድስት ስፍራ እንደተወለዱ የሚያሳስብ ሆኖ አግኝተነዋል። ከኤጀርሳ ጎሮ ያንፀባረቀው ፀዳለብርሃን መላውን ኢትዮጵያ ዘኩለንታሃ ብርሃን ስለአሰኛት ኤጀርሣ ጎሮ ቤቴልሄም ተብላ እንድትሰየም፣ የኖኅተ ምሥራቅ ኪዳነምህረት የታነፀባት ይህቺ ስፍራ ቅድስት እንድትባል ግርማዊነትዎ ዙፋን ስር ወድቀን በታላቅ ትህትና እንለምናለን" አሉ። ጭብጨባው ዕልልታው ቀለጠ። ንጉሡ ደስ አላቸው። ራሳቸውን ነቅነቅ አድርገው ፈገግ አሉና "ፈቅደናል" አሉ። ዕልልታውና ጭብጨባው ዳር እስከዳር አስተጋባ።

በጃንሆይ ዘመነ-መንግሥት መስከረም 10 ቀን የአፄ መስቀል የተቀፀል ጽጌ በዓል በቤተመንግስት ንጉሡ በተገኙበት ይከበራል። በሥነሥርዓቱ ላይ ሚኒስትሮች፣ መሳፍንት፣ መኳንንቱና ሊቃነጳጳሳቱ ይገኛሉ። ፀሎተወንጌል ከተደረገ በኋላ የዓመቱ ባለተራ ደብር ካህናትና መዘምራን "ተቀፀል ጽጌ ኃይለ ሥላሴ አጼጌ" እያሉ ያሸበሽባሉ። ለበዓሉ የተዘጋጀውን ግሥ ወደ ንጉሡ ፊት ቀርበው ያሰማሉ። ጳጳሳት ካህናትና የደብር አለቆች ንግግር ያደርጋሉ። ደብተራዎች ይፎካከራሉ። የመወድስ ቅኔ ለንጉሡ ያቀርባሉ። አንዱ ብርሃን ይላቸዋል። ሌላው ፀሐይ ያደርጋቸዋል። ሶስተኛው መልአክ አራተኛው አንበሣ . . .

ይህ የተቀፀል ጽጌ በዓል በሚከበርበት መስከረም 10 ቀን በአንዱ ዓመት የባለተራው ደብር አለቃ ቀረቡና :-

"ግርማዊ ጃንሆይ! አባትዎ ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት እነሆ የምድር ነገሥታት ተሰብስበዋልና እነርሱም በአንድነት መጡ። አንተንም አይተው አደነቁ፤ ብሎ ትንቢት የተናገረው ለግርማዊነትዎ መሆኑ በጎላ በተረዳ ግልጥ ሆኖ አግኝተነዋል" አሉ። የሌላውም ደብር አለቃ ተነሱና እጅ ነስተው ወደ ንጉሡ ቀረቡ:-

ከመምህርም መምህር ግርማዊ ባሕቲቱ፣
የተገለጠበት ምስጢረ ምፅአቱ፣
አቢይ ደብረ ታቦር መንበረ መንግሥቱ።
በታቦር የታየ ኤልያስ እንዳየው፣
ኃይለሥላሴማ ኃይለሥላሴ ነው።
ከመላዕክት አንዱ ቴዎፍሎስ ያየው፣
መልአክ አባጠቅል ዘላለም ሕያው።
ደጋጎች ነቢያት ያዩትን አየነ፣
ዓለም በጠቅላላው የእግሩ ጫማ ሆነ።"

በማለት መወድስ ቅኔ አቀረቡ።

አንድ የሾረ ደብተራ ደግሞ
'እምቢ! እምቢ! እምቢ!' እያለ እንደፎካሪ እየተንጎራደደና እየተቁነጠነጠ ቅኔ ይዞ ቀረበ።

"እምቢ! እምቢ! እምቢ! እምቢ!
ኃይለሥላሴ የኢትዮጵያ መሪ
አይደለህም እምቢ!
ኃይለሥላሴ የኢትዮጵያ ፈጣሪ
አይደለህም እምቢ!
ኃይለስላሴ የተቀባው ለኢትዮጵያ አይደለም።
እምቢ! እምቢ! የአፍሪካ መሪ ነው።
የአፍሪካ አባት ነው እምቢዮ!
የአፍሪካ መሪ ነው" አለ።

ንጉሡ ከተቀመጡበት መነሳት እስኪቀራቸው ድረስ በዙፋናቸው ውስጥ ውዝውዝ ይሉ ነበር። እንዲህ እንዲህ እየተባለ ንጉሡን አሳወሯቸውና ራሳቸውን ከፈጣሪ ጋር ማወዳደር መጣ። ንጉሡን የተመኩ ዙፋኑን የተጠጉ ይህን ዋርካ የተጠለሉ እንዲሁም የገዥነት ሰማያዊ ደም በደም ስሮቻቸው የሚንፎለፎል የጥቂት ዜጎች እብሪት ልክ አጣ። ችጋርና ቅማል በወረሰው ድሃ ትከሻ ላይ ተንፈራጠው ተቀመጡ። . . . የዛሬ ስንት ዓመት ገደማ ከእነዚህ እብሪታቸው ልክ ካጣው ዜጎች መካከል እንዲቱ ቀብራራ ወይዘሮ "ለመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስንት ይሆናል?" ተብላ ተጠየቀች አሉ። "እሰሱም ገሰሱም ካልተቆጠረ በቀር የኢትዮጵያ ሕዝብ የምንባለው አምስት መቶ ብንሆን ነው" አለች አሉ። የተቀረው ስንት ሚሊዮን ኢትዮጵያዊ ከቁጥር አይገባም። ከእርሷና ከመሰሎቿ ጋር እኩል ልትቆጥረው ተቸገረች። እብሪት ልቧን ደፍኖ አይኗን ጋረደውና በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን የእርሷው ቢጤ ጠይም ኢትዮጵያዊ ወገኗን እሰስ ገሰስ አለችው። ከቁጥር ልትጥፈው ተጠየፈች። ያቺን ደንቆሮ እብሪተኛ አለም ሰማት። ሰማይና ምድርም ሰሚት። ከደመናም በላይ ያለው ፈጣሪ ሰማት። በየቀበሮ ጉድጓዱና በየበረሃው ኮዳውን ተንተርሶ እንደተኩላ የተራበ ወታደር አዘዘባት። ከእሰስ ገሰስ የተቆጠረው ድሃ ሕዝብ ቀፎው እንደተነካ ንብ ወረራት። ያ የተመካችበት ዙፋን፣ የኮራችበትና የታበተችበት ሰማያዊ የገዥነት ደም፣ ፀሐዩ ንጉሠ-ነገሥት አላስጣሏትም። የተራበው ተኩላ ቆርጥሞ በላት። የተራበው ተኩላ ለንጉሡም አልራራላቸውም። አላሳሱትም። ውርደት አከናንቦ ትንፋሽ ሲያጥራቸው በትራስ አፍኖ ገደላቸውና ከመፀዳጃ ቤቱ ግርጌ በአርማታ ለስኖ ቀበራቸው።

አዱኛ ብላሽ! የመወድስ ቅኔው ሙገሳው አበቃ። የተራበው ተኩላ ወደቤተመንግስት ገባ። የቤተመንግሥቱን ማማር የዙፋኑን ውበት ተመለከተ። ከንጉሡ ማዕድ በላ። ሆዱ የቻለለትን ያህል ዋጠ። እጁ ያነሳለትን ወሰደ። ጥጋብ ያዘው፤ ቁንጣን ወጠረው። የቆረጠው ጮማ የቤተመንግሥቱ እፍታ ልቡ ላይ ፈላበት። ጥጋብ አሰከረው። እብሪት የሚሆነውን አሳጣው። ከወንዶቹ ሰፈር ደርሶ የወንዶቹን ወንድነት መዝኖ አየ። ቀና ቀና ያለውን አንገቱን ቢቆርጡት የተቀረውን አንድ ላይ እንደ አጋሰስ አቆራኝቶ መጋለብ እንደሚቻል ታወቀው። የባለዲግሪዎችን ጎራ የምሁራንን መንደር ጎበኘው። ለሆዱ ያደረ ከርሣም እሾም እሸለም ባይ ቶስታሳ የሞላበት መሆኑን አጠናው። የካህናትና የደብተራዎችን አምባ ዘልቆ አየው። ከመሀል ከመሀሉ የሐር ቆብና ካባ ቢደፉበት፣ አለፍ አለፍ እያሉ ለአንዳንዱ የወርቅ መስቀል ቢያስጨብጡት የንጉሱ ቅኔ መወድስና ሙገሳው እንደማይቀርበት ገባው። ሁሉን አየ። ገመተ። መዘነ። የልብ ልብ ተሰማው። እብሪት ልቡን ሞልቶ እንደእብደት ጀማመረው። ከእኔ ወዲያ ማን አለ! ነብር ሆነ። ሁሉን ቢያየው ጭብጥ የማይሞላ ሆነበት።

"የፍየል ወጠጤ ትከሻው ያበጠ ልቡ ያበጠበት
እንዋጋ ብሎ ከነብር ላከበት።"

ሲል በአደባባይ አቅራራ። ፎከረ። ምድር ጠበበችው። "እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ አያዋጣም። አያስኬደንም" ያሉትን ዜጎች ርህራሄ በሌለው ዱላው ቀጠፋቸው። የልቡ አልደረሰም። አልበቃውም። ዘላለማዊነት አማረው። የፈጣሪም ሥልጣን አሰኘው። ቁስ–ቁሳቁስ እንጂ እግዚአብሔር የሚባል የለም ለማለት ደፈረ። በቀበሌ ስብሰባ፣ በውይይት ክበብ እግዚአብሔር አለ የለም ድምፅ ተሰጠበት። በድምፅ ብልጫ የክርስቲያን ደሴት የምትባለዋ ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን የማታውቅ ምድር ሆነች። የእብደት ዘመን – ሚሊዮኖች አገር አልባ ሆነው የተሰደዱበት፣ በረሃብ ያለቁበት፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ በጥይት የተቆሉበት፣ እናት በልጅዋ አስከሬን ላይ ቆማ መፈክር እንድትል የተገደደችበት፣ ቤተሰብ አስከሬን ለመውሰድ የጥይት ዋጋ የከፈለበት የእብደት ዘመን! መሪዎቻችን በእብሪት የሰከሩበት ዘመን! የእብሪት መፈክር በምድሪቱ የተስተጋባበት የእብሪት ዘመን! ይህን የመሪዎቻችንን እብሪትና ጩኸት አለም ሰማላቸው። ሰማይና ምድርም ሰሙ። የውሻ ደም የሚመልስ አምላክም ሰማቸው። በተጋጠ ጭንጫ መሬት ውስጥ ተቀብሮ አፈር ሲቅም የኖረ ፍልፈል አዘዘባቸው። ያ የተናቀው የተረገጠው ድሃ ሕዝብ ዳግመኛ ቀፎው እንደተነካበት ንብ ከያለበት ተመመ። ነብር ነኝ፣ አንበሣ ነኝ፣ ጎሽ ነኝ ሲል የነበረው ተኩላ ወደቀ። አልተነሳም። ፍርክስክሱ ወጣ። የሆዱን ሞራ እንደተልባ ያለጠለጠ የፊቱን ወዝ ፍልፈል በላው። ያ የተመካበት ጠመንጃው ኮትቻ ወድቆ ሙጃና ዳዋ በቀለበት። የፈረጠመ ክንዱን ቅልጥም፣ ሰንቱን የረገጠበት የእግሩን አንጓ ውሻ ቆረጠመው። ትንታግ አንደበቱ ከላንቃው ተጣብቆ አፉ ተዘጋ። ፊታ አኩምፕሊ!

ዛሬ ደግሞ ባለሳምንት ባለጊዜ ከቤተመንግስቱ ገብቶ ያተራምሳል። ያለፈበትን ጎዳና አያስተውስም። ረስቶታል። ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ ምቹ ወንበሩን ሁሉ ተኮፍሶበታል። እንደተስቦ ከሚጋባው የስልጣን እብሪትና ዕውርነት ግን ያመለጠ አይመስልም። "የኢትዮጵያ ፖለቲካ በትክክለኛው ሕዝባዊ መሠረት ላይ አልቆመም። የጎሣ ፖለቲካ አገሪቱን ለመከፋፈልና ለእርስ በእርስ ጦርነት ይዳርጋታል። ስልጣን አናሳ (minority) በሆነ አንድ ብሄረሰብ በሞኖፖል ተይዟል።" ተብሎ ለሚቀርብ አስተያየት "ለብዛት ለብዛቱማ ቦዬ – አሣማም ብዙ ነው" የሚሉ ደፋር ባለጊዜዎች ሞልተዋል። "ኧረ አይሆንም። ይህ አካሄድ የሚያዋጣ አይደለም። በሕዝቦች መካከል ፍጥጫ ጥላቻና ዕልቂት ያመጣል" ሲባሉ "ተወው ምን አባቱ ይሆናል? 400 ዳቾች ናቸው ደቡብ አፍሪካን ስንት መቶ ዓመት ቀጥቅጠው የገዙት" በማለት የሚመልሱ እብሪተኞች ብቅ ብቅ እያሉ ነው።

. . . በቅርቡ እዚህ አዲስ አበባ አንድ ሆቴል ይመረቃል። የሆቴሉ ባለቤቶች ከባለጊዜዎች ወገን ነበሩና አልፎ አልፎ ከተቀላቀለው በቀር አብዛኛው ባለጊዜዎቹ ነበሩ። ግብዣው ደርቶ ጨዋታው ሲጀመር ወንዱም ሴቱም ተነስቶ ክብ ሰርቶ "ደርብ" ይል ጀመር። ጨዋታው ደርቶ ተጋባዡም እየተሟሟቀ ሲሄድ ወንዶቹ የሴቶቹን ነጠላ ተቀብለው በወገባቸው ላይ ሸብ አድርገው ተሽከረከሩ። ትንሽ ቆይተው ሞቅታው ወደ ግለት ሲዳረስ ወንድ ወንዱ በነጠላው ምትክ ሽጉጡን አውጥቶ ከአናቱ በላይ እያሽከረከረ ክብ ሰርቶ ይጨፍር ጀመረ። አይን ያወጣች እብሪተኝነት ይሏል ይህቺ ናት!

. . . ሰሞኑን ከአንድ የመንግሥት ሱቅ (ሱፐር ማርኬት) ገብቼ ለልጆች የሚሆን ጨርቃ ጨርቅ እመለከታለሁ። አንድ ጠና ያሉ ሙሉ ሰው ጫማ ሊገዙ ያደረጉትን ጫማ አውልቀው አዲሱን ጫማ ይለካሉ። የሆናቸው አይመስለኝም። አልገባ ብሎአቸው ይታገላሉ። ሌላ ቁጥር እንድትሰጣቸው አስተናጋጇን ይጠይቁአታል። አስተናጋጇ አልሰማቻቸውም። T-shirt ይሁን ካኒቴራ የሚገዛ ሰው እየነተረካት አትሰማቸውም።

"እባክሽ የእኔ እህት ሌላ ቁጥር ስጭኝ" በማለት ለምን አልሰማሽኝም በማለት ሻጯን መቆጣት ይቃጣቸዋል።

"ቆይ እባክህ ጠብቅ?" ሲል ካኒቴራ የሚገዛው ሰው ያመናጭቃቸዋል። ሰውዬውም ግራ ተጋብተው "ሁለታችንም ገበያተኞች ነን ምን ያስቆጣሃል?" ሲሉ ያፈጡበታል። ካኒቴራ የሚገዛው ሰው የእኚህን ሰው ቁጣ ከምንም ሳይቆጥር ካኒቴራውን ለመለካት የፈለገ ይመስል ኮቱን አወለቀ። ሰውዬውም ገርሞአቸው ዝም ብለው ይመለከቱታል። ኮቱን ሲያወልቅ ውኃ የመሰለ ኮልት ሽጉጥ ከብብቱ ስር ተጋድሞአል።

አምስት ስድስት የሚሆኑ ጥይቶች እሰገባው ላይ የኮረዳ ጥርስ መስለው ተደርድረዋል። ሰውዬው በድንጋጤ ለትንቹ አፍታ እስገባው ውስጥ የተጋደመውን ሽጉጥ ተመለከቱና ሊገዙት የነበረውን ጫማ ወዲያ ጥለው እያጉረመረሙ ተፈተለኩ። የኮቱ መውለቅ ካኒቴራ ለመለካት ሳይሆን ማንነቱን፣ የዜግነት ደረጃውን ሊያሳያቸው መሆኑ ገብቶአቸዋል። ቅልብጭ ያለች እብሪት!

እብሪተኛ የገዛ ኩሱን ይበላል፤ እብሪት ምንትስ ያስበላል ይባላል። . . . ሰውዬው ጊዜ የሰጠው እብሪተኛ ነው አሉ። አንድ ቀን ሲፀዳዳ ሌባ ጣቱን አይነ-ምድር ይነካበታል። በዚህ የተበሳጨው እብሪተኛ ሆዬ "ይህቺ ጣቴ ያለቦታዋ ገብታ አይነምድር ጠንቁላለችና መቆረጥ አለባት" ብሎ ይወስናል። ከጣቱም ላይ አይነምድሩን ሳይጠርግ እጁን አንጠልጥሎ ጣቱን ቀስሮ ቢላዋ ወደሚሰሩ ባለእጆች ዘንድ ይሄድና "ይህቺ ጣቴ ያለ ቦታዋ ገብታ አይነምድር ነክታለችና ትቆረጥልኝ" ይላቸዋል። በነገሩ የተገረሙት ባለእጆች በሳሙና ብታታጠበው ይለቅልሃል። ጣትን የሚያክል ነገር መቆረጥን ምን አመጣው? ብለው አንቆርጥልህም ይሉታል። ከእነርሱ እልፍ ብሎ ወደአለው ቀጥቃጭ ይሄድና "ይህቺ ጣቴ ዓይነምድር ጠንቁላለችና ትቆረጥልኝ" ይለዋል። ቀጥቃጩም በሁኔታው ይገረምና "በሳሙና ታጠበው" ብሎ ይመልስለታል። "የለም። ያለቦታዋ ገብታ መንካት የሌለባትን ነክታለችና ትቆረጥልኝ" ይለዋል። ቀጥቃጩም "በል ና ወዲህ ጠጋ በል" ይለውና ከፍሙ ውስጥ ቀይ ሆኖ የጋለ ማረሻ በጉጠት አውጥቶ ያቺን ጣቱን ቸስ፣ ድብን አደረገው። የጋለ ማረሻ ጣቱ ላይ ያረፈበት አቶ እብሪተኛ ሰማይ ምድሩ ዞሮበት ነፍሱ እስክትወጣ ጮሆ ትቆረጥልኝ ብሎ ከነአይነምድሯ ቀስሯት የመጣውን ጣቱን ሃም! አድርጎ ጎረሳት ይባላል። እብሪት እንትን ያስበላል ማለት እንደዚያ ነው።

ለመሆኑ እናንተስ እንዴት ናችሁ? ይኽ እብሪት የሚሉት በሽታ እናንተስ ዘንድ አለ ይሆን? የእናንተው ደግሞ እንዴት የሚያደርገው ይሆን? የሚሰማችሁ ቢሆን እብሪት እንትን ያስበላል በሉልኝ!!

በቸር ይግጠመን የናንተው ወርቃየሁ (ከአዲሳባ)

---

## ይህን መስለን ከረምን !







ማሞ ወልዴ ጥንት (ችቦ የያዘው)





የከምሴ ኮረዳዎች

የአፋር ገበያ



ጭድ ተራ



# ሰላምታ ከወደ ባህር ማዶ

# ከይግለጡ ለወርቃየሁ

ያገር ልጅ ወርቃየሁ እንደምን ከርመሃል። መቼም በግንባር አንተዋወቅም። ያጠናሁህ በወርቅዬ ብዕርህ ነው። ማን ያውቃል። ይች ዓለም ጠባብ ናትና አንድ ቀን ጊዜው ሲፈቅድ እንገናኝ ይሆናል። እስከዚያው እስቲ ወንዝ አቆራርጠህ፣ አህጉር ሰንጥቀህየምትወረውረውን ቀለም አታንጥፈው። መልስ ብጤ የሚሰጥ፣ አስተያየት ቢጤ የሚሰነዝር፣ እኛም እንዲህ ነን የሚል ቢጠፋ ነው ብዕሬን ያነሳሁት። እና እንግዲህ የታከተ ይረታ፣ ይሸነፍ ባይ ነኝ። አንተ ትታክታለህ የሚል ሃሳብ የለኝም። ምነው ቢባል ምን የሚሰራ ይኖርና ለዚህ ትሰንፋለህ ሙያህን በጎበዞቹ ሳትቀማ አትቀርምና ክንድህ በርትቶ አፀፋውን እስኪመልስ ድረስ ነገር መልቀምህን፣ ወሬ መቃረምህን አታቁም። ሹክ ማለት ደግሞ የዘመኑ ቁም ነገር "ተኩሶ መጣል ወይም ወሬ መተኮስ" መሆኑን አትዘንጋ። አይ የእኔ ነገር ገና ከጅምሩ እኔም ነገር መተኮስ ጀመርኩ መሰለኝ። አትቀየም ቅያሜ ደግ አይደለም። ባይሆን እያለሳለሱ መያዝ ነው ደጉ። ዳሩ ምን ልትጎዳኝ? እስራ ሁለት ሺህ ማይልስ አቋርጠህ ትግል አትገጥመኝ። እዛው ከጎበዞቹ ጋር፣ ክንደ ብርቱዎቹ ላይ በርታ። እኔ እንደሁ ዳር ቆሜ የእናንተን መጨረሻ ማየት ነው የናፈቀኝ። ለነገሩ የእናንተ መጨረሻና የሀገሪቱ ዕጣ ፋንታ ምን ይሆን? አያያዛችሁ ደግም አይደል። የሰው ፍጥረት እኩል መሆኑ ቀርቷል አሉ። አንዱ ሌላውን መዝለጥ፣ ብርቱው ደካማውን መቀማት የዕለት ተግባር ነው ይባላል። ለእውነትነቱ ባልጠራጠርም አንዳንዴ ጎበዞቹ ደግ አረጉ፣ ይህም ሲያንስ ያሰኛል። ምነው? እንዳትለኝ መልስ አልሰጥህምና።

አየህ ልጅ ወርቃየሁ "ሃበሻ አንዴ የጎረሰውን ዓመት ያላምጣል" ተረቱ ካልሠራ ዘመን በተለወጠ ቁጥር እያላመጣችሁ መኖር ነው። "የጎረሱትን ለመዋጥ አለመታደል የሽንፈት ምልክት ነውና።"

ሳላውቀው የአገር ጉዳይ ጎተተኝ። እስቲ የእኛን ላውጋህ። እምይ አሜሪካ አገር አትምሰልህ! ሁሉ በእጅህ ሁሉ በደጅህ ነው። ዘመን የወለደው፣ ምርምር የፈጠረው በማለዳ እጅህ ላይ ይወድቃል። እንዳሻህ ተናግረህ፣ እንደፈለገህ ተዘዋውረህ መሸቀል መብትህ ነው። በዘር፣ በሃይማኖት፣ በፆታ የሚፈጠር አድሎ አትመለከትም። ሁሉም እኩል ነው። ዘሩን የሚቆጥር በፍፁም አታይም "ሃይማኖትና ዘር የግል ነው አገር የጋራ ነው" የሚል ትልቅ እምነት አለው። በፖለቲካ ድርጅት ተከፋፍሎ መነታረክ፣ መዋጋት፣ ገድሎ መሾም፣ መመስገን ቦታ የላቸውም። ሁለት ወር ጫካ ከርመህ ነፃ ላወጣችሁ መጣሁ ብትል ድፍን አሜሪካ ተሰልፎ ይስቅብሃል። ለዚያውስ መሸፈትህን ማን ከጉዳይ ቆጥሮት። ድንገት አምርረህ ጫካ ብትገባ እንኳ አንተን ለመውጋት ጦር ማዝመት አያስፈልግም። የሸፈትክበትን ጫካ ዙሪያውን በሽቦ አጥረው የቱሪስቶች መዝናኛ ያደርጉታል። "የሰው አውሬ የሚኖርበት ጫካ" የሚል ትልቅ ምልክት ይደረግልሃል።

ታዲያ አንተን ለማየት የመጣው ህዝብ ላይ አደጋ ብትጥል አንተን አያድርገኝ። ይኼውልህ ሽፍትነት በአሜሪካ ይህን ይመስላል። በእኛ አገር ግን ክብር ነው። አለተቀናቃኝ ቤተመንግስት ለመግባትና የፈላጭ ቆራጭነት ሥልጣኑን ለመጨበጥ ሁለት ወር እንጦጦ ተራራ ላይ ወጥቶ ቡራ ከረዮ ብሎ መመለስ የጀግንነት ምልክት ሆኗል።

አይ አሜሪካ! የስንቱን አገር ልብ ታስኮበልል መሰለህ? እስኪገቡባት ውስጧን እስኪያዩ ልብ የምታሸፍት አገር። ታዲያ ሁሉም ነገር እንደሚወራው እንዳይመስልህ። አንድ ቀን ስራ ከፈታህ የሁለት ቀን ቀለብ ማጣትህ ነው። ካልደከመህ ግን ተደራቢ ሥራ ፈልገህ መስራት መብትህ ነው። የመተዳደሪያህን ሥራ የሚቀማ ወያኔ ይገጥመኛል ብለህ መስጋት የለም። ሁሉም ይሮጣል። በአቅሙ፣ በችሎታው ይሸቅላል። የጉልበት ሸቀላም ብቻም አይደል። ጥሩ ምላስ ያለው በቀልጣፋ አንደበቱ ፋራውን በአደባባይ መላጨት አይከለከልም። እንደ አገር ቤቱ ቁጭ በሉዎች እንዳይመስህ። በህግ የታወቁ ቁጭ በሉዎች እንደ አሸን የፈሉበት አገር ነው። ልብ በሚሰልብ ደብዳቤ "የእኛን ምርት በዚህ ዋጋ ከገዛህና ዕድልህ ከቀናህ የዚህን ያህል ሚሊዮን ብር ባለቤት ትሆናለህ" ይሉሃል። ይህ እንግዲህ "ሸቀላ በቀላጤ" የሚሉት ነው። ይኸው ማስታወቂያቸው በሬድዮ፣ በጋዜጣ፣ በቴሌቭዥን፣ በበራሪ ወረቀት ሲለፈፍ ትሰማለህ። ልብህ ከሸፈተ ዕድልህን መሞከር ነው። በዚህ ያተረፈ ሰው ግን አይታይም፤ ቢበዛ እያዋጣህ ጥቂት ጮሌዎችን መደጎሙን ማንም አይከለክልህም።

ይኸውልህ የአሜሪካ ሕዝብ ብዛቱ ከ250 ወደ 263 ሚሊዮን ከፍ ካለ ትንሽ ወራት አስቆጠረ። ይኼ ቁጥር እኛን መጤዎቹንም ይጨምራል። አገሪቷን በአሁኑ ጊዜ የሕዝብ ብዛት የሚያስፈራት አይመስልም። ለጊዜው ሰፊ ባዶ መሬት፣ ብዙ የሰው ኃይል ያስፈልጋታል ግን ከአሁኑ ቁጥጥር ካልተደረገ በመጪዎቹ 100 ዓመታት መቆሚያም የሚገኝ አይምስልም። ሁሉም ሩጫው ወደ አሜሪካ ነው። ከተወለደበት መንደር ይልቅ አሜሪካን የማይናፍቅ ሰው ያለ አይመስለኝም። ለምን ቢባል ሁሉም መልሱ አንድ ነው። "I Love America".

አንዳንዴ ሳስበው የአገሬ ሰው ስለ አሜሪካ መታመም ከጀመረ የቆየ ቢሆንም የዘንድሮው የባሰ ይመስለኛል። ሕዝበ ክርስቲያንና ሕዝበ እስላም ስለ ሀገሩ ማሰብ፣ መቆርቆር፣ መታመም ጭራሽ ያቆመ መሆኑን የተረዳሁት አሁን ነው።

ወርቃየሁ! እንዴት? ለመሆኑ ምን ሰምተህ ነው እኛነታችንን የረሳን የምታስመስለን ትለኝ ይሆናል። ተገቢ ጥያቄ ነው።

በቅርቡ ከአንድ አገር ቤት ሳለሁ በጣም ከምቀርበው ወዳጄ የተፃፈልኝን ደብዳቤ ዝርዝሩን ትቼ ቁም ነገሩን ላስነብብህ። ደብዳቤው በሰላምታ ይጀምርና ወደ ዝርዝሩ ሲገባ እኔ ከምጠብቀው ውጪ ሆኖብኝ እንደማስገረምም ማሳቅም ከጀለኝ ሁለት ገፅ ሙሉ ስለአሜሪካ ሕገ መንግስትና አገሪቱ በውጪው ዓለም ስላላት ፖሊሲ ይተነትናል። ዝቅ ሲል ደግሞ የማይክል ጆርዳንን ወደ ቅርጫት ኳስ ተጫዋችነት መመለስና ስለ ኦጄ ሲምሰን የፍርድ ቤት ሙግት ያወራል። የእክላሆማ የቦንብ ፍንዳታ፣ የማይክል ጃክሰን አዲስ አልበም ለማስቀረጽ የሚያደርገውን ዝግጅት ሁሉ በደብዳቤው ላይ ሰፍሯል። በእያንዳንዱ አስተያየት የራሱን ሃሳብ ሲተነትን ደግሞ የአሜሪካንን የውጪ ፖሊሲ እንደ አንድ የኮንግረስ አባል ሆኖ በድጋፍ ድምፅ ሲሰጥ፣ የማይክል ጆርዳንን ወደ ቅርጫት ኳስ ተጫዋችነት መመለስ ተገቢ ነው ባይ ነው። የጃክሰን አዲስ አልበም ለምን እስካሁን እንደዘገየ ቆጭቶታል። ኦጄ ሲምሰንን በፍፁም ከደሙ ንፁህ ነው ይላል። ደብዳቤውን በአንክሮ ደጋግሜ በማንበብ ታዘብኩት። ትናንት በቁምነገረኛነቱ፣ በቤተሰብ ኃላፊነቱና በአገር ተቆርቋሪነቱ የማውቀው ሰው አልመሰል አለኝ። እስቲ በማያውቁት ነገር ላይ መፈላሰፍና መቆጨት ምን የሚሉት ቋንቋ ነው።

ይህን የሚመስል ስመለከት የአገሬ ሰው ልቡ እንደተሰለበ፣ ለራሱ እንዳያስብ፣ እቅሙን ብቻ ሳይሆን አዕምሮውንም የተቀማ መሆኑን ለመገመት ጊዜ አልፈጀብኝም። "ሰው እንዴት ያልበላውን ያካል።"

ወደ አሜሪካን ልመልስህ። በዚህች አገር መብትና ግዴታ ጎን ለጎን በእኩልነት የሚሄዱ ሲሆኑ ሁሉም ግዴታውን ማክበርና በመብቱም መጠቀም በህግ ላይ የሰፈረ ደንብ ብቻ ሳይሆን ባህልም ጭምር ነው።

ወንዶች በሴቶች ላይ የሚፈፅሙት የበላይነት ድርጊት በዚህ ምድር ላይ አይሞከርም። ልፈፅምም ብትል እንኳን ፀጉርህን ተላጭተህ ዘብጥያ (ከርቸሌ) መውረድህ ነው። የተለያየ ሃይማኖትና ዕምነት ያላቸው ህዝቦች የሚኖሩት በአንድ ዓይነት የህግ ጥላ ስር ሲሆን የዘር ህግ፣ የሃይማኖት ህግ የሚባል ነገር የለም።

ታዲያ በዚህ ሁሉ ለረጅም ጊዜ ተለፍቶበት በደረጀ ህግ ስትኮራ አንዳንድ ከተፈጥሮ ውጭ የሆነ ድርጊት ስታይ ደግሞ ቅር ይልሃል።

ብዙ አስቀያሚ ድርጊቶችን ትቼ አንዱን ላውጋህ። በሰው ተፈጥሮ ሁሉም የፆታውን ሚና እንዲጫወት ተፈጥሮ ያስገድደዋል። በዚህች ምድር ላይ ግን የተፈጥሮ ህግ በግለሰቦች ሲረገጥ ታያለህ።ሴት በሴትነቷ፣ ወንድ በወንድነቱ ተፈጥሮ በለገሰቻቸው ስሜት መዋደድ፣ መፋቀር፣ መጋባትና ልጅ ወልዶ ቤተሰብ መመስረት በተፈጥሮ ህግጋቱ የተለመደና ያለ መሆኑን የሚዘነጋ ዓለም ግን በተቃራኒው ወንድ የወንድ፣ ሴት የሴት አፍቃሪ ሲሆን አያስደነግጥህም። በአሜሪካ ምድር የተመሳሳይ ፆታ ግኑኝነት በአደባባይ ወጥቶ አገር ያወቀው የሕብረተሰብ ችግር መሆኑ ከታወቀ የቆየ ቢሆንም በያዝነው ዘመን የምታየው ግን በኃጢያትነቱ ተወዳዳሪ የለውም።

እስቲ አንድ ጥያቄ ላቅርብ?

"የአቶ ታምራትና የአቶ ከበደ የጋብቻ ሥነሥርዓት በዚህ ቀንና በዚህ ቦታ ስለሚፈፀም በስፍራው እንዲገኙልን" የሚል የሠርግ የጥሪ ወረቀት እጅህ ላይ ቢወድቅ ምን ይሰማሃል። ወይም "ወ/ሮ ከበቡሽና ወ/ሮ ምፅላል በዚህ ቀን ጋብቻቸው ተፈፀመ" የሚል ወሬ ብትሰማ ምን ትላለህ?

አልጨረስኩም። ከዚህ ሳልርቅ ብዙ የምለው አለኝ። በአሜሪካ ስላለው የኢትዮጵያ ፖለቲካና ፖለቲከኞች፣ ድርጅቶችና የዜጎቻችንንም ስለሃገሩ ያለውን ስሜት የዘነጋሁ እንዳይመስልህ ሁሉንም በደረጃ ተከታታይ ዓላማዎቼ ናቸው።

እስከዚያው በቸር ያቆየን።

ይግለጡ ነኝ - ከነፋሻዋ ከተማ



# ሀናና ብንያም
# የልብስ ስፌትና ዲዛይን
# H & B TAILORING

የሠርግ የሚዜ ልብሶች በትዕዛዝ እንሠራለን።

ጤፍ ዱቄት
በሶ
እልበት
ቡና
በርበሬ
ሚጥሚጣ
ሽሮ
ቅመም በያይነቱ
በተጨማሪ
የቪዲዮ ካሴቶች
የቴፕ ካሴቶች
የተለያዩ መጽሄቶች

**ወለላ ወርቁ**
**WOLELA WORKU**

LEMO SERVICE
ለሠርግና ለልዩ ዝግጅት
የሌመዚን አገልግሎትም
እንሰጣለን።
1-800-679-1816
Pager- 738-7783

የተለያዩ የአገር ባህል
ልብሶች እንሸጣለን።

431 North Indian Creek Rd
Suite E
Clarkston, GA 30021
Phone: (404)296-2766
Pager - 632-6283

ቆንጆ ጤፍ እንጀራም እንሸጣለን
ጎብኙን!



# RE/MAX®
## today's inc.
an independent member broker

ቤት መግዛት ለምትፈልጉ
መሬት ገዝታችሁ መሥራትም
ሆነ Subdivision ውስጥ ለማሠራት የምትፈልጉ
ሁሉ ደውሉልኝ እረዳችኋለሁ።

የክሬዲት ሆነ የሥራ ማጣት ችግር
ቢኖርቦትም ጭንቀት የለም ወገኖች
ደወሉልኝ።

ሁልጊዝም ኮሚሽን የምከፈለው
በሚሸጠው ሰው ነው።

WOW!
YO! YO!



*Have Cash?*
*Bad Credit?*
*No Job?*
*No Problem*
*Just Call me.*

- *Residential*
- *Commercial*
- *Business*
- *Relocation*
- *Forclosures*
- *HUD*



*Selamawit "Sammy" Tadesse*
*Realtor*

**ሰላማዊት ታደሰ**

*Remax Today's Inc*
*1597 Phoenix Blvd. Suit - 5*
*College Park, GA 30349*

*Tel - (404) 907-0525*
*or 907-0183*
*Fax - (404) 907-0524*

# እንዲህ ሆነ

በኢትዮጵያ የላንዳፍታ ወኪል የተጠናቀረ

## የሚያዝያ 29ኙ ምርጫ ተካሄደ። ኢሕአዴግ አሸንፌያለሁ አለ።

የሕዝብ እንደራሴዎችና የክልል ምክር ቤት ተወካዮች ምርጫ በተያዘለት ቀን ቀጠሮ መሠረት ከአፋር ከሐረሪና ከኦጋዴን ክልሎች በቀር በመላው ኢትዮጵያ ተካሂዷል። ከ15 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ በመራጭነት ተመዝግቦበታል በተባለበት በዚህ ሕዝባዊ ምርጫ የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች ያቀረቧቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎችና ጥቂት የግል ተወዳዳሪዎች ብቻ የቀረቡበት መሆኑ ታውቋል። በዚህም ምርጫ ኢሕአዴግ ከፍተኛውን ድምፅ በማግኘት ተመርጧል ሲል የምርጫ ቦርዱ ይፋ አድርጓል።

ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ያልተሳተፉበት ይህ ምርጫ ከመነሻውም ኢሕአዴግን ሕጋዊ ሽፋን በመስጠት የአገዛዝ ዘመኑን ከማራዘም ያለፈ ፋይዳ የለውም በማለት ከፍተኛ ተቃውሞና ትችት ሲሰነዘርበት የቆየ ሲሆን ኢሕአዴግ በምርጫው አሸንፌያለሁ እንደሚል አስቀድሞም ይታወቃል ሲሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች በእርግጠኛነት ይናገራሉ። ለምርጫው ማስፈፀሚያ 94 ሚሊዮን ብር ወጪ መደረጉም ታውቋል።

የሽግግር መንግሥቱ ፕሬዚዳንት አቶ መለስ ዜናዊ በተወለዱበት የአድዋ ከተማ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ ትግል የጀመርኩበት ባሉት ጋይንት በዕጩነት ለውድድር ቀርበው በከፍተኛ ድምፅ መመረጣቸውን መንግሥታዊ የዜና ምንጮች ገልፀዋል።

* * *

## የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት አገር አቀፍ ጉባኤ እየጠራ ነው።

በዶ/ር በየነ ጴጥሮስ የሚመራው የሰላምና የዲሞክራሲ አማራች ኃይሎች ምክር ቤት ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች ያቀፈ አንድ ብሔራዊ ጉባኤ በመጥራት ላይ መሆኑን አስታወቀ። የጉባኤው ጥሪ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ላሉ የሀገሪቱ ጉዳይ ይመለከተናል ለሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ እየተሰራጨ መሆኑን ምክር ቤቱ ገልጸ ውይይቱም "ነፃ ርዕታዊና ሐቀኛ ምርጫ" እንዲሁም "ዲሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት" የሚሉ አቢይ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ መሆኑን አስታውቋል። ጥሪው ለኢሕአዴግና በኢሕአዴግ ዙሪያ ለሚገኙ ድርጅቶች፣ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ለሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ በመዳረስ ላይ መሆኑም ታውቋል። ኢሕአዴግ ሕዝባዊ ምርጫ ተካሂዶ ተመርጫለሁ በሚልበትና ለሌላ አምስት የሥልጣን ዓመታት በሚዘጋጅበት በአሁኑ ወቅት የተጠራው ይህ የአማራጭ ኃይሎች ም/ቤት አገር አቀፍ ጉባኤ ከባድ ፈተና ሊገጥመው እንደሚችል የፖለቲካ ታዛቢዎች ይገምታሉ።

## በምርጫው ዋዜማ በድሬዳዋ የቦምብ ፍንዳታ ደረሰ፤ የሰው ሕይወት ጠፋ።

ሚያዝያ 25 ቀን 1987 ዓ.ም ምሽት በድሬዳዋ ከተማ ልዩ ስሙ ጫት ተራ ተብሎ በሚታወቀው የገበያ ቦታ በተጣለ ቦምብ 12 ሰዎች ወዲያውኑ ሲሞቱ 18 ሰዎች በፅኑ መቁሰላቸውን ከስፍራው የደረሱ ዜናዎች አስታውቀዋል። ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች የተጣሉት ቦምቦች ዒላማ ማን እንደሆነ ባይታወቅም በዚያው ሰሞን በድሬዳዋ ከተማ በሁለት ቀናት ልዩነት አራት ቦምቦች መጣላቸውን ዜናው ጨምሮ ገልጿል። የድሬዳዋ አካባቢ የኦጋዴን ነፃነት ግንባር፣ የኦሮሞ እስላማዊ ነፃነት ግንባርና የሱማሌ ተቀናቃኝ ቡድኖች ወታደራዊ ግብግብ የሚታይበት መሆኑ ይታወቃል።

በተያያዘ ሌላ ዜና ግንቦት 28 ቀን 1987 ዓ.ም በአርባምንጭ ከተማ አንድ አሜሪካዊ ዜጋ በተወረወረባቸው የእጅ ቦንብ መገደላቸውንና አንድ የኔዘርላንድስ ዜጋ በጽኑ መቁሰላቸው ተዘግቧል። ስለሁኔታው የአሜሪካ ኤምባሲ በሰጠው መግለጫ ሟቹ አሜሪካዊ በኢትዮጵያ ውስጥ በግል የሚኖሩ መሆኑን ጠቅሶ አደጋው የደረሰው በአጋጣሚ ነው ብሏል። በሌላ በኩል በሰኔ ወር የመጀመሪያ ሳምንታት ያልተለመደ የሰራዊት እንቅስቃሴ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ መታየቱን የተለያዩ የዜና ምንጮችና የአይን ምስክሮች ጠቁመዋል።

## ኢሠማኮን የሚተካ ተለጣፊ የሠራተኛ ማኅበር ሊቋቋም ነው።

ለግል ጥቅማቸው በቆሙ ጥቂት ምንደኞች አማካይነት የፖለቲካ ሥርዓቱን በሎሌነት የሚያገለግል ተለጣፊ የሰራተኛ ማኅበር ለማቋቋም በመንግሥት በኩል በግልጽ እንቅስቃሴዎች እየተካሄዱ መሆናቸውን አቶ ዳዊ ኢብራሂም የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን (ኢሠማኮ) ሊቀመንበር አስታወቁ። አቶ ዳዊ በሰጡት መግለጫ በሥልጣን ላይ የሚገኘው ኢሕአዴግ ለግል ጥቅማቸው የቆሙ ጥቂት የማኅበር መሪዎችን በመጠቀም በኢትዮጵያ ሠራተኞች እንቅስቃሴ ላይ መሰናክል ፈጥሯል፤

ብሔራዊ ማኅበሩን አግዷል ሲሉ አማረዋል። እያይዘውም የኢሠማኮ ቢሮዎች መታሸጋቸውን፣ ሠራተኛው ከደመወዙ አዋጥቶ የገዛቸው ተሽከርካሪዎች ተቀምተው ለፖለቲካ ድርጅቶች መሰጠታቸውንና ከ2 ሚሊዮን ብር በላይ የማኅበሩ ገንዘብ የት እንደደረሰ እንደማይታወቅ ጠቅሰው የመንግሥት የወቅቱ እንቅስቃሴ ኢሠማኮን የሚተካ ተለጣፊ የሠራተኛ ማኅበር ለመመስረት መሆኑን ተናግረዋል።

## በአዲስ አበባ የታክሲ ሾፌሮች የሥራ ማቆም አድማ አደረጉ

በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የታክሲ ሾፌሮች በግንቦት ወር አጋማሽ ላይ የሶስት ቀን የሥራ ማቆም አደረጉ። በትራፊክ ፖሊሶችና በመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ተቆጣጣሪዎች አግባብ ያልሆነ ተጽዕኖ ተደረገብን በማለት በተካሄደው በዚህ የታክሲዎች የሥራ ማቆም አድማ የታክሲ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ በመቋረጡ ከፍተኛ የትራንስፖርት ችግር በተጠቃሚው ሕዝብ ላይ አስከትሎ እንደነበር ታውቋል። ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣኖች ከታክሲ ባለንብረቶችና አሽከርካሪዎች ጋር ባደረጉት ውይይት ከሶስት ቀናት የሥራ ማቆም አድማ በኋላ ታክሲዎቹ ሥራ ጀምረዋል። ይህ ድንገተኛና ያልታሰበ የታክሲዎች የሥራ ማቆም አድማ በመንግሥት ባለሥልጣኖች ዘንድ ድንጋጤ መፍጠሩንና የአድማው አስተባባሪዎች ናቸው የተባሉት ግለሰቦች በስውር ተለቅመው መታሰራቸው ውስጥ አዋቂ ምንጮች ይጠቁማሉ።

## የፖለቲካ መጠለያ ተፈናቃዮች ዳግመኛ ተፈናቀሉ

ኢሕአዴግ መላ ኢትዮጵያን በተቆጣጠረበት ወቅት ከኤርትራና ከሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች የተፈናቀሉ ተፈናቃዮችና የቀድሞ ወታደሮች በየጥጋጥጉ የሰሩት የፕላስቲክ መጠለያዎቻቸው በፖሊስ ኃይል ፈርሰው ዳግመኛ መፈናቀላቸው ታውቋል። በተለይም በጥቁር አንበሳ አጥር ዙሪያ የላስቲክ ቤቶች ሰርተው ይኖሩ የነበሩት የቀድሞ ውታደሮች በሚካሄደው ምርጫ ኢሕአዴግን ከመረጣችሁ መጠለያዎቻችሁ አይፈርሱም ተብለው ምርጫውን ካካሄዱ በኋላ ግንቦት 6 እኩለ ሌሊት ላይ በፖሊስ ኃይል ከበባ በማድረግ በመሣሪያና በዱላ በማስፈራራት የፕላስቲክ መጠለያዎቻቸው እንዲፈርሱና ከፊሉም እንዲቃጠል መደረጉን የተፈናቃዮቹ ተወካዮች አስታውቀዋል። በዚህም ምክንያት ሶስት ተፈናቃዮች በብርድና በረሃብ ለሞት መብቃታቸውን፤ የሌሎቹም ሕይወት በከፍተኛ አደጋ ላይ መሆኑን ተወካዮቹ ገልፀዋል።

## የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤን ለመበተን ጥቃት እየተካሄደበት ነው።

በፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም የሚመራውን የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ ለመበተን በተለያየ መልኩ ጥቃት እየተካሄደበት መሆኑን ጉባኤው በሰጠው መግለጫ አስታውቋል። እንደጉባኤው መግለጫ ጥቃቱ የተጀመረው "ዲሞክራሲ የሕግ ልዕልና ሰብአዊ መብቶች ቃልና ተግባር" በሚል ርዕስ ጉባኤው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ካሳተመው መጽሐፍ ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ የስዊዘርላንድ አምባሳደር ጋር በተፈጠረው አለመግባባት መሆኑን አክሎ ገልጿል። የስዊዘርላንድ ኤምባሲ ለመጽሐፉ ማሳተሚያ ለኢሠመጉ የ10 ሺ ዶላር ዕርዳታ የሰጠ ቢሆንም መጽሐፉ ታትሞ ከተሰራጨ በኋላ ግን አምባሳደሩ ሚዛናዊነት የጎደለው ስድብ አዘል ደብዳቤ ለጉባኤው መፃፋቸውን ጉባኤውን ገልጾ አስሩ ሺ ዶላር አምባሳደሩ የኢትዮጵያን ሕዝብ በሙሉ የሰደቡበት ስለሆነ በቅርቡ ገንዘቡን ከተቆርቋሪ ወገኖች አሰባስቦ እንደሚመልስላቸው አስታውቋል። የሽግግር መንግሥቱን የሰብአዊ መብት ረገጣ በፎቶግራፍ በተደገፉ ማስረጃዎች ያቀረበው ይህ መጽሐፍ እንደታተመ ጉባኤው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ውስጥ ያስቀመጠው ከ600,000 ብር በላይ እንዳይንቀሳቀስ በመንግስት ታግዷል። በተያያዘ ሌላ ዜና በግንቦት ወር መጨረሻ ገደማ የኢሠመጉ ቢሮ ባልታወቁ ሰዎች በኃይል ተደፍሮ ንብረቱ መዘረፉን ድርጅቱ አስታውቋል።

## የቀድሞው መንግሥት የጦር ጄኔራል በሳውዲ እስር ቤት ውስጥ ሞተው ተገኙ

በወታደራዊ መንግሥት በኤርትራ በነበረው የሁለተኛ አብዮታዊ ሰራዊት የወታደራዊ ደህንነት ኃላፊ የነበሩት ብ/ጄኔራል ታደሰ በየነ በግንቦት ወር መጀመሪያ ላይ በስደት በሚገኙበት በሳውዲ አረቢያ ወህኒ ቤት ውስጥ ባልታወቀ ምክንያት ሞተው መገኘታቸው ተገለፀ። ጄኔራሉ አሥመራ በሻዕቢያ በተከበበችበት ወቅት ከጦሩ ዋና አዛዥ ከሜጀር ጄኔራል ሁሴን አህመድ ጋር በአውሮፕላን ሳውዲ አረቢያ ጅዳ ሸሽተው በስደት ይኖሩ እንደነበር ታውቋል። ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሁለቱ የጦር ጄኔራሎች መካከል እስከመደብደብ የደረሰ የሃሳብ ግጭት መፈጠሩ ጄኔራል ታደሰ በወህኒ ቤት ውስጥ እንዲታሰሩ መደረጉንና ከጥቂት ቀናት በኋላ በዚያው እንዳሉ ሞተው መገኘታቸው ተገልጿል። በአሟሟታቸው ምስጢራዊና አጠራጣሪ የሆኑ ሁኔታዎች መኖራቸውን የዘገበው የዜና ምንጭ ራሳቸውን አጥፍተዋል ማለት የማይታመን ነው ብሏል። የጄኔራሉ ሞት በስደት ላይ በሚገኙ የቀድሞ የጦር ጄኔራሎችና ተቃዋሚ የፖለቲካ መሪዎች ላይ የሽግግር መንግሥቱ በሚስጢር የሚያካሂደው አፈናና ግድያ ውጤት ሳይሆን እንደማይቀር አንዳንድ ወገኖች ይገምታሉ።

# ??? አንድ ጥያቄ አለኝ ???

## ጥቂት ስለምርጫው
(ከተለያዩ የአገር ውስጥ የግል ጋዜጦች የተጠናቀሩ)

* እንኳን ለምርጫው አደረሳችሁ። ዲሞክራሲ በአካፋ ልትዝቅ ነው!
● ወይድ! በአካፋ የሚዛቅ ቆሻሻ ነው።
*  *  *

* ሬዲዮኑም፣ ቴሌቭዥኑም ጋዜጣውም በዚህ ምርጫ ነገር እጅ እጅ ብሉን ነበር።
● አሁን ገና መቼ ለየለት። እርስ በእርሱ ሲሺሺም አዋጅ ቅብጥርሴው መመሪያው እገር እገር እስኪለን ያሰለቸን የለ!
* እንዲያ ከሆነስ ሬዲዮና ቴሌቭዥን የሚገዛ አስማሙኝ።
● ስዕል ይለጥፉበት። ሻጭ እንጂ ገዥ ጠፍቷል።
*  *  *

* ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ መረጠ ሲሉ አያፍሩም?
●ዓይናቸውን በጨው ከታጠቡ 4 ዓመት ሞላቸው እኮ!
*  *  *

* የደርግ የመጨረሻው ምሽግ ስታዲየምና ነፃ ፕሬስ መሆኑን ያውቃሉ?
● እርስዎስ ከየትኛው ምሽግ ነው ያሉት? ከደደቢት ወይስ ከኑና?
*  *  *

* አዳሜ ስትሙህ ብትውል ምርጫው ተሳክቷል። በህልም ዓለም ስለሆነ ያላችሁት እውነቱ አይገባችሁም?
● ከቅዠት ዓለም የህልሙ ሳይሻል ይቀራል?
*  *  *

* በቃ እንዲህ ከወያኔ ጋር እንደተግማማን 5 ዓመት ልንቆይ ነው?
● እስቲ ማዘጋጃ ቤት ብቅ ብለው ይንገሩአቸው።
*  *  *

* ማንም ይግዛ ማን አዳሜ ምን አስቀናው?
● ማንም ይግዛ ግን ንብ እንዴት ቤተመንግሥት ትገባለች። ባይሆን ማሩ እንጂ!
*  *  *

* ይሄ የእጼ ምኒሊክ ቤተመንግሥት ነገር አለው። መሪ አይቆይበትም። ከእንግዲህ አምስት ዓመት ኢሕአዴግን ያሰነብት ይመስላችኋል?
● ተስለናል።

* ዶሮ ብታልም ጥሬዋን ይባላል። እናንተም እንደዚያ ናችሁ!
● ታዲያ በዶሮ ምን አስቀናህ?
*  *  *

* ብፁዕ አባታችን አቡነ ጳውሎስ የምርጫውን ዲሞክራሲያዊነት አደነቁ። ደግሞ የልብሳቸው ንጣት ከሌሎች ተለየብን ምነው?
● እሳቸው እኮ ድሮም ነጭ ለባሽ ናቸው።

*  *  *
* እስቲ ማን ይሙት ምርጫው አድሏዊ ነበር ትላላችሁ?
ተክለእግዚ – ከአድዋ
● ምርጫ ስለመካሄዱ የሰማነው ከአንተና ከሬዲዮ ነው።

*  *  *
* እስቲ የዓመቱን ታላቅ ፌዝ ንገሩኝ።
● ኢሕአዴግ ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ተወዳድሮ በምርጫ አሸነፈ።

*  *  *
* ምንአለበት እውነቱን ብታወሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ በምርጫው ሲሳተፍ እያያችሁ አይደል!
● ድንቄም! ባዶ የምርጫ ጣቢያ ታቅፋችሁ ዝንባችሁን እሽ ስትሉ መዋላችሁን አልሰማን!



ደመራ
<u>የአገር ባህል ምግብ ቤት</u>

እንኳን ለ12ኛው ዓመት የሰሜን
አሜሪካ ኢትዮጵያውያኖች የግር ኳስ
ውድድር አደረሳችሁ
እያለ
ውድድሩን ምክንያት በማድረግ
ከወትሮው በተለየ መልክ ባህላዊ
በሆነ አሰ.ራር ክትፎና ዱለት
ከማዋራረጃው ንፁህ የማር ጠጅና
የዶሮ ዓይን ከመሰለው ጠላ ጋር
ሌሎች ባህላዊ ምግቦችን ጨምሮ
ባማረ ፈገግታ ልናስተናግዳችሁ
ዝግጁ ነን።

CAFE DEMERA
1271 S. La Brea Ave
Los Angeles, CA 90019
Tel (213)937-1959



ባቲ ገበያ
BATI MARKET
Variety of Ethiopian Spices and Products
የልዩ ልዩ ቅመማ ቅመምና የሥጋ መደብር

እንዲሁም

| | |
|---|---|
| የአገር የጤፍ እንጀራ | አይብ |
| የአበሻ ዳቦ | የተነጠረ ቅቤ |
| ቋንጣ | ጭኮ |

6750 Shady Brook Lane, Suit 108
Dallas, TX 75231
(214)739-3949
(we are located next to Fasica Restaurant)



Limited only by Your Imagination

"Fatuma Originals"

Dressmaking: Formals
Costumes, Original Designs
and



Expert Alterations

Fashion Consultant
By Appointment Only
FATUMA LEGESSE
404-320-1095


## ውድ የላንዳፍታ አንባብያን

መጽሄታችንን የበለጠ ለማሳደግ፣ ጥራቱን ለመጠበቅ አንባብያን ደምበኛ እንዲሆንዋት እንጋብዞታለን። ይህኛውን መጽሄት ተውሰው ከሆነ ያነበቡት የሚቀጥለውን እትም ይገዛሉ ወይም ደምበኛ ይሆኑናል ብለን እናምናለን።

መጽሄቷ ደግሞ የበለጠ ልታድግ የምትችለው ለዝግጅቷ የሚወጣውን ወጪ መሸፈን ስትችል ነው። በአገርዎ ቋንቋ በሰው አገር የምትታተመው መጽሄት ማደጓን እርሶም ይፈልጋሉ በሚል እምነት ነው።

የደምበኝነት ቅጽ ገጽ 48 ላይ ይገኛል።

ልብወለድ

# የኮለምበስ ጉዞ

## ክፍል ሶስት

# ''ይበልጣል ካፕሬቶ''

ከአብዩ

አዲስ አበባ ገና ከእንቅልፍ አልነቃችም። የሌሊቱ ጨለማ አልፎ ወገግ ብሏል። ደስ የሚል የበጋ ማለዳ ነው። የወፎች ጫጫታና የቤተክርስቲያን ደወል ይሰማል። ፀሐይዋ ገና አልወጣችም። ከማደሪያዋ ልትነሣ እየተሰናዳች መዓዛዋና ውበቷ የምታልፍበትን መንገድ ቀድሞ እንደሞላው ያህል የምሥራቁ አድማስ በማለዳ ጀንበር ውጋጋን ተሞልቶአል። ከአድማሱ ጥግ የተቆለለው የደመና ክምር ፍም እሳት ይመስላል። እየነጋ ሲሄድ አድማሱ ከዳር እስከ ዳር ወርቅ የተነጠፈበት መሰለና ከተራራው አናት ጫፍ መሬቱን እየሸረከተች ፍልቅቅ እያለች የምትወጣ ኩልል ያለች የበጋ ጀንበር ጫፏን ብቅ፣ ጨረሯን ፍንጥቅ አደረገች። በዚያ ፀጥ እርጭ ባለ የበጋ ዳመና አይን የማትቆረቁር ልስልስ ያለች የማለዳ ጀንበር አድማሱ ጥግ በተራራዎቹ አናት ላይ የተቀመጠች ትልቅ የወርቅ ምጣድ መሰለች። የተራራዎቹን አናት እየለቀቀች ከፍ ስትል የብርሃኗን ፍንጣቂ በኮረብታዎችና በገደሉ በተንጣለለው አረንጓዴ መስክ ላይ ስታሳርፍ በቀስታ ከንፈሮቿን በፍቅረኛዋ ከንፈር ላይ ያነካካች ቆንጆ ትመስላለች። እነርሱም እጃቸውን ዘርግተው ደረታቸውን ገልብጠው ሁለንተናቸውን ሰጥተው የተቀበሏት ይመስላሉ። ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል 8ኛ ፎቅ በቁጥር 283 ውስጥ የተኛ አንድ ህመምተኛ የሆስፒታሉን ፒጃማ ለብሶ ጋቢውን ተከናንቦ የመስኮቱን ጠርዝ ተደግፎ ቆሞ በዛች የማለዳ ጀንበር ላይ አይኑን ተክሎ በሃሳብ ጭልጥ ብሏል። የምትወጣውን የማለዳ ጀንበር እያደነቀ ይሁን ከራሱ ጋር እየተሟገተ ብቻ ከቆመበት ሳይነቃነቅ ተገትሯል። ከመኝታ ክፍሉ ትይዩ ማዶ እሰማዩ ጥግ ከአድማስ ባሻገር በተራራዎች አናት ላይ ቅብብ ብላ ከግርጌዋ ለሚገኝ ፍጡር ሁሉ ብርሃኗን እየፈነጠቀች ያለችዋ ጀንበር የእርሱንም ልብ በጨረሯ ጎንትላ፣ በልቡ ልብ ውስጥ የሕይወት ተስፋ፣ የመኖር ጭላንጭል የፈነጠቀችበት ይመስላል። ፍዝዝ ቅዝዝ ብሎ ይመለከታታል። በሃሳብ ርቆ ሄዷል፣ መስኮቱን እንደተደገፈ ፈዞ ቆሟል።

. . . ይህቺ ጀንበር ከስንት ሚሊዮን ዓመታት በፊት እንዲሁ እንደዛሬው ማለዳ ውብ ሆና ስትወጣ ነበር። ይኸው ዛሬም ወጣች። ነገ ምናልባትም ለሚቀጥሉት ብዙ ሺህ ሚሊዮን ዓመታት ትውልድ ታፈራርቃለች። ማንንም ልብ ሳትል ከቁም ነገር ሳትቆጥር ትወጣለች። ትጠልቃለች። ደግሞም ትወጣለች። ትጠልቃለች። ቀናት ወራትና ዓመታት እያፈራረቀች ትመላለሳለች። ስንቱ ሰው፣ የትኛው ትውልድ እሷንስ ልብ ብሏት ይሆን? የብርሃን ፍንጣቂ፣ የህይወት ጨረር የምትናኝ ይህቺን ውብ ጀንበር፣ በተራሮች መሃል ከምስራቅ አድማስ ጥግ ተፍለቅልቃ የምትወጣ ይህቺን የእንቁ አሎሎ የምትመስል ኩልል ያለች የበጋ ጀንበር ስንቱ በማለዳ ልብ ብሎ አይቷት አድንቋት ይሆን? አዲስ ቀን፣ አዲስ ጅማሬ፣ አዲስ ተስፋ ይዛ ሁሌ በማለዳው ብቅ ማለቷንስ ስንቱ ያስተውል ይሆን?

በጠና ለታመመ፣ ቀኖቹ ለተቆጠሩበት ሰው፣ በስቃይ ውጋት ሲያቃስት ለሚያድር ታማሚ ከጭንቅ ሌሊት የምትገላግል ብርቅዬ ነች። ግን! ግን! ይህቺ የዕንቁ አሎሎ የምትመስል ውብ ጀንበር ማንም ልብ ቢላት ባይላት የሕይወት ድር እንደምታደራ የሕይወት መንኮራኩር ከምሥራቅ ምዕራብ ትመላለሳለች። እንደስልጡን ባለሟል፣ የተጫነችውን ለማድረስ እንደምትቸኩል ሠረገላ የሕይወት ጠረን፣ የሕይወት ለዛ፣ የሕይወት ምግብ፣ የሕይወት ዘር እየፈነጠቀች ለሁሉም እንደዓመሉ ልታዳርስ ትፈጥናለች። የፍጡራን ስንክሳር የግዑዛን ቋንቋ እንደማይበግራት ሁሉ በብርሃንዋ ጨረር ጫፍ ገልጣ ገላልጣ ሁሉን ነክታ ተጀንና ትመላለሳለች። የብርሃንዋ ፍንጣቂ የማይደርስበት፣ የማያበራው፣ የማያሞቀው ከእይታዋ የሚያመልጥ እንደሌለ ሁሉ የእርሷን ምልልስ፣ መውጣት መጥለቋን ጠብቆ ዓይነቱ የበዛው የምድር ፍጡር በቋንቋ ሳይነጋገር እንደባሕርይው፣ እንደየመልኩ ይስተናበራል። እርሷ ከምሥራቁ አድማስ ከሰማዩ ጥግ ብቅ ስትል አራዊት ወደ ዋሻው፣ ወደ ጉድጓዱ፣ ወደ ጫካው ይሰበሰባል። የሰው ልጅ በተራው ከስርቻው ይወጣል። ጉዞዋን ጨርሳ ስትጠልቅ ጨለማ ስፍራውን ሲረከብ ደግሞ የሰው ልጅ ወደ ጎጆው ይሰበሰብና አረዊት ተራውን ይረከባል። የሰው ልጅ የዚህችን ውብ ጀንበር ውበት ሳያደንቅ፣ የብርሃን ፍንጣቂዋን፣ የምትናኘውን የሕይወት ዘር ልብ ሳይል ሳያስተውል ለነገ ለመድረስ ይንከላወሳል። ከአራዊት ጋር ፈረቃ ገብቶ ይፈራረቃል። ሰው ማለት ራሱ ክፉ አውሬ ነው። አንድ አዲስ ቀን ይዛለት የመጣችውን ይህቺን ውብ ጀንበር ልብ አለማለቱ ብቻ ሳይሆን በስግብግብነቱ የሌላው ጀንበር እንድትጠልቅ፣ እንድትጠፋ የሚታከት አውሬ! በግብዝነቱ የሌላውን ብርሃን ሆን ብሎ የሚያጨልም ክፉ አውሬ! በየቤቱ ስንት ዓይነት ሰው አለ? በእጆቹ የሰው ሕይወት ከሚቀጥፈው ነፍሰ–ገዳይ በማያንስ ሁኔታ በድርጊቱና በሃሳቡ የሌላውን ሕይወት እያጨለመ ያለ ወንጀለኛ ስንት ይሆን? . . .

ሕመምተኛው በመኝታ ክፍሉ መስኮት አጠገብ ቆሞ የምትወጣዋን የማለዳ ጀንበር ትኩር ብሎ እየተመለከተ ፍዝዝ ብሎ በሃሳብ ነጎደ። ከትንሽ አፍታ በፊት ልስልስ ያለች የማትቆረቁረዋ ውብ

ጀንበር ከፍ እያለች ሄዳ መፋጀት ጀምራለች። ዓይን ትቆረቁራለች። ከጥቁር አንበሣ ሆስፒታል ግርጌ ደረቱን ሰጥቶ የተጋደመ በሚመስለው የቸርችል ጎዳና ላይ ሰውና ተሽከርካሪ ውር ውር ማለት ጀምሯል። በሆስፒታሉ ግቢ ውስጥ የሰው ትርምስና ድምፅ ይሰማዋል። በደንብ ነግቷል። በመስታወቱ ውስጥ የምትገባዋ ፀሐይ አቃጠለችው። ሃሳቡ ደግሞ በአንድ ስፍራ ደርሶ ተቸንክሮ አስቸገረው።

"ውቢት ፍፍቴ" – ውብት መንገሻ፣ ለምለም ኩርኩር፣ ደጉ፣ ደብሪቱ፣ መልኪ አጎናፍር! በአይነ ህሊናው በመካከላቸው ተገትሮ ቆመ። የሆነው ሁሉ እንደሚያስፈራ የቁም ቅዠት አንድ በአንድ ተደረደሩበት። አንዳች ነገር አቃጠለው። አንገበገበው። የምትሞቀዋ ፀሐይ ግን አልነበረችም። በራሱ ግብዝነትና ጭንቀት ምንም ባላደረጉ ንፁህ ሰዎች ላይ ያደረገው ድርጊት የልቡን ቁስል ሸነቆጠው። "የሌላውን የሕይወት ተስፋ አጨለምክ" ሲል አንዳች ነገር በአዕምሮው ጓዳ አቃጨለበት። የመኝታ ክፍሉ በር ሲከፈት ተሰማውና ከሄደበት ሃሳብ ተመልሶ ወደ በሩ ዘወር አለ። ተረኛዋ ነርስ ነበረች።

"አቶ እንደሻው ከአልጋዎ ላይ መውረድ የለብዎትም። ለረጅም ጊዜ መቆምና በሃሳብ መመሰጥ ህመምዎን ሊያባብስብዎት ይችላል።" አለች ነርሷ።

"ምንም አልል አሁን በጎ ነኝ።" አለ ህመምተኛው

"የሐኪሙ ትዕዛዝ መከበር አለበት። ህመምዎ የአዕምሮ ዕርጋታና ዕረፍት የሚያስፈልገው ነው።" አለች ነርሷ ፈርጠም ብላ።

"መተኛቱ ሰለቸኝ። ደግሞም እንቅልፍ አልወስድህ ብሎኝ ተቸግሬ አደርኩ።"

"የእንቅልፍ ክኒን ታዞሎት የለም። ለምን አልወሰዱም?"

"እሺ እወስዳለሁ።"

"እወስዳለሁ ሳይሆን መውሰድ ነበረብዎት።" ብላ የረሳችው ዕቃ ትዝ እንዳላት ያህል ከክፍሉ ፈጥና ወጣች። ብዙም ሳትቆይ በስጦታ ወረቀት የተጠቀለለ አበባና ኤንቬሎፕ ይዛ ተመለሰች።

"ይህን አበባና ኤንቬሎፕ አንድ ሰው በር ላይ ለዘበኞች ሰጥቶ ነርሶች ቢሮ ተረስቶ ቆየ?" አለች አበባውን ከአልጋው ራስጌ ኮሜዲኖ ላይ እያስቀመጠች።

"ኧረ ተይ የእኔ አይመስለኝም!"

"እንደሻው ሳህሌ ማለት እርስዎ አይደሉም እንዴ?"

"እሱማ እኔው ነኝ።"

"ነርሶች ቢሮ ተረስቶ አበባው ጠውልጓል። ቢሆንም እኔ አድርሻለሁ" ብላ ከአልጋው ላይ እንዳይወርድ አስጠንቅቃው ከክፍሉ ወጣች። እንደሻው ሳህሌ ከተኛበት ሆኖ የአበባ ስጦታ ተሸክመው ሊመጡ የሚችሉትን ወዳጆቹን አሰላሰለ። "በችግርና በደህና ቀን መጠያየቅ ለየቅል ነው" አለ ለራሱ። የደስታ ስሜት ወረረው። ከአበባው ጋር ያለውን ኤንቬሎፕ ከፍቶ ተመለከተው። አንድ ካርድና በእጅ የተፃፈ ደብዳቤ አለበት። የጥርጣሬና የደስታ ስሜት ተቀላቀሉበት። በመጠራጠር ኤንቬሎፑን ልብ ብሎ ተመለከተው።

"ለአቶ እንደሻው ሳህሌ" የሚል ጽሁፍ በትልቁ ተጽፎበታል። ካርዱን ኮሜዲኖው ላይ ወረወረውና ደብዳቤውን ለማንበብ ትራሱን አመቻችቶ ተደግፎ ተቀመጠ። በቀስታ በጥሞና አነበበው። እንዲህ ይላል:

–ለአቶ እንደሻው ሳህሌ!

እግዚአብሔር ጨርሶ ይማርህ። ድነህ ለቤትህ እንድትበቃ ፍጹም ምኞቴ ነው። ከዚህ ለሚበልጥ ሰላምታና መልካም ምኞት ጊዜ የለኝም። በግንባር ላገኝህ ፈቃዴ ነበር። ብዙ ተመላለስኩ። አልሆነልኝም። ራሱን የሳተ ህመምተኛ በሚገባ ከመዳኑ በፊት ለመጠየቅ አለመቻሉ ሲነገረኝ በልቤ ያለው ከነጭራሹ ከሚቀር ብዬ ይህን ማስታወሻ ልተውልህ ወደድኩ። ለምን እንደምጽፍልህ አላውቅም። ምን ያስፈልጋል? አይገባኝም። ግን የሕሊናዬን ሸክም አንድ ሰው ቢያውቀው ያም ሰው አንተ ብትሆን ትንሽ ተንፈስ የሚልልኝ ይመስለኛል። ስለ ማንነቴ ብዙ አትጨነቅ በማንነቴ አታውቀኝም። ከነመፈጠሬም ከነመኖሬም አታውቅም። እኔም አንተም ያላሰብነው አጋጣሚ አቀራኝቶናል። ከእንግዲህ በኋላም ብታውቀኝ የምትረዳኝ ነገር አይኖረኝም። ልታውቀኝም አትድከም። አታውቀኝም። ምስኪን ይበልጣልን አታውቀውም። የምታውቀውም ዓይነት አይደለም።

ይበልጣል አባመስጠት ቸር ነው። በካዛንቺስ፣ በአራት ኪሎ፣ በዶሮ ማነቂያ፣ የሚገኙ መደበኛ ጠጪዎች፣ አሻሻጭ ሴቶች የሚያውቁት ዝነኛ ሰካራም! ገንዘብ ኪሱ ካለ መንገደኛውን እንኳ ሳይቀር ቢጋብዝ ደስታው ነው። ደመወዙን ተቀብሎ እስከሳምንት ስራ አይገባም። ደመወዙን በኪሱ አጭቆ ሲጋብዝ ሲጋበዝ፣ የጠጣበትን የዱቤ ሂሳብ ሲያወራርድ ሰንብቶ የተቀበላትን የወር ደመወዙን ሰጥ አድርጎ አመድ የተነፋበት መስሎ እያዛጋ ወደቢሮው ብቅ ይላል። ጥሎበት ከመጠጥ ሁሉ ቬርሙጥ ይወዳል። የተማረ ሰው መጠጥ ይለዋል። ጂን ነፍሱ ነው። ባለጌ የሚያደርግ የባለጌ መጠጥ ይለዋል። ከቬርሙጥ ሞቅታ፣ ከጂን ስካር በኋላ ከእንስት ፆታ ጋር የሚያደርገው ልፊያና ድሪያ የተለየ ደስታ ይሰጠዋል። ያስፈነጥዘዋል። ሴትን ልጅ ባወቃት ቅጽበት አልጋው ላይ አድርሶ ሴትነቷን ካልሞከረው ወንድነት አይሰማውም። ነገልቦ ካላየ የሴትን ልጅ

ቤትነት አያምንም' ይሉታል ጓደኞቹ። የሴት ነገር የበሽታ ያህል ያመዋል። ለአንዲት ሌሊት ብቻውን ማደር አይሆንለትም። የሴት ልጅ ገላ የሴት ልጅ ጠረን አይጣ እንጂ ስለቁንጅና፣ ስለውበት፣ ስለፀባይ የሚያውቀው ነገር የለውም። ዝቃጭ ኑሮ፣ ከዝቃጭም ዝቃጭ አተላ ሲገፋ የኖረ መላ-ቢስ ወንደላጤ ነው። አንድ ቀን እንደልማዱ ደመወዙን ተቀብሎ አዳዲስ የብር ኖቶችን በኪሱ ሞልቶ ወደ እሪ በከንቱ ብቅ አለ። የሚወደውን ቬርሙጥ ደጋግሞ ተጎነጨ። በአናቱ ደረቁን ጂን ከለበሰበት። ሞቅ አለው የሴት ገላ መዳሰስ፣ መንካት አሰኘው። ዳሩ የሁሉም ሰካራም ወንድ ባህርይ እንዲህ አይደል?

"ነይ አንቺ?" አላት አንዷን

"ምነው?" አለች እየተሻሸችው። ከተቀመጠበት ባለሶስት እግር የባንኮኒ ወንበር ላይ እንደተቀመጠ ወደራሱ አስጠጋት። የወሲብ ረሃብና ቬርሙጥ ባጋላቸው እጆቹ ዳበሳት። ውብ ነች። ባትሆንም መሰለችው። በሳቅ እየተፍነከነከች በደረቱ ላይ ጥፍ አለችበት። የረሃብተኛ ጉሮሮው አሳበቀበት። እቅፍ አድርጎ ወደ ራሱ አስጠጋት። ተንፈራጦ ከተቀመጠበት ወንበር ላይ ሳይወርድ በእግሮቹ መሃል አስጠጋትና አቀፋት። በጆሮዋ አንድ ነገር አንሾካሾከላት። ድው ድው የሚል የልቡ ምት ተሰምቷታል። የሚፋጅ ትኩሳቱ እንዳች ነገር ነግሯታል። ከት ከት ብላ ሳቀችበት። ሳቅ አይደለም። አሽኮለሌ ነው። - ሴቶች የልባቸውን ሲነግሯቸው የሚስቁት ዓይነት ሳቅ! ወንድ ልጅ ለሴትነታቸው መረታቱን መሸነፉን ሲያውቁ፤ ኮርማውን ቀንዱን ይዘው ማንበርከካቸውን፣ መረታቱን፣ መሸነፉን ሲያውቁ የሚስቁት የአሸናፊነት ሳቅ ዓይነት! አሽኮሌሌ! . . . "አንተ ስድ ባለጌ!" አለችው በመሽኮርመም። እንደሲካካ ዶሮ እያስካካች! ደረቱ ላይ ተለጥፋ ወጠጤ ፍየል የምታስመስለውን የአገጩን ጉትዬ ጢም አሻሸችለት። ታከከችው። ይበልጣል ደጋግሞ ከቬርሙጡ ተጎነጨ። ከሲጋራው ሳብ ሳብ አደረገ። ወንድነት ተሰማው።

"ለመሆኑ አልጋህ ተነጥፏል?" አለችው በማሾፍ ዓይነት። ደጋግማ ወደ ቤቱ መሄዷን ልትነግረው የፈለገች ይመስል

"አብረን እናነጥፈዋለን" "ምን በወጣኝ! ሂድ አልጋህን አንጥፍና አልጋህ ስር የወረወርከውን ቆሻሻ ካልሲ ካለ አጥበህ፣ ቤትህን ጠርገህ ቁጭ ብለህ መጣች ቀረች እያልክ ጠብቀኝ" አለችው። መቀለዷ ነበር። ይበልጣል ጥሎአት መሄድ አይቻለውም። እርሷም ስታብል ነው። ልሂድም ቢል ብቻውን አትለቀውም። እንኳን አልጋ አንጥፎ ቤቱን ጠራርጎ ሊጠብቃት ቀርቶ ከዚህ እንደወጣ የሚያገኛትን የእርሷ ቢጤዎች የመጀመሪያዋን እንደማያልፍ ታውቀዋለች። "ሂሳብሽን አስረክቢና እንሂድ"

እንዴ ምን ነካህ? ሰዓቱ እኮ ገና ሶስት ሰዓት ነው!" "ሂሳብሽን እኔ እሞላለሁ አስረክቢና እንሂድ" አላት በተቻኮለ ስሜት። እየተሽኮረመመች ጢሙን አሻሽታ ሂሳብ ለማስረከብ ወደ ውስጥ ገባች። ይበልጣል ደብል ጂን አስቀዳና ተመቻችቶ ተቀመጠ። ለወራት የሚቀመጥ መሰለው።መኝታ ክፍሉ፣ አልጋው ናፈቀችው። ከጂኑ ደጋግሞ ተጎነጨለት። ሰዓቱን ተመለከተ። ሶስት ሰዓት ከአምስት ደቂቃ ይላል። አምስት ደቂቃ ብቻ! ሰዓቱ የተንቀረፈፈበት መሰለው፣ አሁን መጠጥ አላሰኘውም። ቬርሙጥም ጂኑም በቅቶታል። የናፈቀው የሴት ገላ የሴት ጠረን ነው። ቡና ቤቱ ውስጥ ያለውን ሰው ተመለከተ። ሁሉም በየራሱ ጨዋታ ተመስጧል። እበሩ አካባቢ ቆሎ የያዘች አጠር ያለች ልጅ በየጠረጴዛው ላይ እየዞረች እየሰፈረች ትሸጣለች። መጀመሪያ እንደነገሩ አያት። ቆሎ ገዝቶ በእርሱ እየተከዘ መጠበቅ አሰኘውና ልብ ብሎ ተመለከታት። የምትታየው ከጀርባዋ በኩል ነው። በብልግና ዓይኑ ከላይ እስከታች አንዴ አነበባት። ደግሞ እንደገና አብጠርጥሮ ፈተሻት። ቀጭን ወገብ ሰፋ ያለ ዳሌ ድቡልቡል እግር የተጎነጎነ ዞማ ፀጉር! ሳያስበው ልቡ ትርክክ አለበት። ደቂቃዎች የረዘሙበት ወንድነቱ ተግ አለበት።

"ባለቆሎ" ሲል ተጣራ።

"ቆሎ አይደለም። ሎሚ ነው የያዝኩት" አለች ድንቡሽቡሽ ያለች አንዲት ኮረዳ ወደ እርሱ እየመጣች። የምታምር ድንቡሽ ያለች ፉንጋ ልጅ ናት። ይበልጣል በግምት ዓይን ተመለከታት። ትንሽ ትምሰል እንጂ ትንሽ አልነበረችም። ለሴትነት ወግ እንግዳ አለመሆኗን አይነ-ውኃዋ ነገረው።

"ስንት ነው?" አላት አንድ ሎሚ አንስቶ።

"አንዱ አስር ሳንቲም ሁለቱ አስራ አምስት" አለችው ፍርጥም ብላ።

"ሁሉንም ብገዛሽ ስንት ይሆናል?" አላት ጉዳዩ ከሎሚው ሳይሆን ከእርሷ መሆኑን ሁለመናው እያሳበቀበት።

"እንዴ! ሁሉም ምን ያደርግሎዎታል?" አለች በመሽኮርመም ሳቅ ብላ። ስትስቅ ደግሞ አማረችው። ሳቋ የደረሰች ኮረዳ ቅላጼ አለው። ለሴትነት ወግ መድረሷን ከአይነ-ውኃዋ አነበበ። ሳቋ አረጋገጠለት።

"ለእቤት ነው የምፈልገው። እቤት ካደረስሽልኝ ሁሉንም እገዛሻለሁ።" አላት በሃሳቡ ይህቺን ድንቡሼ ኮረዳ አልጋው ላይ እንዴት እንደሚያደርሳት እያሰላ።

"እቤት ድረስ እንኳ እፈራለሁ። ሰፈር ድረስ ግን ልወስድልዎት እችላለሁ።" አለች አሁንም እንደቅድሙ እየተሽኮረመመች።

"ምን ትፈሪያለሽ?"

"እንዴ! ለምን አልፈራም?"

"እኮ ምን ትፈሪያለሽ?"

"የማላውቀው ሰው ቤት መሄድ እንዴት አልፈራም?"

"ይኸው አሁን አወቅሽኝ"

"አሁን ባውቅዎትስ?"

"አትፈሪኝማ!"

"ብቻዬን ወንድ ቤት መሄድ እፈራለሁ" አለች። እየተሽኮረመመችና እየተቅለሰለሰች። መቅለስለሷና መሽኮርመሟ የነገር ነው። የሴትነት ነገር!!! . . . ሴቶች የልባቸውን የሚናገሩበት ወንዶችን ጋራ አዙረው አጥር አዘልለው ከእጃቸው የሚያስገቡበት ዓይነት መሽኮርመም። ይበልጣል ወንዱ – ወንድነቱ ተግ አለበት። እንኳን ይህቺንና የዝንብ ጠንጋራ ያውቃል። ከደቃቂዎች በፊት የምሽት ወዳጁን እንዳልተነጋገረ ያህል ከመቀመጫው ዱብ ብሎ ወረደና ሃያ ብር ባንኮኒው ላይ ወርውሮ መልስም ሳይጠብቅ ባለሎሚዋን ልጅ ይዞ ወጣ።

በዋናው አስፋልት ትንሽ ከሄዱ በኋላ በኮረኮንቹ ታጥፈው ወደ ጉራንጉር ሰፈር ውስጥ ገቡ።

"እዚህ ግቢ ነው ቤቴ" አላት "እሺ! ይውሰዱትና ገልብጠው ዕቃውን ይስጡኝ እዚህ እጠብቅዎታለሁ።" አለች በመሽኮርመም።

"ለምን አትገቢም?"

"እፈራለሁ"

"ምን ያስፈራሻል? ይልቅስ በእንቅብ ሙሉ ሎሚ ተሸክሜ ስገባ የሰው መሳቂያ አታድርጊኝ። አድርሽልኝና ተመለሺ" ብሎ ጥፍንግ አድርጎ ጎተታት።

"ግን አልቆይም"

"ልቆይ ብትይም የሚያቆይሽ የለም" ወና ወና የምትል አንዲት ትንሽ ክፍል ቤት ከፍተው ገቡ። አልጋው አልተነጠፈም። ዕቃ የለባትም። ያለውም ዝርክርክ ያለ ነው። የመላ–ቢስ ወንደላጤ ክፍል መሆኗ ያስታውቃል።

"በይ አረፍ በይ"

"አልቀመጥም ። እቤት ይቆጡኛል። ይልቅስ ሎሚውን ገልብጠው ገንዘቡንና ዕቃውን ይስጡኝ"

"አታስቸግሪ ትንሽ ቁጭ በይ!"

"እንዴ! ምን አስቸገርኩ" አለችና እጥጉ ላይ ካለው ሳጥን ላይ ተቀመጠች።

ይበልጣልም ከፊት ለፊት አልጋው ጠርዝ ቁጢጥ አለ። ለትንሽ አፍታ ተፋጠው በዝምታ ቆዩ። ምን እንደሚያደርጋት ግራ ተጋባ። ድመት እንደያዘቻት ወፍ ብጥቅጥቅ፣ ቢያደርጋት ወደደ። ዘለህ ተከመርባት፣ እነቃት እነቃት አሰኘው። ብትጮህስ ሲል ትንሽ አሰበና ፍርሃት ቢጤ ተሰማው። የምትጮህ ብትሆን እዚህ ድረስ ምን ያመጣታል? ሲል ለራሱ መለሰ። ትኩር ብሎ አያት። ኩርፍፍ ብላ ጥግ ይዛ ተቀምጣለች። ትንሽዬ ድንጉጥ ፍጡር። የሚናገረው ጠፋበት። መልሶ ትኩር ብሎ አያት። እንደዚያው ኩርፍፍ ብላ ድምጿን አጥፍታ የልቧን ምትየምታዳምጥ መሰለችው። ከተቀመጠችበት ፍንጥር ብላ ተነስታ ብር ብላ የምትሄድበት መስሎት ጨነቀው። ተንቆራጠጠ። ትኩር ብሎ ተመለከታት። አትንቀሳቀስም። አንገቷን አቀርቅራ ተሽኮርምማ ከጥጉ ላይ እንደተወሸቀች ናት። ከዚህ በላይ ምን ታድርግ? በሴት ልጅ ቋንቋ ተናግራለች። ለራሱ ነገረው። ደግሞ ልብ ብሎ ሲያያት ትልቅ መስላ ታየችው አንገቷን አሸዋ ውስጥ ቀብራ የተደበቀች ሰጎን መሰለችው። . . . የቀረውን አካሏን ጭልል ባለው አሸዋ ላይ አንከርፋ አንገቷን ብቻ አሸዋ ውስጥ ከቀበረች ሰጎን ዘንድ ደርሶ የሚያመነታ አንበሣ እንደሆነ ተሰማው። ሊይዛት ሲያሳድዳት ቆይቶ አንገቷን አሸዋ ውስጥ ቀብራ የቆየችው ሰጎን ዘንድ ደርሶ የሚያመነታ አንበሣ! ወይኔ ይበልጣል!! አፋን ከፍቶ አፏሸከ። ሆዱን ሞረሞረው። የወሲብ ረሃብ ጓጎጠው። ጥርሱን ነክሶ ዓይኑን ለአፍታ ጨፈነና ከተቀመጠበት ተስፈንጥሮ በሁለት እጆቹ እፍስ አደረጋት። ጥልጥል አድርጎ ተሸከማት። አልከበደችውም። ከእቅፉም አልሞላችለትም። እየተንገዳገደ ተጣድፎ ወስዶ ከአልጋው ላይ ዝርግፍ አደረጋት። ፋታ ሳይሰጣት በተራበ አፉ ጎረሳት። የወሲብ ትኩሳት ባጋሉት ክንዶቹ ፍጥርቅ እስከትል ጠፍንጎ ያዛት። አልታገለችውም። እንደፈራውም አልጮኸችም። አንገቱ ላይ ተጠምጥማ በትኩሳቱ ቀለጠች። ዝርግትግት ብላ በአንበሳው ክንድ ላይ ተንጋለለች። በሰቀቀን ስቃይ እቃሰተች። ጠረኗ አወደው። የሽቶ ወይም የቅባት አልነበረም። ሎሚ ሎሚ ሸተተችው። ትንፋሿ እንደጥቅምት ንፋስ ሽውታ ከሩቅ ይጣራል። ልትፈነዳ እንደደረሰች እንቡጥ ጽጌረዳ ውብ ሆነችበት። እንደምንጭ ውኃ ኩልል ጥርት ያለች የልጃገረድ ጠረን፤ የደረሰች ዓይነ–ግቡ ኮረዳ ወዘና አፋን ሞላው። ደጋግሞ ምራቁን ዋጠ። በስሜት ሲቃ ተፍነከነከ። አፍንጫውን አንገቷ ስር ወሽቆ እንደውሻ አነፈነፈ። ተስገብግቦ ሊውጣት ታገለ። አልቻለም። ቅርጥፍጥፍ አድርጎ በላት። ጣፈጠችው። ምኗም ሳይቀረው አጣጣማት። ኩርፍፍ ያለች ሰጎን ሳትሆን ኩርሽም! ኩርሽም! ኩርሽም! እንደምትል የጥጃ ስጋ ጣመችው። ካጥሬቶ! ካጥሬቶ! ካጥሬቶ! . . . ሲል በእርካታ ጮኸ። አልሰማችውም። የለችም። ርቃ ሄዳለች። ትንሽ ቆይታ እንደፈዘዘች በድካም መንፈስ እያቃተተች የሞት ሞቷን ዓይኗን ትንሽ ገለጥ አድርጋ አየችው። በስስት ዓይን ደግማ አየችው። በሀዘኔታም አይደለም። በትዝብትም አልነበረም። ደርሳ የተመለሰችበትን ሩቅ አገር በእርሱ ውስጥ አሰበችው። ሩቅ አገር! ሩቅ አገር! . . . ትንሽዬ ድንጉጥ ፍጡር!

ይበልጣል ይህን ዓይነቱን ሲሳይ አያውቀውም። በቬርሙጥ ስካር የሚጎትታቸውን ሴቶች፣ የሲጋራ፣ የመጠጥ፣ የሽቶ፣ የፓውደር የተቀላቀለ ጠረን እንጂ! ይህቺን ባለሎሚ ወደዳት። ሊለያት አልፈለገም። እርሷም ለመደች። ተመላለሰች። ማታ ማታ ባንኮኒ ላይ ተቀሽሮ ቬርሙጥና ጂን መጨለጡን ትቶ ይህቺን ኮረዳ መጠበቅ አብሮአት ማምሸት

እርሷን መሸኘት ማድረስ ሆነ። ለአንድ ቀን ሳያያት ከዋለ ናፍቆት ይገድለዋል። አስቦት የማያውቀውን ትዳር ሁሉ ማሰብ ጀመረ። ከብዙ ወራት በኋላ አንድ ቀን:-

"ካፕሬቶ ማለት ምን ማለት ነው? ሁሌ እጠይቅሃለሁ እያልኩ" አለችው በጨዋታቸው መሃል ከንፈሮቿን ጣል አድርጋ ዓይኖቿን እያቅለሰለሰች።

"ካፕሬቶ? ካፕሬቶ ማለት? . . . አንቺ ነሻ! የእኔ ካፕሬቶ!"

"እኔ ካፕሬቶ አይደለሁም"

"ታዲያ ምንድነሽ?"

"እንዴ! ማናዬ ነኛ። ማንአለብሽ ትርፌ። አባቴ ያወጣልኝን ስም ትቼ ደግሞ ማን ልባል ነው ልጄ!"

"ለእኔ ግን ካፕሬቶ ነሽ!"

"ውሸታም"

"ውሸቴን አይደለም። ለእኔ ካፕሬቶ ነሽ። የአባቴ ስም ቀርቶ ጓደኞቼ "ይበልጣል ካፕሬቶ" ብለው እንደሚጠሩኝ አልነገርኩሽም? ምንም አልከፋኝ። አንቺ የእኔ ካፕሬቶ ነሽ።" አለና ትክ ብሎ አያት። "አይደለሽም?" አላት ፍጥጥ ብሎ እያያት

"ኧረ! የማነው ይኼ? እኔ ማንአለብሽ ትርፌ ነኝ። የምን ካፕሬቶ ነው? ካፕሬቶ ስም ነው እንዴ?"

"ካፕሬቶ ማለት እኮ! . . . ይሽውልሽ . . . ምን መሰለሽ? በቃ ጥሩ ነገር ነው። አንቺ ግን አልወደድሽውም?"

"ያስጠላኛል። ሁሌ እነግርሃለሁ እያልኩ አስብና . . "

"ማን ብልሽ ደስ ይልሻል?"

"በስሜ ጥራኝ!"

"ካላቆላመጥኩሽ ደግሞ ቅር ይለኛል።"

"ቅር ከሚልህ ማናዬ! ማኒ! በለኝ"

"እንደርሱ ብጠራሽ ደስ ይልሻል?"

"እዎ"

"ሌላ ሰው የለም እንደዚያ የሚጠራሽ?"

"እንዴት ዓይነት ጥያቄ ነው የምትጠይቀኝ?"

"ማለቴ ሌላ ሰው እንደዚያ የሚያቆላምጥሽ የለም ወይ?"

"ኧረ! ይሄ የማነው ሞዛዛ?"

"ሞዛዛነት አይደለም። አንቺን የምጠራበት የግሌን የቁልምጫ ስም ስለምፈልግ ነው።"

"እንግዲህ አትድረቅ! ሞዛዛ!"

"እሺ ማነው? ማኒ ማናዬ ብሎ የሚጠራሽ? እኔ ብቻ ከሆንኩ ነው እንደዚያ የምጠራሽ!"

"ሰው ይጠፋል እንዴ ታዲያ?"

"ማነው እሱ?"

"ኧረ ይሄ! ምነው ተሚዘዝክ ዛሬ ቀን"

"ባውቀው ምናለበት? ሞዛዛነት ነው? እሺ አንቺ የእኔ ካፕሬቶ አይደለሽም?" በጥያቄ ትክ ብሎ አያት። የእውነት ካፕሬቶ ናት አለ በልቡ። ኩርሽም ኩርሽም የምትደረግ ካፕሬቶ ሲል አሰበ። ድንገት አንድ ሃሳብ ትዝ አለው። . . . ይህቺን ቀበጥ ጽጌረዳ መጀመሪያ የቀጠፈ ማን ይሆን? ማኖ አስነክቶ ማኒ ያላት ጎበዝ ማንኝ ይል ይሆን? ሳያስበው በልቡ ውስጥ የቅናት እሳት ቦግ አለበት። የተለመደ የወንዶች ባሕርይ ነው አይደል? ከሴት ልጅ የሚፈልጉትን ሲያገኙ ያላትን ሳይሆን የሚጎድላትን መመልከት መጀመር!

"እሺ ንገሪኛ!"

"ሌላ የምታወራው ጨዋታ የለህም? በቃ ይህን አርዕስት እንተወው።"

"ምንአለበት ብትነግሪኝ? ያለፈ ነገር እኮ ነው። ምን ክፋት አለው? እኔና አንቺ ስላለፈ ነገር ማውራት አንችልም?"

"ያለፈ ስለሆነ አይደለም። በሕይወት ስለሌለ ሰው ማውራት ስለማልወድ ነው።"

"ሞቷል ማለት ነው?" "ምናለ ብትተወው ይህን አርዕስት? በቃ ካልሆነ ልሂድልህ።" አለች ከንፈሯን ጣል አድርጋ እየተነሳች። አይኖቿ እንባ ቋጥረዋል። እንባዋን ሲያይ ቅናቱ ባሰበት።

"ከእኔ ይበልጥ ትወጅዋለሽ?"

"አላውቅልህም! በቃ ተወኝ አልኩህ። ተወኝ!"

"ይሽውልሽ! የግላችን በሆነ ነገር ላይ በግልጽ መነጋገር መቻል ክፋት የለውም። ለወደፊትም ቢሆን ግልጽ መሆንን መልመድ አለብሽ። ብዙ ጊዜ ነግሬሻለሁ። ያሳደገን ህብረተሰብ በነፃነት ስላላሳደገን ግልጽ መሆን ያቅተናል። እኔ የራሴን ስንት ነገር አውርቼልሽ አላውቅም? ደርሶ ዛሬ ምን አዲስ ያደርግሻል?" አላት። እቅፍ አድርጎ እያባበለ።

"ለእርሱ አይደለም!" አለች እንባዋን እየጠራረገችና እንደህፃን ልጅ ሳግ እየተናነቃት

"ታዲያ ምንድነው?"

"የሞተ ሰው ስም ማንሳት . . . " አንጠልጥላ ተወችው።

"መቼ ነው የሞተው?"

"ከሳምንት በፊት"

"እንዲህ በቅርቡ?"

"እዎ!"

"ማን ይባላል?"

"መ-ል-ኬ" አለች ስሙን መጥራት የፈራች ይመስል ፊደሎቹን እየቆጠረች።

"መልኬ! መልኬ! መልኬ! ይህን ስም አውቀዋለሁ ልበል? መልኬ ማነው የአባቱ ስም?"

"መልኬ አጎናፍር"

"በምን አወቅሽው አንቺ?"

"ካስጠጋችኝ ሴትዮ ዘንድ ተከራችም ገብቶ ነበር።"

"ያስጠጋችኝሽ ሴትዮ አሮጊት ነች አላልሽኝም? አሮጊት ዘንድ ተከራችም ይገባል እንዴ?"

"በፊት እንደወዳጅነት ነበር። በኋላ ግን ደባል ተከራይ መስሎ ጠቅልሎ ገባ።"

"እዚያው ሆኖ ነው ከአንቺም ጋር ሌላ እንትን የጀመረው?" አላት ነገሩ እየከነከነው። መልስ አልሰጠችውም። ዝም አለችው። "እንዴት

ዓይነት ክፉው ነው እባካችሁ? ከአንድ ቤት ሁለት ሰው?" አለ በቅሬታ ስሜት።

"ኧረ! እሱስ ክፉ አልነበረም። ራስዋ ነች እልህ ያስገባችው። አስጠጋችኝ እንጂ ደግሞ ዝምድና የለንም።"

"እንዴት እልህ?"

"ለምን አየሃት? ለምን ተናገርካት? እያለች ስትጨቀጭቀው በቃ እልህ አስያዘችው"

"በኋላ እንዴት ሆናችሁ?"

"አንድ ቀን የእርሱን ልብሶች ሳጥብለት መጣችብኝና ብሽቅጥቅጥ አድርጋ ሰደበችው። ልብሱን መሬት ላይ ዘርግፋ ሳፋውን ወሰደችና እኔንም ልትመታኝ ስትል አመለጥኳት። በፊትም ሰበብ ነበር የሚፈልገው ዕቃውን እንኳ ሳይወስድ በዚያው እንደወጣ ቀረ።"

"የምን ሰበብ?"

"ለእንቺ ብዬ ነው እንጂ የዚህች አሮጊት ገንፎ ሰለቸኝ። ሆዴን አቆዘረኝ ይለኝ ነበር። እንደወጣ ሳይመለስ ለአፈር በቃ።"

"ከአሮጊቷ ተጣልቶ እንደወጣ ነው የሞተው?"

"የለም! ካዛንቺስ "ውቢት ፍፍቴ" የሚባል ቡና ቤት ያላት ሴትዮ ጋ ገብቶ ነበር። ደህና አምሮበት እያለ ድንገት ሞተ።

"ከእንቺ ጋርስ ትገናኙ ነበር?"

"ልጆች ቆሎዬን እየደፉ አስቸገሩኝ ስለው ሎሚ ገዝተሽ ብትሸጪ ይሻላል ብሎ ገንዘብ የሰጠኝ እርሱ ነው። ከከለርሽ ጋር ይሄዳል የምትለኝን ቀዩን ቀሚስም እርሱ ነው የገዛልኝ። እ . . . "

"ማን አልሽኝ ስሙን?" አላት አቋረጣትና።

"መልኬ! መልኬ አጎናፍር"

"ስሙን የሰማሁት ይመስለኛል። የት ነው የተቀበረው?"

"ጊዮርጊስ"

"እዚሁ ቅርባችን ጊዮርጊስ? ሳልሰማው አልቀርም። እማ ዞቢያውነሽ የነገረችኝ መስሎኛል?"

"ማናቸው እማ ዞቢያውነሽ?"

"እዚህ እኛ ሠፈር ያሉ አስለቃሽ ሴትዮ ናቸው። ምን የመሰለ ጎበዝ ሞቶ ሙሾ ተቀባይ ጠፍቶ ብቻዬን መልኬ! መልኬ! ስል ዋልኩ ብለው ያወሩልኝ መስሎኛል።"

"እኛ ከተቀበረ ነው የደረስነው።" አለችው በእንባ የሞሉ ዓይኖቿን እየጠራረገች።

እርሱ ግን የሰማው ነገር ልቡን እንደቁስል ክፉኛ ጠዘጠዘው። የዚያች ዕለት ምሽት ለወትሮው ከእርሷ ጋር እንደሚሆነው መሆን አቃተው። ሸኝቷት ከተመለሰ በኋላ የሟቹን ቁመናና ካፖርቶ ያወራችለትን እያውጠነጠነ አሰላሰለ። ሟቹ ኮተቱን ጠቅልሎ የተከረቸመው ካስጠጋት ሴትዮ ዘንድ ሳይሆን ከእርሱው 'ካፖርቶ' ዘንድ መሆኑን ልቡ ሲያውቀው ቅናት እንገበገበው። የእሟሟቱ ድንገተኛነት ደግሞ እንዳመረቀዘ የቆላ ቁስል አሳመመው። . . . በምን ይሆን የሞተው? ምን በሽታ ይኖርበት ይሆን? ሲል አሰበ። በሕሊናው ጓዳ ውስጥ የስጋት ፍንጣቂ ብልጭ አለችበት። እየተጣደፈ ወጥቶ ወደ እማ ዞቢያውነሽ ቤት አመራ። እማ ዞቢያውነሽ ጥጥ እየፈተሉ ነበር። ሰላምታ ሰጥቶአቸው ተቀመጠ።

"ካቲካላ – አረቂ ልስጥህ?" አሉት።

"የለም አልጠጣም።"

"ታዲያ ጠላ የለኝም። ምን ትጠጣለህ?"

"መጠጥ እኮ ትቻለሁ ብዬ ነግሬሻለሁ እማ ዞቢያው!"

"ያቺን ባለሎሚይቱን ካገኘህ ወዲህ ሰው ሆነሃል በል። የዋዛ ድባኖ አይደለችም። ያን ትንባሆና መጠጥ እርግፍ አድርጋ ማስጣሏ! ከሆነስ ሆነና ታገባታለህ ወይስ እንዲሁ ስታመላልሳት ልትከርም ነው?"

"ምን እኮ ላግባትስ ብል የኑሮ ውድነቱን ታይዋለሽ?"

"ምን ኑሮ ውድነት ቢሆን ለእርሷና ለራስህ አታንስ? መቼም በግርግም አይበላ!"

"ቢሆንም!"

"ወይ እያ ገላው! በግላጭ አግኝተህ ሰፍረህባታላ። እጅህ እስከትገባ ሱሪህን እንኳ ሽጥና አምጣ ቢሉህ ቅር የማይልህ የልብህን አድርሰህ፣ የሰው ልጃገረድ አጓጉል አድርገህ በኑሮ ውድነት ታመካኛለህ። ምን ታደርጉ የዛሬ ወንዶች! አይፈረድባችሁም። ሴቱ ልብ የለው! ወይኔ ዞቢያው መርኔ! ድሮ በእኛ ጊዜ እርሷን የመሰለች ቆንጆ በስንት ደጅ ጥናት ነበር የምትገኝ። የዛሬ ልጃገረድ ከምኑም የለበት። ወይ ጊዜ ወይ ጊዜ" አሉ በመቆጨት።

"ይልቅስ እማ ዞቢያው ይኸ በቀደም ጊዮርጊስ ተቀበረ ያልሽኝ ሰው ማን ነበር ያልሽኝ ስሙን?

"የቱን ልጅ?"

"በቀደም ጊዮርጊስ ተቀባይ አጥቼ ብቻዬን ሙሾ ስወርድ ዋልኩ ብለሽ የነገርሽኝ!"

"የዛሬ ለቅሶ ምን እልቃሽ አለው ብለህ ልጄ! ሙሾ መውረድ ድሮ ቀረ። ወጣት ወጣቱንማ ይኼ የዘንድሮ ቀሳፊ በሽታ እየጨረሰው እንኳን ሙሾ አውራጅ ቀባሪውም በልክ ነው።

"ይኸ ያልሽኝ ሰው በዚህ በሽታ የሞተ ይመስልሻል?"

"ምኑን አውቄ ልጄ! ቢሆንስ ቤተዘመድ በእርሱ ነው አይል!"

"መቼስ ወሬው አይደበቅ ለቀስተኛውም ቢሆን ማውራቱ ይቀራል?"

"እርሱማ አዎ!"

"እንግዲያ ለቀስተኛው ምንድን ነበር የሚያወራው?"

"ዳሩ ለቀስተኛውስ የታለ? ታላቅ ወንድሙ በድንጋጤ ራሱን ስቶ ሆስፒታል ገብቷል አሉ።

የቅርብ የሚባል ዘመድ ሰው አልነበረም። እኔም የእንጀራ ነገር ሆኖብኝ ገንዘባቸውን ስለበላሁ ነው ያለ ተቀባይ መልኬ! መልኬ! ስል መዋሌ።"

"መልኬ ማነው የአባቱ ስም?"

"መልኬ ማነው አሉኝ ባክህ? . . . እ ቆይማ አዎ! መልኬ አጎናፍር! እኔ ስሜ ይጥፋ ልጄ! ስሙን እንኳ እየጠሩ የሚያለቅሱት የሆኑ ሴቶች ብቻ ነበሩ። ሁለቱ እንዲያውም ልጅ አዝለው ነው የሚያለቅሱ የነበሩት። አዬ! እንግዲህ ማን ያውቃል? እነርሱም ይሄኔ ዲቃላ ያሸከማቸው ልጃገረዶች ይሆናሉ። መቼም ወንድ ልጅ በየጓዳው የፈለፈላቸው ዲቃላዎች ልክ የሞቱ ዕለት አይደበቅ!"

"እንዴት?"

"ምን እንዴት አለ? እርሱ ክዶአቸው ሸሽጎ ቢኖር የሞተ ዕለት ዲቃላዎቹ አባቴ ብለው መምጣታቸው አይቀርማ! ሥጋ አይደል?"

"ግን የቀብሩ ዕለት ሰው ምን ይል ነበር? ይሄ የዘንድሮው በሽታ ነው የገደለው ይላል?"

"ምን አባቴን አውቄ እኔ ልጄ! ሰውማ ብዙ ያወራል"

"ምንድን ለምሣሌ?"

"ገሚሱ ሰው ነው የገደለው ይላል። ገሚሱ ይሄ የዘንድሮው ቀሳፊ በሽታ ነው የገደለው ይላል። ይሄው በሽታ ሳይሆን አይቀርም የገደለው ክፉ ማጋጣ ነበር አሉ።"

"ሌላስ ምን ይባል ነበር?"

"ሌላማ ምን ይባላል ልጄ! ለሞተው ይብላኝለት እንጂ! ለቀስተኛ የሚያስናብት ሁነኛ ዘመድ እንኳ አልነበረውም። የአሟሟት ክፉ! ይልቅስ ደህና ነፍስ አባት ኖሮታል በደንብ አድርገው አሳርገው ለቀስተኛውን አሰናበቱት።"

"እሳቸውስ ምን አሉ ሲያሳርጉ?"

"ያው የሟቹን ያለ ዕድሜው መቀጠፍ ነው የተናገሩት። ሰው ሁሉ ከክፉ ስራው እንዲመለስ እግዚአብሔርን እንዲፈራ ሲያስጠነቅቁ ነበር።"

"ይኸው በሽታ የገደለው ቢሆን ነዋ እማ ዞቢያው?"

"እሱው ይሆናል እባክህ የገደለው። በሳንባ በሽታ፣ በብርድና በተቅማጥ እየተመካኘ ስንቱ አይደል እየተቀጠፈ ያለው! አንተ ዘመድህ ሆኖ ነው ወይስ ባላንጣህ እንዲህ ስለ አሟሟቱ አጥብቀህ ጠያቂ የሆንከው?"

"ኧረ! ምኔም አይደል። እንደአጋጣሚ የሚያውቀው ሰው አግኝቼ ስለነበር ትዝ ብሎኝ ነው።"

"ምን ላድርግ ብለህ ነው ልጄ! የዘንድሮ ባላንጣ ሞት የስጋ ዘመድ ያህል ይከነክናል። ድሮ በእኛ ጊዜ ባላንጣን የት አግኝቼው በገደልኩ ነበር የሚባለው። ዛሬ ጊዜ ተለውጦ የባላንጣ ሞት እንደ እናት ሞት ያህል የሚቆረቁር ሆኗል። ክፉ ጊዜ ደረስን። ሄደን ሄደን . . . ወይ ስምንተኛው ሺ!" አሉ እማ ዞቢያውነሽ በረጅሙ ተንፍሰው።

ይበልጣል ተሰናብቶአቸው ወጣ። ወደ ቤቱ ተመልሶ አልጋው ላይ በጀርባው ተጋድሞ ኮርኒሱ ላይ ዓይኑን ተክሎ በሃሳብ ነጎደ። ልቡን ከባበደው። በአንድ ፊት የቅናት ስሜት በሌላ በኩል ከባላንጣው ሞት የሚመጣበት ዳፋ ሕሊናውን አስጨንቆ ያዘው። እርሱ ለስንት ያሰባት ካፕሬቶ፣ ኩልል ያለች የምንጭ ውኃ እጅ ያልነካት ጽጌረዳ ሲላት የከረመው ማንአለብሽ ትርፌ መልኬ የሚባል መጋዣ መፈንጫ መራገጫ ነበረች። መሞኘቱ አበገነው። ገመሬ ጅንጀሮ እንደዋለበት የበልግ አዝመራ እርመጥምጦ አበሽቃቅጦ ወደ ሞት ሄዷል። ገመሬ ጅንጀሮና ጎረምሣ አንድ አይደል? ከእንግዲህ ምን ትደረጋለች? እርሷን መውደድ፣ እንደ ድሮው መሆኑ፣ ለብዙ ነገር ማሰቡ ይቅር ግን ሌላዋስ እንዴት ትታመናለች? ሰው መውደድ የሚቻልበት ልብስ ከዬት ይመጣል? . ይህቺ ዓለም እንዴት ዓይነት ነች? አንዱ እንደንግሥት የሚያያትን ሌላው እንደመጋዣ ይፈንጭባታል። መቀለጃ፣ መራገጫ አድርጎ ያልከሰክሳታል። ነገሩ አናደደው። የዚህ ሰው ሞት ዳፋ ለእርሱም እንዳይተርፈው ስጋት ተጫጫነው። ዓይኖቹን ኮርኒሱ ላይ ተክሎ ዝም ብሎ አሰላሰለ። ግን ውል ያለው ነገር አልታይህ አለው። ሁለመናው ባዶ ሆነበት።

ካፕሬቶ አልናፈቀችውም። በልቡ ውስጥ በጥንቱ ስፍራ የለችም። . . . ካፕሬቶን ከእንግዲህ ምን ያደርጋታል? ምን ይላታል? ግልጽ አልሆነለትም። እንደወትሮው ሊወዳት መቻሉን ተጠራጠረ። ሳይቸግረው በገዛ እጁ ጎርጉሮ ማወቅ የሌለበትን ያለፈ ታሪኳን አውቋል። "ቅብጠት ነውር ነው የሰራሁት" አለ ለራሱ። "ምንም ይሁን ምንም የሴትን ልጅ ያለፈ ታሪክ፣ ከዕውቂያ በፊት ያሳለፈችውን ሕይወት በቅናት መንፈስ መጎርጎር ብልግና ነው ነውር።" ሲል በራሱ ላይ አጉረመረመ። ከዚህ በኋላ በግል ኑሮው በውጥኑ ላይ የሚያደርገው እርማት ተምታታበት። "ይበልጣል ካፕሬቶ" እያሉ ለሚያበሽቁት ጓደኞቹ ሳይሆን ለራሱ ሕሊና የሚመልሰው ከባድ ሆኖ ታየው። ሰው እንዴት ከራሱ ሊያመልጥ ይቻለዋል? ባዶነት ከንቱነት ዋጠው።
ከትንሽ አፍታ በኋላ ግን አንድ ሃሳብ መጣለት። በመልኬ ሞት ምክንያት ራሱን ስቶ ሆስፒታል የገባውን ታላቅ ወንድሙን አፈላልጎ ማግኘት ደህና ፍንጭ እንደሚሰጠው ገመተ። ከብዙ ጥረት በኋላ ሆስፒታሉንና የተኛበትን ቁጥር አገኘ። ግን አልሆነለትም። አልተሳካም። ወንድምዬው ራሱን እንደሳተ ነው። ይሙት ይኑር ገና አለየለትም። ብዙ ቀን ቢመላለስም እንዳሰበው ሳይሆንለት ቀረ። ራሱን አውቆ ከrecovery ቢወጣም ከአስታማሚ በቀር ሌላ ሰው ሊጠይቀው እንደማይቻል አወቀ። የልቡን ቁስል በሕሊናው ውስጥ የሚተራመስበትን የቅናትና የስጋት እንዳይመች እንፋሎት በሆነ መልኩ መተንፈስ አሰኘው። አንድም ሳያስቀር የመናዘዝ ያህል ፃፈለት። ከህመሙ ድኖ ካነበበው ጥሩ ነገር፣ በዚያው ከወንድሙ ጋርም ከተቀላቀለ ግልግል!! እርሱ ግን ወጣለት። ይበልጣል ካፕሬቶ ተነፈሰ።

ይህን ደብዳቤ የፃፍኩልህ ያ "ይበልጣል ካፕሬቶ" እኔ ነኝ። ለምን ይህን ሁሉ ዝባዝንኬ ለአንተ መፃፍ አስፈለገኝ? አላውቅም። ማወቅም አይኖርብኝም። ግን የታመቀ የውስጥ እንፋሎቴና ሕሊናዬ መተንፈሻ ያገኙ ያህል ቀሎኛል። በራሴ ላይ ለመሳቅ ግን ገና ነኝ። በራስ ላይ መሳቅ መቻል እንዴት ትልቅ ችሎታ ነው? በአንተ ላይ ምን ዓይነት ስሜት ያሳድራል? አላውቅም። ደግሞም አይመለከተኝም። ሙሉ ጤንነትና መልካሙን ሁሉ እመኝልሃለሁ።    አክባሪህ – ይበልጣል 'ካፕሬቶ'

እንደሻው  ሳህሌ ደብዳቤውን አንብቦ እንደጨረሰ አንዳች ነገር ሁለመናውን ወረረው። ባለ በሌለ ኃይሉ ከአልጋው ኮተት ብሎ ወረደ። ከራሱ ጭንቀትና ስጋት ተነስቶ በአንዲት ምሽት የፈፀመው ስህተት ስለነገሩ ምንም የማያውቁ ሰዎችን ኑሮ መመነቃቀሩ ከፉኛ አሳመመው። በራሱ ጥፋት የሌሎችን ጀንበር ማጨለሙ፣ ማጥፋቱ አንገበገበው። መጮህ መጮህ አሰኘው። ደብዳቤውን በእጁ እንደጨበጠ በሩን በርግዶ ወደ ኮሪደሩ ተጣድፎ ወጣ።

"አይደለም! አይደለም! መልኬ አይደለም! ሀሰት  ነው ሀሰት ነው! መልኬ አይደለም" እያለ ኮሪደሩን በጩኸት አናወጠው። ነጫጭ ካፖርት የለበሱ ሀኪሞችና ነርሶች ከየክፍሉ ብቅ ብቅ አሉ። ኮሪደሩ በዚያች አፍታ በሰው ተሞላ።

"መልኬ አይደለም! አይደለም! መልኬ አጎናፍር አይደለም! መልኬ አይደለም! ሲል ዳግመኛ ጮኸ። ገሚሱ ከንፈሩን መጠጠ። አንዳንዱም በሀዘኔታ ራሱን ነቀነቀ። ሐኪሞቹና ነርሶቹ ግን ተረባርበው ያዙት።

"መልኬ አይደለም! መልኬ አጎናፍር አይደለም! ሐሰት ነው! ሐሰት ነው! ይበልጣል ካፕሬቶ መልኬ አይደለም! ለይበልጣል ካፕሬቶ ንገሩት! ለይበልጣል ካፕሬቶ ንገሩት!" እያለ ኮሪደሩን በጩኸት አደበላለቀው። ተወራጨ። ከእጃቸው ለመውጣት ተፍጨረጨረ። ተረባርበው ይዘው አልጋው ላይ አውጥተው አስተኙት። "ይበልጣል ካፕሬቶ! ይበልጣል ካፕሬቶ! ሀሰት ነው! ሀሰት!" እያለ ተውተረተረ። ሐኪሞችና ነርሶች የእንደሻው ሳህሌን አልጋ ከበው መኘታ ክፍሉን አጣበው ቆሙ። የሆነ ነገር በእንግሊዝኛ ተነጋገሩና አንደኛው እንደሻውን ክንዱ ላይ መርፌ ወጋው። ከጥቂት አፍታ በፊት እየተወራጨ፣ እየታገለ፣ እየጮኸ ያስቸግር የነበረው እንደሻው ሳህሌ ጭልጥ አድርጎ እንቅልፍ ወሰደው።

(ተፈጸመ – – – ደግሞ ይቀጥላል)

---


International Culture & Technology Transfer, Inc.
2816 Sans Pareil St.
Jacksonville, Florida 32246
*Telephone (904) 645-6954 Fax (904) 645-3419*

ICATT

**The International Culture and technology Transfer, Inc**. (ICATT - *pronounced as I-KAAT)* is dedicated to the improvement of community quality of life by facilitating the exchange of culture and technology.

**African Cultural Performances:** We can provide you with array of authentic African performing artists who can inspire, inform and entertain your audience.

**Technology Transfer**: We can facilitate an avenue  for you that includes providing local contacts and organizing private or group business tours to Africa.

**Process Consulting for Organizational Empowerment:** We can provide you with consulting expertise in leadership development, teambuilding, strategic planning, staff training & development and organizational process improvement interventions to meet your organizational Empowerement needs.

# የግጥም ጉባኤ
# ቦስጠኛ ቡታን አታምጣ

ከመሪጌታ ልሳኑ ስምረት (ሴንት ሉዊስ)

እስፈርመህ በአውራጣቷ፣ አሻራዋን አትላክልን፣
ኮርጀህ ሆሄ ቀድተህ፣ ምስሏን አትጫርብን።
ኩል እስኩለህ አቃላልመህ፣
ሳንሱር አርገህ ቀለም ደፍተህ።
በገረጣ ቆዳ ሕትመት፣ ጤናዋን አታብስረን፣
ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ፣ በሸንገላ አትደልለን።

መስቀል ስመው መሬት ሰግደው፣
ክራራይሶን እንዳሰሙት፣
በአገር ዋርካ ተለማምነው፣
አድባር አውጋር እንደጠሩት፣
ቸነፈሩን ጦርነቱን፣ ተቋቁመው እንደገቱት፣
እባክህን ቦስጠኛ፣ ተለመነን በአገር ታቦት፣
ክፉ ወሬ አታሰማን፣ እርቀ-ሰላም ይውረድበት።

ወጥተው ወርደው እንዳነቁት፣ እንደፖኒ ኤክስፕሬስ፣
ዳቦ ቆሎ ድርቆሽ ሰፍረው፣
እንደጫኑት ሰንጋን ፈረስ፣
ሶምሱመህ በጎዳናው፣ ኬላ ጥሰህ ፈጥነህ ድረስ።
የሰማይ ወፍ አንጠይቅም፣ አንተ ካለህ ቦስጠኛ፣
አንሰልልም ሌላ ተጓዥ፣ አግዳሚውን መንገደኛ፣
ተናፋቂ እንዳለችው፣ አረግራጊ መዝሙረኛ።
እንግዲህ አንተ እውቀው፣ ሥራ ለሠሪው ነውና፣
ከደንገላሳ ልቀህ ሠግረህ፣
ጋልበህ ቁርጡን ይዘህ ና።

ዓይን ፊቴን አትጋርደው፣ በቀፀላህ አትሸፍነኝ፣
እንደባለከል ኃዘንተኛ፣ ቁቢት አታስለብሰኝ፣
ገላዬን ሰድጄ ልረፍ፣ ከፅጌ ሕልም አትነጥለኝ፣
ጤዛ ረግፎ ረፋድ ሆኖ
ቀትር ሲሆን ውኃ ተኖ
ጠጠር ጥለህ ገድ ቀንቶህ፣ ከሰመመኔ ጎስጉሰኝ፣
ወፍ አይተህ ፊደል ገድፈህ፣
ቡና ፈልቷል ተነስ በለኝ።

በማጎደርህ ባኮፋዳህ፣ ገር መጣጣፍ ይሞላበት፣
እንደ ማሕሌታይ ያሬድ፣ ሐሴት ዜማን ተቀኝበት፣
እንደ ቅጽላ መልካም ሽቶ፣
ጥሩ ዕውደት ይሸተትበት፣
በጎዳግህ በቴምብርህ
በብራና በድርሳንህ
እንደሊዮናርዶ ዳቪንቺ፣ ብርቅዬ ምስል ጫርበት።
"ዳኛ ጠፍቶ ፍርደ-ገምደል፣ ካባ ለብሶ ተሰይሟል፣
ለእናት ዓለም ማን ይደርሳል፤
ሕሊናዬ ተመድምዶ፣ ኮንሸንስ ሁሉ ታሟል" በለን፣
ሐድራ አድርተህ ሞቅ አድርገህ፣
ለጆሯችን ሐቅ አሰማን።
ዚፕ ለዚፕ አዘራዝረህ
ጠረን ሽቶህ በር ቆርቁረህ
እንደ ጣዕረ-ሞት ዲያብሎስ፣
ጥቁር መርዶ አታስረዳን፣
እንደወትሮው ፈካ ብለህ፣
ቼክ ሰብስበህ መጣሁ በለን
ሪፈንድ ይዘህ ሾላ ሞልተህ
የሠርግ ዓለም ጫጉላ ወሬ፣ ገራገሩን ተርኩልን።
እንደአዝማድ ወገኖችህ፣
በረው ከንፈው ዝንተ-ዓመታት፣
በስተርጅና ዳገት ወጥተው፣
እምባ ስቃይ በስልቻ፣
ባቅማዳ እንደጫኑት
ዜና ልከው በመለከት፣
ፈረስ ጋልበው ከች እንዳሉት፣
ደራሽ ሆነህ ድረስልን፣ እውነት ይዘህ አስደስተን፣
ተለመነን ቦስጠኛ፣ በደብዳቤህ አታባባን።

እንደሌሎች ኢትዮፎብ፣ የአፓርታይድ ከለልተኞች፣
ሠርገው ገብተው
ብልት ጠብሰው
የነርቭ ጅማት አክራሪዎች፣
ታሪክ መድማጅ ሰላቢዎች፣
የዘር ፅዳት ጎረዶማን፣ የጂን ሕዋስ ተርታሪዎች፣
እንጀት ገምደው ቁርበት ገፈው
ዓይን ነድለው እንጎል ወቅጠው
እንደሠሩት የአጥር ማገር፣ የሸንሽና ኤክስፐርቶች
ጢፍ አጥፍተው
ብርኃን ጋርደው
ቃፊር ሆነው እንዳበጁት፣ የጎጥ ጉዞ ተላሚዎች፣
ሠናይ አርቅ ፀረ ፍኖት፣ የጭለማ ደምባራዎች።
ቦስጠኛ አትጠራጠር፣ ስጦታህ ይመርልን፣
ሥጋ አትመትር አታሳሳን፣ ስኳር ዜና አስቀምሰን።
እምቢ ካልከኝ ካሻፈረህ፣ በአገሬ ቃል ልርገምህ፣
ደሙ ግሎ
ጥፍሩን ስሎ
ክንፉን ከፍቶ
ኩሱን ረጭቶ
ደረቅ እግር ቁራ ጭልፊት፣ አንዣቦ ይመንችፍህ፣
የጥምብ አንሳ ስግብግቡ፣ የበረሃው የሎስ ያንሳህ።

# ኑሮ  በአሜሪካ


በአሜሪካ ኑሮአችሁ ምን ገጠማችሁ? ኑሮን ለማመቻቸት በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ባሉ የማህበራዊ ኑሮ ችግሮች ላይ ለመወያየት ይህ አምድ አስተዋጽዖ ያደርጋል የሚል እምነት አለን። በውይይት የጋራ መፍትሄ ለማግኘት ይቻላል የሚል እምነት አለን። በተጨማሪም በዚህ አገር ኑሮአችን ተሰባስበን በጋራ የምናከናውናቸውን ተግባራት ለማስተዋወቅም ትልቅ አስተዋጽዖ ያደርጋል እንላለን። አንዱ ከሌላው ልምድ ሊማር ይችላልና። በአምዱ ላይ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የሚቀርቡ አስተያየቶችም ሆነ የገጠመኝ ታሪኮች አንባብያን የሚልኩል መሆኑ ይታወቅልን።

## « እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ »

### ከአትናትዮስ

### ክፍል ሁለት

ከእምሳለና ከዘውዲቱ ጋር የነበረኙን ችግሮች ገለፅኩላችሁ። የአንተስ ጥፋት ታይቶህ ይሆን? የምትሉኝ ካላችሁ ንገሩኝና ልሰማ ዝግጁ ነኝ። እኔ እንዳየኋቸው:- እምሳለ ሁሉ ነገር በእሷ ፈቃድ ብቻ የሚሆን፣ እኔ የእሷ መልካም ፈቃድ ያለበትን ጉዳይ ብቻ የሚፈፅም፣ የእኔ አስተያየትና ፍላጎት ቦታ የሌለው፤ ዘውዲቱ – ቅናት ከማንም ሌላ ሴት ልጅ ጋር ምናልባትም ከእህቴም ጋር ቢሆን ማውራት መገናኘት የሌለብኝ፤ በሉ እንግዲህ ሚዛናዊ ፍርዱን እናንተ እንድትሰጡኝ ልተውላችሁ።

ከዘውዲቱ ጋር ብዙም አልቆየንም። ተለያየን። ሁሌ የማስታውሳት ልጅ ናት። የዋህ ናት። በየዋህነቷም ነው ሁሌም የምትጠቃው፤ የዋህ ስለሆነች በወሬ ትሸነፋለች፤ የዋህም ስለሆነች ነው ቅናት እርር ድብን የሚያደርጋት፣ የዋህ ስለሆነች ሰውን ቶሎ ታምናለች፣ ትንሽም ነገር ስታይባቸው ቶሎ ታኮርፋለች እናም ታሳዝናለች፣ እናም ቅናቷ በጣም አስቸጋሪ በመሆኑ አብሪያት ልቆይ አልቻልኩም። ለተወሰነ ጊዜም ራሴን ከሴቶች ለማራቅ ወሰንኩ። ምናልባትም ከእኔ ችግር ሊኖር ስለሚችል ያንን ለማረም እችል እንደሆን በማለት። ደግሞም ከአንድ Relationship ሲወጣ ወዲያውኑ ሌላ Relationship ውስጥ መግባት አደገኛ ነው እያሉ እዚህ አሜሪካኖቹ የሚያወሩትን ለማየትም ጭምር ነበር ከዚህ ሁኔታ ራቅ ለማለት የፈለግኩት። ትንሽ ጊዜ መውሰድ ጥሩ ነው። ይህንን ስል ዘመቻዬ ተቋረጠ ማለት አልነበረም። አንድ ጊዜ አንዱ ጓደኛዬ ከሌላ ስቴት መጥቶ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ተጨዋወትን እሱ የደረሰበትን ደግሞ ላጫውታችሁ፣ እንደኔው ሞክሮ ሞክሮ ሲያቅተው በአንድ ጓደኛው ሚስት አማካኝነት ኬንያ በስደት ላይ ካለች አንዲት ኢትዮጵያዊት ሴት ጋር በደብዳቤ ይተዋወቃል። ደብዳቤዋ፣ በእጅ ሥራ የተከሸነ ፎቶዋ ይኸደጎድለታል። የሚያያፋት ልጅ ቁም ነገረኛ፣ ትዳር ፈላጊ፣ ጥሩ ጠባይ ያላት፣ ደግ፣ ተጫዋች፣ ጥሩ የሆነውን ነገር ሁሉ ያላት ሆና ተሰማችው። በደብዳቤዋ ብሎም በየሳምንቱ በሚደውልላት ስልክ ፍቅር ከውቅያኖስ ባሻገር ጦፈ። በስደት ላይ ያለች ስለሆነች ችግር እንዳይገጥማትም ገንዘብ ያጎርፍላት ጀመር። ልጅትም ከነፍኩልህ መቸ መጥቼ አለችው፤ መቼ መጥቼ ገላህን ዳብሼው አለችው፤ ጓደኛዬ ነሆለለ። እግዜር መከራዬን አይቶ ካሰኝ ብሎም አመሰገነው። ወዲህ የምትመጣበትን ሁኔታ ሁሉ አመቻቸ። መምጫዋም ቀን ተወሰነ። ቀጥታ ስትመጣም እሱ ቤት እንደምታርፍና ወዲያው እንደሚጋቡም ተቆረጠ።የመምጫዋን ትኬት፣ እንዳይቸግራት ደግሞ ስንቅ የሚሆን ገንዘብ ተላከላት።

ለጓደኞቹም ነገራቸው፤ እኔም ሳይመቸኝ ቀረና ቀረሁ እንጂ ሲቀበላት እንዳጅበው ጠርቶኝ ነበር። የመምጫው ቀን ልዩ ድግስ ተደግሶ እሱ ቤት እንግዶች ተጋብዘው እሱ በአጃቢ አይሮፕላን ማረፊያ ጉንጉን አበባ ይዞ ከሶስት አጃቢ ጓደኞቹ ጋር ይሄዳል። ይዟት ይመጣል የተባለው አይሮፕላን በሰዓቱ አረፈ። መንገደኞቹ መውጣት ጀመሩ፤ በፎቶ ብቻ የሚያውቃት ልጅ ቀርቶ የምትመስልም ልጅ ብቅ አልል አለች። መንገደኛው ሁሉ ወጥቶ ካለቀ በኋላ እንኳ ተስፋ አልቆረጠም። ተሳስቶ እንደሆነ በሚል የአየር መንገዱን ደውሎ ያረጋገጠበትን ማስታወሻ አውጥቶ ቢመለከት አለመሳሳቱን ተረዳ። ምናልባት ሳያይዋት ወርዳ እንደሆነ በማለት ጓደኞቹና እሱ ወዲህ ወዲያ ተራወጡ – እሷን ፍለጋ፤ የለችም። በመጨረሻም ወደ አየር መንገዱ ኪዮስክ ጎራ አለና ጠየቀ። ከፍራንክፈርት – ጀርመን በዚሁ አይሮፕላን መነሳቷን ግን አይሮፕላኑ ኒውዮርክ እግረመንገዱን አርፎ ስለነበር ከኒውዮርክ እሱ ወዳለበት እስቴት አውሮፕላኑ ሲመጣ እንዳልተሳፈረችና መቀመጫዋም ባዶ እንደነበረ ተነገረው። እቤቱ ደግሞ ድግሱ ጦፎ ይዟት ሲመጣ በዕልልታና በሆታ ሊቀበሉት ጓደኞቹ ይጠብቁታል። አብረውት ሊቀበሏት የሄዱት ጓደኞቹ የሚያደርጉት ጠፋቸው። የመምጫዋ ሰዓት የተባለው ከምሽቱ 7:30P.M. የነበረው እስከ 12:30 ሌሊት ድረስ እዚያው አውሮፕላን ማረፊያው ሲንከራተቱ ቆይተው ባዶ እጃቸውን ወደ ቤት ይመለሳሉ። እንግዶችም በዘዴ በዘዴ አይሮፕላን ተበላሽቶ ኒውዮርክ አደረች ተብለው ይሸኛሉ። በጣም

የቅርብ ጓደኛው ሁኔታው ስላላማረው እዚያው አብሮ ያድራል። በሚቀጥለው ቀን ከንጋቱ 7:00A.M. ስልኩ ይደወላል። ልጅት ከኒውዮርክ ሆና ነበር የደወለችው። እሱ ያነሳል።

"ወደ አሜሪካ እንድመጣ ላደረግህልኝ ውለታ በጣም አመሰግናለሁ። በሕይወቴ እስካለሁ ውለታህን ለመመለስ እሞክራለሁ። እኔ ግን ባለብኝ ችግር ወደ አሜሪካ ለመምጣት ብዬ ያደረግሁት ነገር ነው እንጂ በጣም የምወደው ጓደኛ አለኝ፣ አሁንም አብሮኝ ነው የመጣው። እኔም የአራት ወር እርጉዝ ነኝ። ለሁሉም አጥፍቻለሁ ይቅርታ አድርግልኝ።" ብላ እሱ መልስ እንኳ መስጠት በማይችልበት ሁኔታ ስልኩን ትዘጋለች። ጓደኛዬ የሆነውን ሁኔታ ልነግራችሁ አልችልም። በንዴት ብዛት ለጥቂት ጊዜ ታሞ እንደነበረ እሱ ቢደብቀኝም ልሰማ ችያለሁ። ይህ የደረሰበት ሁኔታ በአጠቃላይ አጠገቡ የአበሻ ሴት እንዳትደርስ፣ ብትደርስም እሱ ተራውን ብድሩን እልሁን የሚወጣባት እንጂ አምኖ አብሮ አይዘልቅም። የጋብቻን ነገር እርም ብሎታል። ይህን ታሪክ ልነግራችሁ የበቃሁትበትን ምክንያት ሳትረዱልኝ አልቀራችሁም። በስደት ላይ ካሉ ወይም አገር ቤት ካሉ ሴቶች ጋር ዝም ብሎ በዘመድ ወይ በጓደኛ ተዋውቆ በስልክ ወይም በደብዳቤ ብቻ በሚደረግ ግንኙነት ጋብቻን ያህል ታላቅ ነገር መወሰን ምን ያህል ጎጂ እንደሆነ ለመግለፅ ነው።

በተለይ ከአገር ቤት ስለማምጣቱ ጉዳይ ለወንድሞቼም ሆነ ለእህቶቼ የምመክረው ነገር ቢኖር "መጠንቀቁ አይከፋም፤ ይህ እኔ በቅርብ የማውቀው ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ብዙ ነገሮች ሰምቻለሁ።" እላችሁዋለሁ። መቸም ነገርን ነገር ያመጣዋልና አሁን በቅርቡ ደግሞ እየታየ የመጣው ነገር ቢኖር ወንዱ ከዚህ ለአንድ ሁለት ወር ወደ ኢትዮጵያ ይሄድና ወዲያው ዓይኑ የገባችውን ስለባህርይዋም ስለምኗም ሳያውቅ ጋብቻ መስርቶ ይመጣል። ብዙ ባይሆንም ሴቶች እህቶቼም ከዚህ ሄደው ባል በአጭር ትውውቅ አግብተው እንደሚመጡ ሰምቻለሁ። እንዲያውም ይህ "Quick pick" የሚባል ስም እንደተሰጠው ሰማሁ። ፍርጃ ነው እኮ ጃል። የፈለገው ይምጣ እንጂ እኔን በእነዚህ ሰዎች አካባቢ ደምሬ ከዚህ ኢትዮጵያ ድረስ ሄጄ በአጭር ትውውቅ የኑሮ ጓደኛዬን አገኛለሁ ብዬ አላልምም፣ አላስበውምም።

ምን ይህን ሁሉ አስባለህ? ዝም ብለህ ታሪክህን አትነግረንም የምትሉኝ አትጠፉም። ምክንያት ኖሮኝ ነው። በተለያየ አቅጣጫ ሚስት ለማግኘት በወንዶች በኩል የሚደርሰውን ችግር ለማሳየትና እኔም የዚሁ ችግር ተካፋይ መሆኔን ለማሳየት ይረዳኛል ብዬ ነው። በታሪኬ መጀመሪያ ላይ እንደገለፅኩት በስልክ ብቻ የተዋወቅሃትን ሴት እንዴት አምነህ እሷ ያለችበት ቦታ ድረስ ሄድክ? ለሚለኝ ተፋላሚ "ምን ላድርግ ታዲያ?" ብዬ በየአቅጣጫው ያሉትን ችግሮች ለመጠቆም ነው። ወደ ራሴ ታሪክ ልመልሳችሁ። ከላይ እንደገለፅኩላችሁ ከአንድ ሪሌሽንሽፕ ወደሌላ ሪሌሽንሽፕ ወዲያውኑ መግባቱን አልፈለግሁም። ከዘውዲቱ እንደተለያየን ጥቂት ጊዜ ከሁሉም ነገር ለመራቅ ወሰንኩ። ከአንድ ከሶስት ወር በኋላ ሌላ አጋጣሚ ተፈጠረና ፀሐይ ከምትባል ልጅ ጋር ተዋወቅሁ። ፀሐይ የመጣችው በቅርብ ነው። ዓመት ወይም ሁለት ዓመት ቢሆናት ነው አሉኝ። ቆንጆዬ የደስ ደስ ያላት ተጫዋች ብጤ ናት። ቅርብ ጊዜ የመጣች ላለመምሰል ብዙ ብትጥርም ያስታውቅባታል። "አሜሪካ አገር ብዙ አልቆየሁም ማለት ፋራ ያሰኛል" ብላ በመገመት ያደረገችው በመሆኑ ብዙም አላስጨነቀኝም። የተለመደ ነውና። እና ከፀሐይ ጋር መተዋወቅ መቻሌ ብዙ ነገር እንዳውቅ ረዳኝ። በቅርቡ ከአገር ቤት የመጡ ልጆች ምን ዓይነት እንደሆኑ በወሬ ከሚነገረኝ በቅርቡ ሆኜ ለማወቅ የረዳኝ መሰለኝ ባልሳሳት። ፀሐይ በጣም ግልፅ ትመስላለች። መጀመሪያ ስቀርባት እኔ እንደማውቃቸው በተለይ እዚህ እንደከረሙት የእኛዎቹ ልጆች "Game" የሚባል ነገር አላሳየችኝም። ጥንትም እንደማውቀው የአበሻ ባህርይ ተግደርዳሪ አልሆነችብኝም። እዚህ አገር እንደከራረሙት የቲቪ የፊልም "ተዋናዮች" ዓይነት "Game" "Chemistry" ምናምንዬ፣ ቅብጥርስዩ የለም። ይህን ባህርይዋን ወደድኩላት።ገና አዲስ መጪ በመሆኗም ጭምር መሰለኝ ስሜቷና መንፈሷ አልተረጋጋም። ትቅበጠበጣለች። ዛሬ አንድ ነገር ታቅድና ተነገወዲያ እሱን ረስታ ደግሞ ሌላ ታቅዳለች። የቾውን ነገር ሁሉ መዳሰስ ትፈልጋለች። ይህ እንኳ በሁሉም ላይ ያለና እኔም ያለፍኩበት ነውና ግድ አልሰጠኝም። ቀስ ብላ ትረጋጋለች። እንግዲህ የቸገረኝ ነገር ቢኖር ችኩልነቷ ነው። በጣም ትቸኩላለች። የሚገርማችሁ በተዋወቅን በወሩ፤ ገና አራቴ ያህል ይሆናል አብረን የወጣነው፤ "ለምን አንጋባም" አለችኝ። "ገና በደምብ ሳንተዋወቅ፣ ጠባይ ለጠባይ መግባባታችንን ሳናረጋግጥ እንዴት ይሆናል? አልኳት። "ቀስ ብለን አብረን ሆነን መተዋወቅ እንችላለን" አለችኝ። በፍፁም ሊገባኝ አልቻለም። ጋብቻን ያህል ክቡር ነገር እንደው እንደቀልድ የምናደርገው ነገር አይደለም ብዬ የማምን ሰው ነኝ። ትዳር ለመመሥረት በጣም የምፈልግ ሰው ብሆንም ፀሐይን ደግሞ በቁመናዋና በመልኳ ደስ ትበለኝ እንጂ ስለጠባይዋ፣ ስለዓላማዋ ምንም ያወቅሁት ነገር የለም። እና ላስረዳት ብሞክርም ሊገባት አልቻለም። ፍርጥ አድርጋ ለምን እንደቸኮለች ነገረችኝ። የመጣችው ገና ቅርብ በመሆኑና አሜሪካን አገር የመቆየቷ ጉዳይ ችግር ላይ ያለ ስለሆነ ነበር። ለአሳይለም አመልክታ ያቀረበቻቸው ምክንያቶች በቂ ባለመሆኑ ጥያቄዋን ሊቀበሉ ያልቻሉ መሆናቸውን ኢሚግሬሽኖች ደብዳቤ ስለፃፉላት ጠበቃ አማክራ ያላት ምርጫ ከአሜሪካ ዜጋ ወይም ፈቃድ ካለው ሰው ጋር ጋብቻ መመስረት ብቻ እንደሆነ ስለተነገራት ነው። በእርግጥ እኔ ለዚህ ዓይነቱ ችግር መፍትሔ ብሆን ደስ ይለኛል። ግን ደግሞ ራሴን መጉዳት አይሆንብኝም ወይ? ብዙ ነገር ራሴን ጠየቅሁ። ፀሐይ የቀረበችኝ በእርግጥ ወዳኝ ነው? ወይስ የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት ስትል? እንዲሁ ደስ

ብላኛለች ብዬ ጠባይዋንና ዕቅዷን ሳላውቅ፣ ለችግሯም መፍትሔ ልሁን ብዬ ፈቃድዋን ፈፅሜ ባገባትና ወረቀቷን ካገኘች በኋላ ብትከዳኝስ? ይህን የምናገረው አንዳንድ በጆርዬ የሰማሁዋቸው ተመሳሳይ ድርጊቶች ስላሉ ነው። ለማንኛውም ያለችበት ችግር ስላሳሰበኝም በዚህም ላይ ደስስላለችኝ አብሬአት ጥቂት ጊዜ መቆየትን ፈለግሁ። ነገር ነገሩ የበለጠ ላያትም ነበር። እሷ ግን ባገኙችኝ ቁጥር የምታነሳው የጋብቻውን ጉዳይ ነበር። "እስቲ ትንሽ እንቆይ" በሚል አስተያየት አሳምኜያት ቀጠልን። እንግዲህ እኔ ደግሞ በደምብ እከታተላት ጀመር። ምክንያቱም ጋብቻን ያህል ነገር በቀላሉ ማየት ስላልነበረብኝ ነበር። በምትሰራበትና በምትኖርበት አካባቢ ካሉ ሰዎች ጋር ተዋወቅሁ። እነሱ ስለ እሷ የሚነግሩኝን ለመቀበል ሳይሆን እንዲያው ቀረብ ብዬ እሷን ለማየት ሁኔታው እንዲመቻችልኝ በማለት ነበር።ብዙ ጓደኞች እንዳሉዋት ደረስኩባት። ወንድም ሴትም። ለእኔ ግን የነገረችኝ ብዙ ሰው እንደማታውቅ ነበር።

ሁኔታዋን ስከታተል ግን ከእነኚህ ጎደኞቿ ጋር በጣም የሚቀራረቡና የሚተዋወቁ መሆናቸውን ነበር የደረስኩበት። እነኚህን ጓደኞቿን ደግሞ አላስተዋወቀችኝም። እኔ ግን የእኔን ሁሉንም አስተዋውቂያታለሁ። ፀሐይ የፈለገችውን ለመሆን፣ የፈለገችውን ለማድረግ መብት የላትም ማለቴ አይደለም፣ አደራ እንዳትሳሳቱኝ። ከእኔ ጋር ጋብቻ ለመመስረት በመፈለጓ እኔ ደግሞ ስለእሷ ማወቅ አለብኝ፣ ጋብቻ ከሆነ ደግሞ እኔም ለእርሷ እርሷም ለእኔ ግልፅ መሆን አለብን ከሚል ነው። እና በዚሁ ክትትሌ ፀሐይን አወቅሁዋት። ለምን ለጋብቻ እንዳጣደፈችኝም አወቅሁት። ከአንድ ሌላ ልጅ ጋር በድብቅ ትወጣለች። ይህም ልጅ በጣም የምትወደው በመሆኑ ከእኔ ጋር የምትወጣውን ሁሉ ትነግረውና ለምን እንደፈለገችኝም ትገልፅለታለች። እሱ ዋናው ፍቅረኛ ሲሆን እኔ ግን ለግሪን ካርድ (መኖሪያ ፈቃድ) የተፈለግሁ "ባል" ነኝ ማለት ነው። ከጓደኞቿ አካባቢ በብዙ ድካም ባገኘሁት መረጃ መሰረት ልጅት እኔን አበሳጭታ የፍቺ ጥያቄ ከእኔው እንዲመጣ ለማድረግ እንዳቀደችና ይህንንም ለዚያኛው ፍቅረኛዋ ነግራ ያሳመነችው መሆኑን ስሰማ ገረመኝ። የሰው ወሬ ይሆናል ብዬም በብዙ አቅጣጫ ነገሩን ተከታተልኩ። እውነት ለመሆኑ ብዙ ፍንጮች አገኘሁ። አንደኛው ፍንጭ ከራሷ ከዘውዲቱ ጋር ያደረግሁት ውይይት ነበር። የዚህን የጋብቻ ወሬ ራሴ አነሳሁት አንድ ቀን። ከዚያም አንድ የሆነ ነገር ልንገርሽ ብዬ ራሴ የፈጠርኩትን ታሪክ አወራሁላት። "አንዱ እዚህ ዲሲ፤ አንዷን ያገኛታል። ይወዳታል። እሷም ትወደዋለች። ከዚያ በኋላ ይጋባሉ። እሱ የቆየ በመሆኑና እሷ ቅርብ የመጣች በመሆኗ በእሱ አማካይነት በሚስትነት የመኖሪያ ፈቃድ ታገኛለች። የመኖሪያ ፈቃድዋን ባገኘች በሶስተኛው ወር ጠባይዋ እየተቀየረ ይመጣበታል። ሊያባብላት ቢሞክርም አሻፈረኝ ብላ ጭራሽኑ ፍቺ ትጠይቃለች። ግራ የተጋባውም ባል ሁኔታውን ሲከታተል እሷ ሌላ የምትወደው ሰው እንዳለና፣ እንዲያውም አንዳንድ ቀን በሥራ እያመካኘች የምታድረው እሱ ጋ መሆኑን ሁሉ ይረዳል። እንደተሞኘም፣ ለዚህ ሁሉ መሣሪያ እንዳደረገችው ይረዳና በዚህ ተባሳጭቶ አልኩና ታሪኩን ሳልጨርስ ቆም አድርጌ ሌላ ነገር ለማውራት እንደፈለገ ሰው ሆንኩኝ። ዞር ብዬ ሳያት ዓይኗ ፈጧል፣ አይቼ የማላውቀው ድንጋጤ አየሁባት። "እና ምን አደረገ? ተበሳጭቶ" አለችኝና በጉጉት ጠየቀችኝ።

እኔም ነገሩን ቀለል ያደረግሁ መምሰል "እ! ሰውዬው ነው! እሱማ ተበሳጭቶ ሁለቱን አንድ ላይ ሰውዬው ቤት ያገኛቸውና በሽጉጥ ነፍቶ አመለጠ፣ ይኸው የትም ሊገኝ አልቻለም" አልኩና ትክ ብዬ እየሁዋት። ፀሐይ አይኗ እንደፈጠጠ ነው "ሞቱ ታዲያ እነሱ?" አለች። "ሰውዬው ሞተ፣ እሷ ግን paralysed ሆናለች፣ ምናልባት ከዳነች በwheelchair ይሆናል የምትሄደው?" አልኳት ውሸቱን የፈጠርኩትን ወሬ የበለጠ እያጣፈጥኩት። በጣም ግራ እንደተጋባች ተረዳሁ። ኋላም "እንዴ! ሊተዋት ሲችል፣ ዝም ብሎ መፍታት እያለ ምን አስገደለው? ካልፈለገች ደግሞ ምን ዕዳ አለባት፣ አገሩ አሜሪካ ነው ነፃነት አላት።" እያለች ልጅቷ ያደረገችውን ነገር ሁሉ ትክክለኛ እንደሆነና ይህንንም ለማድረግ ሙሉ መብት ያላት መሆኗን ሽንጧን ይዛ ተከራከረች። ሰውየው ስላደረገላት ውለታ፣ ስለደረሰበት የመንፈስ ወለምታ ምንም ስሜት እንዳልሰጣትና ስለ እሱም ምንም አስተያየት እንዳልሰጠች ስረዳ ነገሩ የበለጠ ገባኝ።

እኔ የፈጠርኩት ታሪክ እውነት ይሁን አይሁን አይደለም ጉዳዩ። እሷን ለመፈተን ሁኔታው ረዳኝ። እናም ይህን ታሪክ ከነገርኳት ቀን ጀምሮ ትሸሸኝ ጀመር። እንኳን ስለጋብቻው ልታወራ ቀርቶ ጭራሽኑ እኔ ጋ ለመምጣት ፍላጎቷ እንደቀነሰ ተሰማኝ። መጀመሪያ ላይ እልህ ሊይዘኝ ነበር ግን ኋላ ምን ጨነቀኝ ብዬ ተውኳት። ቀስ እያለም እየቀረች መጣች። እኔም ተውኳት። ኋላ ኋላ ስሰማም እንዲሁ ከመጣ የቆየ እንዲያውም የአሜሪካ ዜጋ የሆነ ሰውዬ ጋር መውጣት እንደጀመረች ሰማሁ። የድብቅ ወዳጅዋም እንዳለ እንደነበረ ልረዳ ቻልኩ።

የእኔና የፀሐይም ሁኔታ በዚሁ ቀረ እላችኋለሁ። እንግዲህ ሙከራው በየአቅጣጫው መቀጠሉ አይቀርምና እንዲሁ ገጠመኞቼን በአብዛኛው እነግራችሁና እንዴት ወደ "ትዝታ" (አላለልኝ ይሆን?) እንደተሸጋገርኩ፣ ከእሷም ጋር ስለነበረው ሁኔታ በሰፊው እጫውታችሁዋለሁ። አትስልቹኝ፤ የታሪኬን መጨረሻ ሳታዩ ደግሞ ፍርድ ውስጥ አትግቡ፤ አደራ።

(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)

We are proud to be the sponsor of a champion,

***THE ETHIOPIAN ATLANTA SOCCER TEAM.***

We know how to pick winners!

KHAFRA
ENGINEERING CONSULTANTS, INC.

The company where ***"Engineering Excellence"*** is not only a performance, it is a habit too!

**KHAFRA ENGINEERING CONSULTANTS, INC. (KHAFRA)** is a full-service consultant engineering and environmental firm with the following expertise and capabilities:

Environmental Science & Technology
Water Supply Engineering
Water Resources Development
Treatment Plant Designs
Waste Water and Sewer Systems Design
Airport Facilities Design
Water Pollution Control
Water and Waste Water Treatment Plant Operations
Technical Training
Design of Industrial Facilities

Some of **KHAFRA's** clients include the U.S. Environmental Protection Agency, Atlanta Committee for the Olympic Games, the City of Boston, Massachusetts; the City of Birmingham, Alabama; the City of Louisville, Kentucky; the City of Richmond, Virginia; the U.S. Government, and educational institutions.

***Corporate Clients*** include the ***Coca Cola Company*** and ***BellSouth Telecommunications.***

For additional information write to:

**KHAFRA ENGINEERING CONSULTANTS, INC.**
International Division
230 Peachtree Street, Suite 200
Atlanta, GA 30303

Attn: Elias Zewde, P.E., Principal
Ph: (404) 525-0501, Ext. 212
Fax: (404) 522-7941

# ልዩ አምድ

## ስፖርት

## እንኳን ለ፲፪ኛው ዓመት የሰሜን አሜሪካ ኢትዮጵያውያን እግር ኳስ ውድድር በዓል አደረሳችሁ !!

### በናፍቆት የምንጠብቀው ጊዜ!

እንኳን አደረሰን!!

በላቸው ( ከቦስተን)

በሰሜን አሜሪካ ኢትዮጵያውያንን በአንድ ጊዜ በብዛት የሚያሰባስብ ክብረ በዓል ቢኖር በየዓመቱ የሚካሄደው የሰሜን አሜሪካ ኢትዮጵያውያን እግር ኳስ ውድድር ነው። በዚህ ውድድር ወቅት ለረዥም ጊዜ የተለያዩ ጓደኛሞች ይገናኛሉ። አዲስ ጓደኝነትም ይመሠረታል። በየዓመቱ ቢያንስ ከሚያዝያ ወር ጀምሮ ብዙ ኢትዮጵያውያን በስልክም ይሁን በውን ሲገናኙ የሚነጋገሩት ጉዳይ ቢኖር ወደዚሁ በዓል የመሄዱን ጉዳይ ነው። የዓመት የሥራ ፍቃድ ተቆጥቦ ለዚህ ወቅት እንዲውል ማድረግ እየተለመደ መጥቷል። ይህ በዓል ከእስፖርቱ ውድድር ባሻገር ብዙ ጉዳይ የሚካሄድበት እንደሆነ ለመረዳት አያዳግትም። ስለዚህም ሁላችንም በናፍቆት የምንጠብቀው ወቅት ነው።

ባለፉት አስራ ሁለት ዓመታት ሲካሄድ የቆየውን ይህን ዝግጅት ከጥንስሱ ጀምሮ በማቀናባበር፣ በማዘጋጀት አስተዋጽዖ ያደረገውን የሰሜን አሜሪካን ኢትዮጵያውያን እግር ኳስ ፌዴሬሺንን ሳላወሳ አናልፍም። መጀመር ቀላል ቢመስልም ለአስራ ሁለት ዓመታት በተከታታይ መቀጠል ማስቻሉ ጎሽ የሚያሰኝና የሚያስመሰግን ነው። በዝግጅቶቹ ወቅት አንዳንድ ስህተቶች ቢፈጸሙም እነዚህ ስህተቶች ሁን ተብለው የሚደረጉ ሳይሆኑ ከዝግጅቱ ትልቅነት፣ ከተሳታፊዎች ብዛትና ከፕሮግራሙ ሰፊነት የመነጩ ስለሚሆኑ ስህተቶቹን ከሚሰጡት ጥቅም በላይ አጉልተን ማየት አይኖርብንም ባይ ነኝ። እነኚህን ስህተቶች በመጠቆም አስተያየቶችን በመስጠት እንዲታረሙ ለማድረግና ወደፊት እንዲሻሻሉ ጥቆማዎችን ማድረግ አስትዋይነት ነው። ስህተቶች ሲገለጹ እንዲታረሙ ለማሳሳብ እንጂ ጭራሹኑ የተጀመረው በጎ ተግባር እንዲቋረጥና የአዘጋጁን ክፍል ተስፋ እንዲያስቆርጥ መሆን የለበትም። በዚህ ላይ የምጠምረው ጉዳይ ቢኖረኝ ለፌዴሬሽኑ የማስተላልፈው መለዕክት ይሆናል። በአንድ ወቅት የተደረጉ ስህተቶች ለሌላ ወቅት ትምህርት ይሁኑና እባካችሁ አይደገሙ። ችግሩ ምንድነው? ለምሳሌ አምና በዋሺንግተን ኮንቬንሽን ሴንተር የሆነውን ሁኔታ ዓይነት ከእንግዲህ እንኳን በውኔ በህልሜም ላየው አልሻም። እና በበጎ ዓላማ የጀመራችሁት እያካሄዳችሁ ያላችሁት ተግባር ጎልምሶ ከካቻምናው የአምናው፤ ከአምናው የዘንድሮው የበለጠ አምሮ ደምቆ እንዲታይ ከህዝብ የሚጠቆሙ ስህተቶች ይታረሙ እላለሁ። በርቱ፤



# ከአምናው ትዝታ









# የአትላንታ ኢትዮጵያውያን የእግር ኳስ ቡድን



የአሁኑ የአትላንታ እግር ኳስ ቡድን ተጫዋቾች (ናሽቪል ለሪጅኑ የመጨረሻ ውድድር)

የአትላንታ ኢትዮጵያውያን የእግር ኳስ ቡድን በ1978 ዓ.ም. በጥቂት ሰዎች ለመዝናኛና ለጤንነት ተብሎ በመጀመሪያ እንደተቋቋመ ይነገራል። ከዚያም በየጊዜው እያደገ በመሄድ ከነበረበት ቦታ ከፍተኛ ተወዳዳሪ በመሆን 1984 ዓ.ም. በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ስፖርት ፌድሬሽን ከጀመሩት አራት ቡድኖች አንዱ ለመሆን በቅቷል። ከዚያም ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1993 ዓ.ም. ድረስ ስምንት ጊዜ ለዋንጫ ጨዋታ የደረሰ ነው። በ1994 ዓ.ም. የዋንጫ አሸናፊ ሆኗል። በየዓመቱም በሚደረገው ውድድር በጣም አስፈላጊ የሆነውን የፀባይ ዋንጫ ሁለት ጊዜ አሸናፊ ለማግኘት ችሏል።





በ1982 የአትላንታ ቡድን ተጫዋቾች (እነኚህ መሥራቾቹ ናቸው)

የአትላንታ እግር ኳስ ቡድን ጆርጂያ ስቴት ውስጥ በተደረገው ውድድር በ1991 ዓ.ም. በሶስተኛ ምድብ ውስጥ ገብቶ የምድቡ አሸናፊ በመሆን ወደ ሁለተኛ ምድብ አለፈ። በ1993 ዓ.ም. ከ2ኛ ወደ አንደኛ ምድብ አልፎ ብዙ ውድድሮችን ተካፍሏል። በ1994 ዓ.ም. በተለያዩ ውድድሮች ተሳትፎ አሸናፊ ለመሆን በቅቷል። በተጨማሪም በአትላንታ ከተማ የተዘጋጀውን የጥሎ ማለፍ ውድድር ከ42 ቡድኖች ጋራ ተዋዳድሮ 2ኛ በመሆን ጨርሷል። በዚሁ ዓመት ማለት በ1994 የሰሜን አሜሪካ ኢትዮጵያ ስፖርት ፌዴሬሽን ዋንጫ፣ አሸናፊ ሆኖል። በቅርቡ 1995 ዓ.ም. በጆርጂያ ስቴት ሻምፒዮንነቱ ስቴቱን ወክሎ ናሽቪል ቴኔሲ በተካሄደው የደቡብ ምሥራቅ አሜሪካን ሪጂናል ዋንጫ ውድድር በመሳተፍ የዳላስንና የፍሎሪዳን ቡድኖች ካሸነፈ በኋላ ለመጨረሻው ውድድር ከኖርዝ ካሮላይና ጋር በመጫወት ሁለተኛ ለመሆን በቅቷል። አሁን በጆርጂያ ሻምፒዮና፣ በሪጂኑ ደግሞ ሁለተኛ ነው። በተጨማሪም በአትላንታ በዚሁ ዓመት በ42 ቡድኖች መካከል በተደረገው የጥሎ ማለፍ ውድድር አሸናፊ በመሆን የዋንጫ ባለቤት ለመሆን በቅቷል።



ለዚሁ እስፖርት ማደግና በየጊዜው በቅርቡ በመገኘት ጊዜአቸውን በማካፈልና በገንዘብም እርዳታ ከቡድኑ ሳይለዩ የቆዩ ሰዎች በርካታ ናቸው። ጥቂቶቹን ለመግለጽ ቢያስፈልግ፣ ሲሳይ ተዘራ፣ ፀጋዬ ወልደማርያም፣ እንዳለ ተፈራ ሲሆኑ እንዲሁም ቡድኑ ውስጥ በመጫወትና በተለያዩ የአመራር ቦታ ላይ ያገለገሉን፣ መ ሀመድ ሀወል፣ ወንድወሰን ደስታ፣ አቦነህ ማሞ፣ ንጉሤ አስፋው፣ ሸዋንግዛው ተረፈ፣ አያሌው ሞገስ ሲሆኑ አሁን በቅርብ ጊዜ ደግሞ ክለቡን ከነበረበት ደረጃ አንስተው አሁን ከላይ ለተጠቀሱት ድል ለመጎናፀፍ፣ የቲሙን የአስተዳደርና የአሠራር ሁኔታ በማስተባበር ጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል። ለዚህም ማርቆሪዎስ አዳፍሬ፣ ሰለሞን ደምሴና አምሳሉ ከበደ መጠቀስ ያለባቸውመሆናቸውን ከክለቡ ለመረዳት ችለናል። በሌላ በኩል ደግሞ ተጫዋቾቹ በማንኛቸው እስፈ

ላጊ ቦታ ሁሉ በመግባት ከኮሚቴው ጋር በመተባበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ መሆናቸውን ለማወቅ ችለናል። የቡድኑ አባላት ከኳስ ጨዋታው ባሻገር መረዳዳትን፣ ከጊዜ ጊዜ የሚደርሱትን ችግሮች በመመካከር መወጣትን፣ በትምህርት ላይ የሚገኙትን ታዳጊ ተጨዋቾችን መርዳትን የመሳሰሉትን በጎ ተግባራት በማከናወን ለሌሎች ምሳሌ ናቸው ቢባል ስህተት አይሆንም። ወደፊቱም እንቅስቃሴአቸው እየተስፋፋ ከህብረሰቡ ጋራ በመተባበር ብዙ ነገሮችን ለመሥራት ዕቅድ እንዳለው ለማወቅ ተችሏል።

## ጥቂት ስለ ቡድኑ አባላት

የቡድኑ አባላት የቀድሞውም ሆኑ ያሁኑ በሙሉ ለዚህ ቡድን እዚህ ደረጃ መድረስ ትልቅ አስተዋጽዖ አድርገዋል። ስለሁሉም ለመጻፍ ቦታ ስለማይበቃን ስለ ጥቂቶቹ ትንሽ ብናወራ በጣም ደስ ይለናል። በዚህኛው እትም ላይ ያላቀረብናቸውን ድንቅዬ ተጫዋቾች ታሪክ በሰፊው በሚቀጥሉት እትሞቻችን ላይ እናቀርባለን።

## አሰልጣኝ እንዳለ ቱፈር



የአትላንታ እግር ኳስ ቡድን ከታነፀ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ለቡድኑ ምሶሶ በመሆን ያገለገለ፤ ግልጋሎቱ በአባልነት ብቻ ሳይሆን ጭምር ነው። እንዳለ በቡድኑ አባላሎች የተከበረ፣ ለሁሉ አባላት አሳቢ፣ አስተባባሪ ሰው ነው። ጊዜውንና ጉልበቱን መስዋእት በማድረግ ክለቡን አሁን እዚህ የሚያኮራ ደረጃ ያደረሰው እንዳለ ቱፈር ነው። በኳስ ብቻ ሳይሆን ህብረሰቡን በማሰባሰብ ወንድማማችነትና መረዳዳት የሚገኙበትን ዘዴዎች አቋቁሞል። አዳዲስ ወጣት ተጫዎቾችንም ሲመጡ አገር በማለማመድ፣ ሥራ በማስያዝ ትምህርታቸውን እንዲገፉ በማድረግ ብዙ ረድቷል። የእንዳለ ውለታ በመላው የአትላንታ ቡድን አባላት መካከል ከፍ ያለ ነው። ወጣቶቹም የሱን ምክርና የሥራ ሁኔታ በማየት ትልቅ ትምህርት እየተማሩ ናቸው።



ንጉሤ አስፋው

በዋና ገንዘብ ያዥነትና በኋላ ተጫዎችነት ለብዙ ጊዜ ክለቡን ያገለገለ ነው። ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ብሄራዊ ቡድን ተጫወቷል።

### አቦነህ ማሞ

ለአትላንታ ቡድን ለብዙ ጊዜ በጸሀፊነት፣ በአባልነት፣ በተጫዎችነት ያገለገለ ሰው ነው። አቦነህ ማሞ ኢትዮጵያም ውስጥ ለብሄራዊ ቡድን ይጫወት ነበረ።

### ሽዋንግዛው ተረፈ

በአትላንታ ቡድን ውስጥ በተጫዎችነትና በአባልነት ለብዙ ጊዜ የቆየ ነው። በኢትዮጵያ ከብሄራዊ ቡድን ውስጥ ሲጫወት ታላቅ አድናቆትን ያተረፈ ነው።

### አያሌው ሞገስ

በአትላንታ ክለብ ውስጥ በጣም ተወዳጅነትን ያተረፈ ምንግዜም የማይድክመው፣ ቡድን ውስጥ ሲጫወት ታላቅ አድናቆትን ያተረፈ ነው።

### የአትላንታ ቡድን አባላት

ቻላቸው መለሰ
አፈወርቅ ከበደ
ዳንኤል ክፍሌ
ዳዊት ኃይለአብ
ጎሳ ብርሃኑ
ንጉሤ አስፋው
ሸዋንጋዛው ተረፈ
ሲሳይ አስፋው
ዘላለም ተሾመ
ሰለሞን
ክፍሉ

አቦነህ ማሞ
አያሌው ሞገስ
ዳንኤል ተረፈ
ጌቱ ከበደ
መኮንን ጉርሙ
ርዕሶም ገ ትንሣይ
ሰይድ አብደላ
ወንድወሰን አበራ
ቤዛ አበበ
መሰለ

<u>የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ</u>
መርቆሪዮስ አዳፍሬ አምሳሉ ከበደ
ሰለሞን ደምሴ ንጉሤ አስፋው

<u>የእምናው ሥ አ ኮሚቴ</u>
ጸጋዬ ተ ማርያም
ሲሳይ ተዘራ
አቦነህ ማሞ

አፈወርቅ ከበደ (ካቻ)



ዳንኤል ክፍሌ



ጎሳ ብርሃኑ



<u>አፈወርቅ ከበደ (ካቻ) ዳንኤል ክፍሌና ጎሳ ብርሃኑ</u> በተመልካች ዘንድ ከፍተኛ አድናቆትን ያተረፉ ወጣት ተጫዋቾች ናቸው። ሁለቱም ኢትዮጵያ የብሄራዊ ቡድን ተጫዋቾች ነበሩ።
አፈወርቅ (ካቻ) የኢትዮጵያ ወጣቶች ብሄራዊ ቡድን አንበል እንደነበረ ይታወቃል። በአሁኑ ጊዜ በትምህርት ላይ ናቸው። እነኚህ ሶስቱና <u>ቻላቸው መለሰ</u> በድንቅ ጨዋታቸው ለጆርጅያ ምርጥ ቡድን እንዲጫወቱ በእስቴቱ ዋና አሰልጣኝ ተመርጠው ጨዋታ ጀምረዋል።

# እግር ኳስ . . .የዓለም ዋንጫ

ከመኮንን ጉርሙ (ከአትላንታ ጆርጂያ)

በየአራት አመቱ አንዴ የሚዘጋጀው የዓለም የእግር ኳስ ዋንጫ እንዳለፉት ጊዜያት ሁሉ ሃያ አራት ሀገሮችን አካቶ በታላቅ ድምቀት በሎስአንጀለስ ከተማ በሮዝ ቦል ስታዲየም ባለፈው ዓመት ተፈጽሟል። በዚህም ውድድር በኳስየአጨዋወት ስልታቸው ዓለምን የማረኩት ብራዚላዊያን ለአራተኛ ጊዜ አሸንፈው ሻምፒዮን ሆነዋል።

## የአለም ዋንጫ እንዴት ተጀመረ

የአለምን ዋንጫ እንዲጀመር ያደረገው ጁሊየስ ሪመንት የተባለ ፈረንሳዊ ነው። ለዚህም ነው የጁሊየስ ሪመንት ዋንጫ ተብሎ በስሙ የተሰየመው። ይህንንም ዋንጫ ለሶስት ጊዜ በማሸነፍ የግላቸው አድርገው ያስቀሩት ብራዚላዊያን ናቸው። ብራዚሎች ይህንን ዋንጫ የራሳቸው ያደረጉት በ1958 ዓ.ም ስዊድን ላይ ስዊድንን አምስት ለሁለት አሸንፈው በ1962 ዓ.ም ቺሌ ላይ ፖርቹጋልን ሶስት ለአንድ በማሸነፍና በመጨረሻም በ1970 ሜክሲኮ ላይ ካቴና ቱቦ በመባል የሚታወቀውን የጣሊያንን የመከላከል ዘዴ አፈራርሰው አራት ለአንድ በሆነ በሰፋ ልዩነት በማሸነፋቸው ነበር።




የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ መኮንን ጉርሙ የአትላንታ እግር ኳስ ቡድን ተጫዋች ነው

## ውድድሮቹ የትና የት ተጀመሩ።

* የአለም ዋንጫ የተጀመረው ከ1930 ዓ.ም ወዲህ ነው። ውድድሩንም ለመጀመሪያ ጊዜ ያዘጋጀችውም ዑራጓይ ነበረች። በውድድሩም ዑራጓይ አርጀንቲናን አራት ለሁለት አሸንፋ ለመጀመሪያ ጊዜ ሻምፒዮን ሆናለች።
* በ1934 ሁለተኛው የአለም ዋንጫ አዘጋጅዋ ጣሊያን ስትሆን በውድድሩም ጣሊያን ቼኮዝሎቫኪያን ሁለት ለአንድ አሸንፋለች።
* በ1938 ሶስተኛው የአለም ዋንጫ አዘጋጅዋ ፈረንሳይ ነበረች። በውድድሩም ጣሊያን ሀንጋሪን አራት ለሁለት አሸንፋ ለሁለተኛ ጊዜ ዋንጫውን ሀገሯ ወሰዳለች።
* በ1942 ዓ.ም እና በ1946 ዓ.ም በሁለተኛው የአለም ጦርነት ምክንያት ውድድሮች አልተካሄዱም።
* በ1950 አራተኛውን የዓለም ዋንጫ ያዘጋጀችው ብራዚል ነበረች። እንዳሁኑ የእግር ኳስ ህግ በደንብ ከመርቀቁ በፊት ለፋይናልም ሁለት እድል ይዞ መግባት ይቻል ነበርና ሁለት እድል ይዞ የገባው የብራዚል ቡድን በዑራጓይ ሁለት ለአንድ ተሸንፎ ዋንጫውን አጥቷል ።
* 1954 አምስተኛውን የዓለም ዋንጫ ያዘጋጀችው ስዊዘርላንድ ነበረች። በውድድሩም ምዕራብ ጀርመን ሀንጋሪን ሶስት ለሁለት አሸን<u>ፏል</u>።
* በ1958 ስድስተኛውን የዓለም ዋንጫ ያስተናገደችው ስዊድን ነበረች። ለየትና ረቀቅ ያለ ፉትቦል የታየበት ዘመን ነበር። ታላቁም የኳስ ንጉስ ኤድሰን አራንቶስ (ዲና) ሲሚንቶ ወይንም (ፔሌ) ለመጀመሪያ ጊዜ የታየበት ዘመን ነበር። በውድድሩም ብራዚል ስዊድንን አምስት ለሁለት አሸን<u>ፏል</u>።
* በ1962 ሰባተኛውን የዓለም ዋንጫ ያዘጋጀችው ቺሊ ነበረች። በውድድሩም አንጋፋው የብራዚል ቡድን ቼኮዝላቫኪያን ሶስት ለአንድ አሸንፎ ዋንጫውን ለሁለተኛ ጊዜ አገኘ።
* በ1966 ስምንተኛውን የዓለም ዋንጫ ያስተናገደችው እንግሊዝ ነበረች። እንግሊዝና ጀርመን ለዋንጫ ደርሰው ዘጠናውን ደቂቃ ሁለት በሁለት በሆነ ውጤት በመጨረሳቸው በጭማሪው የሰላሳ ደቂቃ ጊዜ እንግሊዝ ሁለት ጎል በማስገባቱ ውድድሩን አራት ለሁለት በሆነ ውጤት አሸን<u>ፏል</u>።

* በ1970 ዘጠነኛውን የዓለም ዋንጫ ያስተናገደችው ሜክሲኮ ነበረች። ለአርባ ዓመታት ሙሉ ከቦታ ቦታ ስትንከራተት የቆየችው የጁሊየስ ሪመንት ዋንጫ ዕድሜውን በማሳጠር የብራዚል ቡድን ጣሊያንን አራት ለአንድ በሆነ የሰፋ ልዩነት በማሸነፍ ዋንጫውን የብራዚል የግል ሀብት ብቻ እንድትሆን አድርገዋታል።
* በ1974 አስረኛው የዓለም ዋንጫ የተካሄደው በምዕራብ ጀርመን ነበር። ፊፋ (FIFA) ያዘጋጀውን ዋንጫ ለመጀመሪያ ጊዜ ያሸነፉት ምዕራብ ጀርመኖች የሆላንድን ቡድን ሁለት ለአንድ በማሸነፍ ነበር።
* በ1978 የአስራአንደኛው የዓለም ዋንጫ አዘጋጅዋ አርጀንቲና ስትሆን በውድድሩም አርጀንቲና በራሷ ሜዳ የሆላንድን ቡድን ሶስት ለአንድ አሸንፋለች። አርጀንቲና ይህንን ዋንጫ ስታሸንፍ በዘጠናው ደቂቃ አንድ ለአንድ ወጥታ በተጨመረው ሰላሳ ደቂቃ ሁለት ጎሎችን አስገብታ ነበር።
* 1982 አስራ ሁለተኛውን የአለም ዋንጫ ያስተናገደችው ስፔን ነበረች። በውድድሩም ጣሊያን ምዕራብ ጀርመንን ሶስት ለአንድ አሸንፋ አዲሱን ዋንጫ ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም ዋንጫ ታሪክ ደግሞ ለሶስተኛ ጊዜ ሻምፒዮን ሆነዋል።
* 1986 አስራ ሶስተኛውን የዓለም ዋንጫ ያዘጋጀችው ሜክሲኮ ስትሆን በውድድሩም አርጀንቲና የምዕራብ ጀርመንን ቡድን ሶስት ለሁለት አሸንፋለች።

* 1990 አስራ አራተኛውን የዓለም ዋንጫ ያስተናገደችው ጣሊያን ነበረች። በውድድሩም ባለፈው አራት ዓመት ለዋንጫ የተገናኙት ቡድኖች በድጋሚ ለዋንጫ ቀረቡ። አርጀንቲና ካሸነፈ ለሶሶተኛ ጊዜ ስለሆነ ዋንጫውን ለማስቀረት፣ ምዕራብ ጀርመን ደግሞ ያለፈው ይበቃል በማለት በልበ ሙሉነት ተፋጠጡ። በውድድሩም ጀርመን በፍፁም ቅጣት ምት አንድ ጎል አስቆጥሮ አዲሱን ዋንጫ ሁለቴ በዓለም የዋንጫ ታሪክ ደግሞ ለሶስተኛ ጊዜ ሻምፒዮና ሆነ።
* 1994 አስራ አምስተኛውን የዓለም ዋንጫን ያስተናገደችው ዩናይትድ ስቴትስ ነበረች። ሁላችንም እንዳየነው ለመጀመሪያ ጊዜ በአለም ዋንጫ ታሪክ በዘጠናው ደቂቃና በጭማሪው ሰላሳ ደቂቃ ስላልተሸናነፉ በተሰጠው የፍፁም ቅጣት ምት ዋንጫውን ማግኘት ይገባዋል የሚባለው የብራዚል ቡድን ጣሊያንን ሶስት ለሁለት አሸንፎ ከሃያ አራት ዓመታት በኋላ ሻምፒዮን ሆነዋል።

በዚህም ብራዚል ለአራተኛ ጊዜ ዋንጫውን በማግኘት ቀዳሚ ስትሆን ጣሊያንና ጀርመን ደግሞ ሶስት ሶስት ጊዜ አግኝተዋል። አርጀንቲናና ዑራጓይ ደግሞ ሁለት ሁለት ጊዜ ሲያገኙ እንግሊዝ አንድ ጊዜ አሸንፋለች። እንግዲህ የአለም ዋንጫ አመሰራረቱ ይህንን ይመስላል።





# አዳም ና ሔዋን

አዳምና ሄዋን የተሰኘው አምዳችን የሚያተኩረው በተቃራኒ ጾታዎች መሃል በሚኖረው ግንኙነት ላይ ነው። የገጠመኝ ታሪኮችና አስተያየቶች የመሳሰሉት ይቀርባሉ— በእውነተኛ ገጠመኝ ላይ የተመሠረቱ የፍቅር ታሪኮችንም እናቀርባለን። አምዱን የመወያያና የመማሪያ አምድ ለማድረግ እንዲቻል አንባብያን አስተዋጽዖአችሁን እንጠይቃለን። በአምዱ ላይ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የሚቀርቡ አስተያየቶችም ሆነ የገጠመኝ ታሪኮች አንባብያን የሚልኩል መሆኑ ይታወቅልን።

## ዕጣዬ

### ከአብርኽት

"ዕጣዬ" በተሰኘ ርዕስ አብርኸት (የብዕር ስሟ ነው) በስደት ኑሮዋ የገጠማትን በተከታታይ እያቀረበችልን ነው። ይህን አሳዛኝ የፍቅርና የስደት ታሪክ ለአንባብያን ስናቀርብ አቀራረቡን እንዲጥም ከማድረግ በቀር በታሪኳ ላይ የጨመርነው ሆነ የቀነስነው ነገር የለም። እሷ በአሁኑ ወቅት በአሜሪካ አገር በስደት ላይ ናት።

---

አብረኸትና ፍቅረኛዋ ሰይፉ በገዳሪፍ የገጠማቸውን ሁኔታና በተለይም በዚሁ ከተማ የኢትዮጵያ ስደተኞችን አኗኗር ተርካልናለች። እሷንና ፍቅረኛዋን ሰይፉን የቀጠረው ነጋዴ አብረኸትን ፈልጓት እሷ ደግሞ ከዚህ ውስብስብ ወጥመድ ራሷን አውጥታ ለፍቅረኛዋ ሰይፉ ያላትን ታማኝነት ለመግለፅ ያደረገችውን ጥረት ተርካልናለች። ከገዳሪፍም ለመውጣት ጥረት መጀመራቸውን ካለፈው ክፍል ፰ ትረካ እንድንረዳ አድርጋለች። የዛሬው ታሪክ ከዚያው የቀጠለ ይሆናል።

## ክፍል ፱

በስደት ላይ ያለን ሁሉ መረዳዳት መደጋገፍ ነበረብን። ቀደም ሲል እንደነገርኳችሁ አንዱ ችግር ላይ ከወደቀ፣ ለምሳሌ ስራ ካጣ ወይም ካለበት ሥራ ሊባረር ከሆነ የመሳሰሉት ችግሮች ቢደርሱበት ለመርዳት የማይፈልግ አይኖርም። እንግዲህ ደግሜ እለዋለሁ። ይህንን የመተሳሰብና የመረዳዳት ሁኔታ የማየው በመሐል አገር በመጣው ስደተኛ ላይ ነው። ከኤርትራ የመጡት ስደተኞች የሚረዱት፣ የሚደግፉት ከራሳቸው አካባቢ የመጣውን እንጅ ወይም ኤርትራዊ የሆነውን እንጂ ሌላውን አይደለም። በፍፁም ራሳቸውን ልዩ አድርገው ነው የሚያዩት ብዙዎች የአረብኛ ቋንቋ ችሎታቸው ልዩ ዕድል እንደሰጣቸው፣ ራሳችውንም እንደ አረብ ለመቁጠር የሚፈልጉ ሞልተውባቸዋል። እና አንድ ከመሐል አገር የመጣ ስደተኛ እንኳን ጥፋት ኖሮት ሳይኖርበት ጥፋት አለው ብለው እሱን ማስያዝ፣ ማሳሰር በምትኩም ሌላ የእንሱን ሰው ሥራውን እንዲይዝ ማስደረግ፣ ብቻ ምን አደከማችሁ ይህን የመሰለ የሚያሳዝን ሥራ ይፈፅሙ እንደነበር እዛ የነበረው ሁሉ የማይስተው ነው። እነሱም ቢሆኑ የማይክዱት ነው። ይህን ያህል ምርር ያደረገሽ ምንድነው ትሉኝ ይሆናል፤ ለምን አልማረርም? የሆንኩትንና ያደረጉኝን ልንገራችሁ።

ቀደም ሲል እንደነገርኳችሁ የምንኖርበት ነጋዴ ችግር እያመጣብኝ ስለሄደ፣ በተለይም ደግሞ የእኔንና የሰይፉን ግንኙነት ካወቀ በጣም መጥፎ ሁኔታ ስለሚፈጥር ከዚህ ችግር ለመላቀቅ ገዳሪፍን ለቀን ለመውጣት እንድንችል ሃሣብና ድጋፍ እንዲሰጡን ሌሎች አበሾችን መተዋወቅ አስፈላጊ ሆነ። በመሆኑም እኔም ሰይፉም በየበኩላችን ብዙ ሰው ተዋወቅን። እኔም ተክሌ ከሚባል ከኤርትራ ከመጣ ስደተኛ ጋር ተዋወቅሁ። ያው ትግሪኛ ተናጋሪ ስመሆኔ አልተቸገርኩም።

ከተክሌ ጋር እንደተዋወቅሁ ያለንበትን ችግር ነገርኩትና እንዲረዳን ለመንኩት። አንደኛ በአካባቢው ብዙ ጊዜ የኖረ፣ ታዋቂነትን ያተረፈ በመሆኑ እሱ ጥሩ መንገድ ይሰጠናል የሚል ግምት ነበረኝ። በመጀመሪያ አቀባበሉ ጥሩ ነበር። በተለይ ያ ነጋዴ ሰውዬ ሊጫወትብኝ ይፈልጋል ስለው ከዚያ ለመሸሽ የማደርገውን እርምጃ ወደደልኝ። ስለ ሰይፉ ያወቀውም የጠየቀውም ነገር የለም። ከአማራ ጋር ግኑኝነት ይኖራታል የሚል ጥርጣሬ ስላልነበረውም መሰለኝ። እና ሊረዳኝ እንደሚችል ነገረኝ። ግን የፈለገው ነገር ነበር። አፍ አውጥቶ ባይጠይቀኝም መጀመሪያ ላይ ከሰውዬው ቤት ውጪና መጥተሽ እኔ ቤት ተደብቀሽ ኑሪ አለኝ። "ከዚያስ" ስለው "እኔም አብሬ ከአንቺ ጋር እጠፋለሁ" አለኝ። "ልጁን እንዴት እናደርጋለን?" አልኩት "ማንን" አለኝ። "ሰይፉን" አልኩት። ቀደም ሲል ስወጣ የረዳኝ ሰው ነው ብዬ ጨረፍ አድርጌ ነግሬው ነበር።

"ስለ እሱ ታዲያ ምን አገባሽ? እሱ የራሱ ችግር ነው? የአንቺ ሌላ ነው? አለኝ።

"ምንም ቢሆን ውለታ ውሎልኛል። ያን ሁሉ በረሃ ሳቋርጥ የረዳኝ፣ በጣም የረዳኝ ሰው ነው። እስካሁን አልተለያየንም እና አየህ እኔ ብጠፋ እሱን ያሳስረዋል፣ ስለዚህ . . . " ብዬ የተናገርኩትን ሳልጨርስ "አልግሺ! ለሃድጊ አማራ ይህን ያህል ምን አስጨነቀሽ?" ሲለኝ ደሜ ከውስጤ ፈላ። ተናደድኩ፤ ግን መቻል ነበረብኝ።በእኔና በሰይፉ መሃል ያለውን ግኑኝነት ብነግረው ደግሞ ምን እንደሚል መገመት የሚያቅተኝ አይምስላችሁ።

እና ዝም ማለቱን መረጥኩ። ይህ ሁሉ ጥላቻ ከምን እንደሚመነጭ ዘላለም ሲገርመኝ ይኖራል።

ሰይፉ ብዙ ውጪ የመውጣት ዕድል ስለነበረው ብዙ ኢትዮጵያውያኖችን ተዋወቀ። መተዛዘኑና መደጋገፉ በይበልጥ ከመሐል አገር በመጡት ላይ ጎልቶ ይታያል። ሰይፉ ከተዋወቃቸው ኢትዮጵያውያን መሐል ከሁለቱ ጋር የበለጠ ግኑኝነት ፈጠረ። አንደኛው ስሙ ፋሲካ ይባላል። ፋሲካ የመጣው ከአዲስ አበባ ነው። በቀይ ሽብር ወቅት በአዲስ አበባ ቀበሌዎች በጣም ሲፈልጉት ጠፍቶ ነው የወጣው። እዚህ ገዳረፍ መኖር ከጀመረ ቆይቷል። ሌላኛው አጥናፉ ሲሆን እሱ ደግሞ ከጎንደር ከተማ ጠፍቶ ከመጣ ቆይቷል። ሁለቱ አንድ ላይ ነው የሚኖሩት። እርስ በእርሳቸው መረዳዳት ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም በጣም ብዙ የረዱ ናቸው። ለሰው ሲሉ ብዙ የሚደክሙ በመሆናቸው የራሳቸው እልባካ ብሎአቸው ከገዳረፍ እንኳ መውጣት አለመቻላቸውን ሰማን።

ሰይፉ እንደተዋወቃቸው ችግሩን ሁሉ ግልፅ አድርጎ ነገራቸው። ከዚያም ቀጠሮ ያዘና አንድ ቀን አብረን እቤታቸው ሄድን። ቀጣሪዬን ዕረፍት ልውሰድ በዚያም አገር እጎበኛለሁ ብዬው በስንት መከራ ፈቅዶልኝ ነበር የሄድነው። እነ ፋሲካንም አገኘናቸው።

(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)

---

## <u>አንድ ጥያቄ አለኝ</u>! (ከጳውሎስ ኞኞ)

(በዚህ ዕትም ዕውቁ ጋዜጠኛ በ1960ዎቹ ዓ.ም አንድ ጥያቄ አለኝ በሚለው አምዱ ከአንባቢዎቹ ለቀረቡለት ጥያቄዎች የሰጠውን መልስ በማጠናከር አቅርበንላችኋል።)

* ከአንዲት ልጅ ጋር ተዋደናል። እንዳንጋባ ሃይማኖታችን የተለያየ በመሆኑ እምቢ አለች። በኃይማኖት የተለያየ ሰው እንዳይጋባ የሚከለክል ሕግ አለ? በፍቅር የሚዋኝ - ከአሥመራ

● ለነገሩ የሚከለክል የለም። አንተ ግን ኋላ ማጠፊያው እንዳያጥርህ።

* * *

* በመንገድም ሆነ በማንኛውም ቦታ ሲያዩኝ ሴቶች ያደንቁኛል። ምን ይሻለኛል?

አዘገ አድማሱ

● ምናልባት ምን ዓይነት አስቀያሚ ነው እያሉ ይሆናልና የሚያደንቁህ። ራስህን አታኩራራ።

* * *

* እባካችሁ በሬና መሬት የሚሰጥ አጠያይቁልኝ። እርሻ መግባት እፈልጋለሁ። ከተማው ሰለቸኝ።

ተስፋዬ አብርሃ

● ሰዎች ካላችሁ ስጡትና ይረስላችሁ።

* * *

*ከልጅነቴ ጀምሮ ትዳር እጠላለሁ። ለወደፊቱም ፍላጎት የለኝም። ምን አስተያየት አለህ? መካሻ -

● ነገሩ ተገላግለሃል። ግን ጤነኛ ነህ?

* * *

* የሚስት ዕድሜ ከባል የበለጠ ቢሆን በጋብቻ ላይ የሚያመጣው ክፋት ምንድነው?

● የወጥና የሴት በሰል ያለ ደግ ነው ሲባል አልሰማህም? ምራቅዋን ዋጥ ያደረገች ሴት እንዲያውም ለትዳር ጥሩ ናት።

* * *

* አንድ ነገር ይገርመኛል። ሰው እንዴት የልጁን እኩያ ያገባል?

● ነውር የማያውቅ ነውረኛ በየቤቱ ብዙ አለ።

* * *

* በወላጆቼ ግፊት ቀለበት አድርጌያለሁ። እጮኛዬን ግን እጠላዋለሁ። ምን ትመክረኛለህ? ጓደኞቼም አልወደዱልኝም።

● አጎብጓቢውን ሁሉ ተይውና ከዕጮኛሽ ለመግባባት ሞክሪ።

* * *

* በራሴ ጥፋት ሚስቴን ከፈታሁ ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ሚስት ለማግባት ሞክሬ አልሆነልኝም። የድሮ ሚስቴ አልታረቀኝ አለች። ሌሎችም ወሬውን ሰምተው እምቢ አሉኝ። እንዴት ልሁን?

ሠራዊቱ ተሸመ - ከደብረዘይት

● ጅብ የማያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል ማለትን አልሰማህም? ለምን ወደማያውቁህ አገር ብቅ አትልም?

* * *

* በውጭ አገር ያሉ አበሻ ወንዶች ፀጉራቸውን የሚያጎፍሩት ወደው አይደለም። ምክንያቱም የእነርሱን ፀጉር ለመቁረጥ ቁራጮቹ ስለሚጠየ<u>ፍቻ</u>ቸው ነው ይላሉ እውነት ነው?

ሌጣ ገለቱ

● ውሸት ነው። እንደአቅማቸው የሚቆርጧቸው ድሆች ቆራጮች አሉ።

* * *

* ይህ ዘመን ለወንዶች ጥሩ ነው ይባላል። እውነት ነው?

ብርሃኑ መንግስቱ

● ባለፈውም ቢሆን ወንድ ረከሶ በጨው አልተለወጠም። ለሞላለት ይሞላለታል። ለጎደለበትም ይጎድልበታል።

* * *

* ስራዬ ከባድ መኪና መንዳት ነው። የምመላለሰውም ቦረና ነገሌ ነው። ጎንደር አንዲት ልጅ አይቼ ፍቅር ያዘኝ። ከቦረና ጎንደር ልቤ ሲመላለስ ያድራል። በፍቅር ላበደ መድሃኒቱ ምንድነው?

ሙሉጌታ - ከነገሌ ቦረና

● የአንተ ማበድ አንሶ መኪናውን አሳብደህ ገደል እንዳትገባ። መድሃኒቱ ሸማግሌ ልከህ ዳሩልኝ ማለት ነው።

* * *

* አይነአፋር ነኝ። ዕድሜዬ እየገፋ ሄደ። እንዴት የኑሮ ጓደኛ ማግኘት እችላለሁ?

ከ . በ - አሰበ ተፈሪ

● ለሀገር ሽማግሌዎች አማክር። እነሱ ይፈልጉልሀ! ብቻ አንዲቱን አይን አውጣ እንዳይጥሉብህ።

* * *

* ጎፈሬ ማሳደግ ምን ነውር አለበት?

ደገፉ ፋንቴ

● እኔማ ምንም ነውር የለበትም ካልኩ ቆይቻለሁ። የራሰ-በራዎቹን ቅናት ከቻልክ ሞክር።

* * *

* ወላጆቼ ለአንድ ሰውዬ ሰጥተውኝ እርሱን ካላገባሽ እንክድሻለን ይሉኛል። እርሱም እጄን ጠምዝዞ ሊያገባኝ ይፈልጋል። ምን ባደርግ ይሻለኛል?

ወ/ት አስቴር . . .

● እስቲ ቀስ እያልሽ ወላጆችሽን በሰው አስመክሪ። እባካችሁ ወንዶች ሴቶች እናገባችሁም ብለው እምቢ ሲሏችሁ እያስለቀሳችሁ አታግቡ። እያለቃቀሳችሁም አታስቸግሩአቸው። ካልተፈቃቀዱ ጋብቻ ምን ያደርጋል?

* * *

* በስራ ምክንያት ከጓደኛዬ ጋር ብንለያይ እኔ የምወዳትን ልጅ አገባት። ምን ትመክረኛለህ?

ካህሳይ ወልዱ - ከድሬዳዋ

● ከድሮውም ቢሆን ጥሩ ጓደኛ አልነበረህም። እግዚአብሔር በምትኳ እስኪሰጥህ ድረስ አርፈህ ስራህን ስራ። የድርሻህን አታጣም።

* * *

* ልጃገረድ እንዳላገባ እንደምታውቀው ጣጣው ብዙ ነው። የኑሮ ጓደኛ እንዴት ላግኝ?

ብርሃኑ ግዛው

● ዳረ-ገብ ጋለሞታዋን ሞክር።

* * *

* አንዳንድ ሴቶች ባል ሳያገቡ የሚወልዱ አሉ። እነዚህ ሴቶች ለምንድነው ወ/ት የሚባሉት?

ብሩ ገመዳ

● ወይዘሪትነቱ ባል ላለማግባታቸው እንጂ የሌላ መታወቂያ አይደለም። ባል ካላገቡ ወይም ካልመለኮሱ መቶም ዓመት ቢሞላቸው ወይዘሪት ይባላሉ።

* * *

* ጥርሶቼ ስለገጠጡ ጓደኞቼ እያበሸቁ አስቸገሩኝ። ምን ይሻለኛል?

ሠለሞን ንጋቱ

● ከጥርስ ሐኪም ዘንድ ሂድና ገጣጣህን ያስተካክሉልሃል።

* * *

* ቆለኛዋን አግብቼ ሙጃሌዋ አላስኖር አለኝ። ምን ላድርጋት?

ዘውዱ

● ከመድሃኒት ቤት ሂድና መድሃኒት ግዛላት።

* * *

* ጓደኛዬ የሰው ሚስት ማባለግ ይወዳል። ብመክረውም እምቢ አለኝ። አንዴም ሊገሉት ሲሉ አመለጠ። ምን ትለዋለህ?

ወንድ ወሰን ወልደኪዳን

● አንዳንድ ወንዶች ባል ያሳመራትን ሴት ይወዳሉ። ጓደኛህ ይህን መጥፎ ጠባዩን ቢተው ይተው። ያለበለዚያ አንድ ቀን በዱላ እየነረቱ ይመክሩታል።

* * *

* ወንድና ሴት ሲጋቡ ሁሉንም ወጪ የሚችለው ወንዱ ብቻ ነው። ጥቅሙም የጋራ ሲሆን ወንዱ ብቻ ለምን ይጎዳል?

ኢየሩሳሌም - ከአሰበ ተፈሪ

● አዝና የምታገዝ ብትገኝማ አይጠላም። ሴቶቹ ቀሚሳችሁን እንኳ ብትችሉ ምናለበት?

* * *

* ወላጆቼ አንዲት ገረባ ከአገር ቤት አጭተውልኝ እርሷን ካላገባህ እንረግምሃለን ይሉኛል። ልረገም ወይስ የማንንም ገረባ አምጥቼ ስቋሰል ልኑር?

ዳኜ መንግስቱ - ከናዝሬት

● የምታስተዳድርበት ካለህ አግባና ገረባህን ታሰለጥናለህ።

* * *

* በወንድ እያስመሰልን ለብዙ ልጃገረዶች የፍቅር ደብዳቤ እየፃፍን ስንልክላቸው ማን እንደሆነ እንኳ ሳያውቁ የእሺታ መልስ ሰጡ። ምን ትላቸዋለህ?

እነ ብዙነሽ - ከዳግማዊ ምኒሊክ ት/ቤት

● ልበ-ቢሶች እላቸዋለሁ። እንዴት ያላዩትን ሰው ወደድኩህ ይባላል?

* * *

* 13,140 ሚስቶች የነበሩትን ሰው ታሪክ አነበብኩ። እኔም የወደፊት ዕቅዴ ይኸው ነው። ምን አስተያየት አለህ?

ዘውዴ - ከአርባምንጭ

● ምናለ እንደአቅምህ ብታልም? እንኳን 13,000 ሚስቶች ሶስቱንም በአንድ ጊዜ ማኖር አትችልምና ህልምህን እርሳው።

# ፓለቲካና ባላገር

ከሂርጳሣ አንዱአለም (ከአለፈው የቀጠለ)

የመጨረሻው መጨረሻ እየተቃረበ ሲሄድ መንግስትም ወያኔም አልተመቻቸውም። ባላገርም አልደላውም። በመንግሥት በኩል የሰራዊት ምልመላውና ሥልጠናው መልክ የያዘ ይመስልና ባልታሰበ ወቅት ደግሞ ፍርክርክ ብሎ የእምቧይ ካብ እየሆነ ተቸግሯል። ወያኔ ደግሞ በያዘቻቸው አካባቢዎች ሕዝቡ ገምቶ፣ አይቶ በድርበቡ ሆኖባት እንደምትፈልገው አልጋለብ ብሏት ተቸግራለች። ባላገር በእነዚህ ሁለት ዝሆኖች መሃል አጣብቂኝ ገብቶ ይረጋገጣል። ወያኔ እርስ በእርሱ አቆላልፋው እንደበቱ ታስሯል።

አንድ ምሽት ወያኔ በያዘቻቸው የጎንደር አውራጃዎች በደብረታቦር አካባቢ በአንዲት አነስተኛ የወረዳ ከተማ ውስጥ ከታወቀ መሸታ ቤት የአገሩ ባላገር ተሰብስቦ አረቄ ይጠጣል። ያወካል። ስለወያኔ ስለመንግሥት፣ ስለጦርነቱ፣ ስለግዳዩ፣ ስለምርኮው፣ ስለወንድነት፣ ስለጀግንነት፣ ስለፈሪነት፣ ስለሽሽት ያወራል። እያነሣ ይጥላል። ጨዋታው ተሟሙቆ ከአረቄውም ገፋ እየደረገ ሲሄድ አንዳንዱን ሽነጥ አደረገው። አንደኛው ብድግ አለና:-

አረቄ ጠጥቶ ትን ብሎታል አሉ፣
ትን ይበለኝ እኔን ሰውነቴን ሁሉ።
አረቄ ጠጥቶ አረቄ ነው ሽታው፣
ይታመማል እንጂ ሰው እንደበሽታው፣
የምን ፍንጥር ፍንጥር
ግንፍል ግንፍል ነው።"

ሲል እዚያ የተሰበሰበውን ባላገር ብሶተኛ ሁሉ በነገር ወጋ ጠቅ አድርጎ ይቀመጣል።

"አንተ ወንዱ ይህን ያልክ ሴቲቱ እንግዲያ ምን ትበል? ሲል መለሰ ሌላው በማሽሟጠጥ።

"ሴቲቱማ የምትለውንማ ልንገርህ እኔው!።"

"በል እማ! ንገረኝ።"

"አንተም ሴት እኔም ሴት አለችው ወዳጁ፣ አንዲት ሰባራ ብረት ብታጣበት ከእጁ። ነዋ የምትለው ሽንጧን አሳምራ"

"የሞተ ዕለት ምን ብላ ልታለቅስ? ባሌ! ባሌ! ወንድሜ! ወንድሜ! ልትል ወይስ እቴ እቴ ልትል?

"የሞተ ዕለትማ:-
"ትላንትም ተጮኸ፣
ሰልስትም ተጮኸ።
ባደምጠው ባደምጠው፣
ድምጡ የሴት ነው፣
ወንዱን በክትቻ ይዘውት ሂደው።
ምን የታደለ ነው፣ ምን የተማረ ሰው፣
አምናና ካቻምና ቀድሞ የሞተ ሰው።
ቆፋሪ ሳያጣ አፈር ሳያንሰው።

እያለች ሙሾ ታወርድለታለቻ!" አለ የለበጣ ሳቅ እያንከተከተው።

"ሴቲቱ አይደለች ረግጣ የምትገዛህ!" አለ የመጀመሪያው ባላገር በእጁ የወያኔ ሴት ታጋዮችን ምልክት እያሳየው። እንዲህ አንድ ሁለት ሲባል ንትርኩ ከረረና የአረቄውም ሞቅታ ተጨማምሮበት ሽለላና ፉከራ ተጀመረ።

አንደኛው ባላገር ሞቅ ብሎት ኖሮ:-

"የወንዱን ጠመንጃ ሴቲቱ ያዘችው፣
ኋላ ሲቸግራት ሽጣ ካልበላችው።
በወንዶች አውድማ አተላ አትድፉበት፣
ረመጥ አይጠፋም ፍም እነበረበት።
ጦር መጣ ይሉኛል እኔ ምን ቸገረኝ፣
ጦር መጣ ይሉኛል ቢመጣም ግድ የለኝ፣
እናቴም ልጅ የላት እኔም ወንድም የለኝ።
ካቻምናን አየነው፣
አምናንም አየነው፣
አርሰንም አየነው፣
ለፍተንም አየነው፣
ተደክሞም መና ነው ተለፍቶም ያው መና፣
ትዳሬም አልቀና እየጎፈነነኝ፣
ቻልአርገው ይሉኛል ቢብስ ምን ሊመጣብኝ።
ጀግና ይሙት ጀግና ይሙት፣
ፈሪ ይኑር ቢሻው፣
አተላ መሸከም ይችላል ትከሻው።

እያለ እየተንቆራጠጠ ፎክሮ ተቀመጠ።

የወያኔ ነገር ሆድ ሆዱን የበላው ጎረምሣ በተራ በተራ እየተነሣ ሽለላውንና ቀረርቶውን ያቀልጠው ጀመር። የእስከዛሬውን ታግሶ አንገቱን ደፍቶ የኖረ ባላገር ዛሬ ደርሶ የመረረው የቆረጠ ይመስል 'እምቢ አሻፈረኝ' 'ጥራኝ ጫካው' "ጥራኝ ዱሩ" ማለት ጀመረ።

አላቅራራም ብዬ መሃላ ነበረብኝ፣
አንጎራጉራለሁ እየጎደለብኝ።
ወይ አገሬ ዱሩ ወይ አይ አገሬ ጫካው፣
አጋሙ ግራሩ ቆንጥሩ ውልክፋው፣
አታሳድርም ወይ አንድ ሰው የከፋው።
ነካካቸው እስቲ
ነካካቸው አትስጣቸው ጤና፣
ምንጊዜም ደህና ሰው አልተባልንምና።
እንሂድ እንሂድ ሄደን እንሞክረው፣
ለወያኔና ለጃርት ይበቃል አንድ ሰው።
አትንኳት ጎጆዬን አትነኳኳት
ከአፈር ላይ ቁማለች፣
ትልቁን አዳራሽ ይዛው ትወድቃለች።
እልከኛው ጎበዝ እልክ የወረሰው፣
የሰራውን ጎጆ መልሶ አፈረሰው።
የቀንጃ በሬውን አጋድሞ አረደው፣
ገልባችሁ ማየት ከእንግዲህ ምን ቀረው።
እኛስ እነማነን እናንተስ ማናችሁ?
ውረዱ እንውረድ ይታያል ልካችሁ።
በዚያ ቁልቁለት በዚያ ድፋታ፣

አባሮ ገዳይ ሎሌና ጌታ።
አንተ ደፋሩ መድፈር አዋቂው፣
ፈሪና ደፋር አደባላቂው።
እምቢ በል እንጂ እምቢ ነው መልካም፣
እንበሣ ጋማውን ዝንብ አያስነካም።
በማለት ከወዲያ ወዲህ እየተንጎራደደ፣
እየተቁነጠነጠ ፉከራውን አስነካው።

የአረቄው ሞቅታና የጎረምሣው ሁካታ ያልጣመው አንዳንዱ ባላገር ሽንቱን የሚሸና እየመሰለ ሹልክ እያለ ወጣ። አንዳንዱም ይህ የአረቄ ላይ ፉከራና ሽለላ ያልታሰበ ዳፋ እንደሚያመጣ አውቆ:-

ተው በሉት ይህን ሰው ተው በሉት ይሞታል፣
የተያዘው ክላሽ አገዳ መስሎታል።
የተሳለ ቢላዋ ሳያኖረው ከቤቱ፣
እንደወንዶቹ ሳይሰናዱ፣
ኧረግ እነቡከን እነዝርጥ ሆዱ፣
ከአረቄ ቤት ምን ቢንጎራደዱ፣
ኋላ ይቸግራል ያገሩ ጎዳና
ሲጠፋው መንገዱ፣
ከዚያ ከበረሃው ከሽመሉ ለምለም፣
እቀፊኝ ደግፊኝ አንተርሽኝ የለም።

ሲል እንደመርከርም እንደመምከርም ብሎ ተመልሶ ተቀመጠ። ይህን የእርሱን ስጋት ያልተረዳው፣ ነገር ነገሩን ያላስተዋለው ሌላው ደግሞ ከፍርሃት ቆጠረበት። ፍንጥር ብሎ ተነሣና ያዙኝ ልቀቁኝ እያለ እየተንተከተከ ይፎክር ገባ።

. . . ዘራፍ አካኪ ዘራፍ . . . አካኪ ዘራፍ
ምን ይላል ይህ ሰው ወላዋይ ሰውዬ እየወላወለ፣
ጠላቱን ሰደደው ዛሬ ነገ እያለ፣
የቀለሳት ጎጆው እንዲህ ከቆጨችው፣
ሚስቱና ትዳሩ እንዲህ ከቆጨችው፣
እርሱ ይኑር በአገር
አተላ መሸከም ይችላል ትከሻው።
ዓይኑን ዓይኔ ልቡን ልቤ ሲያውቀው፣
ኧረ! ከምኔው ነው እንዲህ የተዝረጠረጠው።
ውረድ እንውረድ ከቁልቁለቱ፣
የሞተው ይሙት ታልቅስ እናቱ።
የሰውዬው ልጅ የዚያ የከፋ ሰው፣
በጥቁር አፈር የተለወሰው፣
ከኋላ ደርሶ መቀነቻውን፣
ሲዞር መስቀሉን መሃል ግንባሩን፣
ከጥይት ጥይት መርጠ ቀርቃሪ፣
በአጭር ምንሽር በደም ነካሪ፣
ጭር ባለው ሌሊት ጎራ አሸባሪ።
ዘራፍ አካኪ ዘራፍ አካኪ ዘራፍ፣
ሄደ ንቡ ሄደ ንቡ መሄድ የለመደ፣
ድንጉሉ ቀረ እንጂ ቤቱን የወደደ፣
ሂድ ሲሉት ካልሄደ፣ ና ሲሉት ካልመጣ፣
ሚሽቱን ስደዱለት እጁን ይዛው ትምጣ።
ዘራፍ አካኪ ዘራፍ አካኪ እራፍ አካኪ
ዘራፍ የዘራፍ ወንድም
እንበለው እንጂ እንሽሽ አይወድም።
ዱብ ዱብ ባይ እንደበረዶ፣
ከልጅነቱ በረሃ ለምዶ።
መታጠቅ ምንሽር ነው፣
መታጠቅ ቁምጣ ነው፣
መግደል በዲሞትፈር በአሥራ ሁለት ጎራሽ፣
ፈሪ ተጨንቆ አገር ሲያበላሽ።
ፈሪና ወንዱ ቢመዛዘኑ፣
ፈሪ በለጠ ከነቅዘኑ፣
ፈሪ ፈሪና ጉድባ ቢተኛ፣
ጆሮውን በላው የአይጥ ቀበኛ።
ዘራፍ አካኪ ዘራፍ አካኪ ዘራፍ
የሌለ ነገር በአገር በወንዛችን፣
ወንዱ ልጅ ፈርቶ ቆሟል ደጃችን።
ሂዱ ንገሩት ሱሪውን ያውልቅ፣
ቀሚስ ተሰርቶ ንገሩት ያጥልቅ፣
ከሚስቱ ጉያ ሄዶ እንዲወሸቅ።
ወንዱ ልጅ እንዲህ እርብትብት ሲሆን፣
ወንዱ ልጅ እንዲህ ልበ-ድንጉጥ ሲሆን፣
ለአገሩም አይበጅ ለቤቱም አይሆን።

እያለ መቆሚያ ስፍራ እስኪጠበው ድረስ እየተቁነጠነጠ ፎከረ። ትንሽም ሞቅ ብሎታል። ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል ሆነና እዚያ የተሰበሰበው ጎረምሣ ሁሉ በእግሩ አውራጣት መሬቱን እየቆፈረ በእጁ ነገር እየጠበጠበ ተካከዘ። በዚሁ ወደ ዱር እንጂ ወደ ቀዬው የማይመለስ መሰለ።

ነገር ግን በመካከሉ "ተው ጎበዝ ይቅርባችሁ" ያለው ባላገር ሁኔታው አሁንም አልጣመውም። መሸታ ቤት አረቄ እየጨለጡ በአረቄ ሞቅታ እንዲህ ያዙኝ ልቀቁኝ የሚባለውን ፉከራ አልወደደውም። ባይሆን ተሰናድቶ፣ መሄጃ መውረጃውን መድረሻውን አጥንቶ መክሮ ነው እንጂ እንዲያው በባዶ እጅ መሸታ ላይ ፍጥጥ ፍጥጥ ማለቱ አላማረውም። ጎምለል ብሎ ብድግ አለና ዙሪያውን እንደመገርመም እንደመቃኘት አደረገ። ቆፈነነው። ግንባሩን ቁጥርጥር አደረገና

ዘራፍ አካኪ ዘራፍ አካኪ ዘራፍ የዘራፍ ወንድም፣
ግንባሬ ኩስኩስት ቁመቱ አጣሬ፣
በአልበን በጓንዴ የሚያንጠራራ።
አልሞ የማይስት የቀኤው ጌታ፣
ጠላቱን ገጥሞ ድል የሚመታ።
መች እንዲህ ሆነና ከአገር ሲሄዱ፣
መች እንዲህ ሆነና የአባትን አገር ለቀው ሲሄዱ፣
መች እንዲህ ሆነና ከቁልቁለቱ ከአምባው ሲወርዱ።
ሻኛማ በሬ እየጎመዱ፣
እልፍኝ ከአዳራሽ እያነደዱ።
ዘራፍ አካኪ ዘራፍ አካኪ ዘራፍ፣
ከነኩፍኩፌት ጨዋታ ለምዶ፣
ከነጎራዲት ጨዋታ ለምዶ፣
የጎራውን ዱር ሳያየው ወርዶ፣
ወንዱን ወንድ ናቀው ወይ ነዶ ወይ ነዶ።
እንኳን በክላሽ ጥይት በቃመው፣
በቆላ ሽመል ቢለመጥጠው፣
ቅራሪው ወጣ የቀላወጠው፣
አረቄው ወጣ ቁም የጨለጠው።

በወይራ ሽመል ይዞ ቢለምጠው፣
ድንቹ ወጣ ሳይልጥ የዋጠው።
አሁን ምንድነው እርጭ እርጩ፣
የፍልፈል ታህል አፈር ሳይረጩ፣
ዘራፍ አካኪ ዘራፍ አካኪ ዘራፍ፣
እጅ ይጡም እጅ ይጡም፣
አፍ ይጡም አፍ ይጡም፣
ሰው በሰው ይስቃል የራሱን አያውቅም።
መምከር ከወንድ ነው፣
መምከር ከወንድም ነው ማማትም ሜዳ ላይ፣
ባዕድና ፈሪ ያጋልጣል ግም ነው።

እያለ ተውተረተረ። ሁኔታው ከፉከራ ይልቅ የእንጉርጉሮ ዓይነት ነበር። እርሱ ገና ሳይጨርስ አንድ ሌላ ባላገር ተስፈንጥሮ ተነሣና "ዘራፍ አካኪ ዘራፍ" በማለት ፉከራ ጀመረ። የመጀመሪያው ባላገር እንደቆመ ከእግር እስከራሱ ገላመጠውና:-

"ምን ይላል ይሄ ልጋጋም! ተው እረፍ አንተ ሰው!" አለ ሊፎክር በተነሳው ባላገር ላይ አይኖቹን እያጉረጠረጠ። "እረፍ ብዬሃለሁ አንተ ሰው! እርፍህ አረቄህን እማትጠጣ? ሙያ መስሎሃል እንዴ አረቄ ላይ መፎከር። ከድሃ ቤት ኅመን የተቀቀለ ዕለት ሲዘፈን ይታደራል አሉ።" ሲል በመቆጣት የተጋጋለውን ፉከራና ቀረርቶ ፀጥ አሰኘው። ከየባላገሩ መሃል ለኮር ምልምልነት የተመለመለው፣ ለታጣቂነት ደጅ የሚጠናው ወሬኛና አሳባቂ እንኳን ይህቺን ያህል ፍንጭ አግኝቶ በመላ ፈስ ዳለቻ ነው ብሎ ያሳብቅ ጀምሯል። ይህኛው ባላገር ደህና ጠርጥሯል። አረቄያቸውን ጨርሰው ሲወጡ እንደፈራው እንደጠረጠረው ታጣፊ ክላሽ የያዙ የኮር ምልምሎችና ወያኔዎች ከበራፉ ላይ ጠብቀው ሰብስበው ወሰዷቸው። ገሚሱን ወደባዶ ስምንት ገሚሶቹን ወደ ደንቆሮ ዋሻ ይዘዋቸው ነጎዱ። ወያኔ በኮር ምልምሎቿ አማካይነት የምትጠረጥረውን ባላገር ሁሉ እየለቀመች እግር ከወርች ትጠፍር ጀመር። ይህቺን ያየ ባላገር:-

ጓደኛዬ ብዬ ሚስጥሬን ብነግረው፣
የእኔን ሰምቶ ሰምቶ ለዚያኛው ነገረው።
አቻምና በበጋው የተደናገረኝ፣
ውሻ ራቴን በልቶ ጦሜን አሳደረኝ።
አንበሣው ተኝቶ ጊደር ሸናችበት፣

ከእንዴት ያለው ጊዜ እንዴት ደረስንበት። በማለት ትዝብቱን በግጥም በዜማ አንጎራጎረ። ባላገር የወያኔን ኮተት ተሸክሞ፣ አጋሰሷን ነድቶ፣ መንገድ መርቶ መልካውን አሳይቶ ያልደገፈውን ያልረዳውን ያህል አሁን ከመሃል ከመሃሉ ቀና የሚለውን ይዛ ጥብስ ማድረግ ጀመረች። ባላገርም:-

እኛው ራሳችን ጎትተን ጎትተን፣
ብርሃኑን አጥፍተው ጨለማ ከተቱን።
ቀን ያልፋል ብለን ብንጠብቅ ብንጠብቅ፣
እንኳንስ ሊያልፍ ጨለማ ነው ጥቅጥቅ።
መያዙንስ ይያዝ ድንቅ አድርጎ ይዞታል፣
ገበሬውን አስሮ ምን ያደርግለታል?
እንግዲህ ኢሕአዴግ ተመከር ተመከር፣
ውሎ ያደረ እንደሁ ማጠፊያው እንዳያጥር።
እንግዲህ ኢሕአዴግ በርታ ተበራታ፣
አበሳህ እንዳይዘልቅ የማታ የማታ።

እያለ ይመክርና ያስጠነቅቅ ጀመር። ቀን እስኪያልፍ መላ የሚሆነውን እየተመካከረ በዘፈንና በግጥም እያስመሰለ ከአባይ ማዶ በመንግስት ቁጥጥር ስር ላለው ባላገር ጭምር መልዕክት መቀባበል ያዘ።

እስቲ ኅመን ዝሩ ኅመን የጋራ ነው፣
ሽምብራ ከዘሩ ጠርጣሪው ብዙ ነው።
ወይ ዘንድሮ ስትይ ወይ ትያለሽ ከርሞ፣
ከእኔ የሚብሰው ይመጣና ደግሞ።
የሰው ሁሉ አካሉ አድጎ አድጎ ያበቃል፣
የእኔስ ጥቃት ጉድ ነው እንደገና ያድጋል።
እኔም አልናደድ ሰው በደለኝ ብዬ፣
ቅን ፈራጅ አምላኬ ሳለ ፈጣሪዬ።
መጨነቅ መጠበብ ለፍቅር ብቻ ነው፣
ለጠሉት መድኃኒት ተወት ማድረግ ነው።

ሲል ተመካከረ።

* * *

በመንግሥት ይዞታ ስር ባሉት የጎጃም፣ የጎንደር፣ የደቡብ ወሎና የሰሜን ሸዋ አውራጃዎች ውስጥ የሚሊሽያ ሰራዊት ስልጠናው ተሟሙቋል። ባህርዳር በጭንቀት ተውጣለች። ጎንደር ጨፍጎጓታል። ወሎ እንቅልፍ አጥቷል። የሰሜን ሸዋው መንዜ የባሩድ ሽታ አፍኖታል። በየቤቱ ሁሉም የበኩሉን መሰናዶ ይዟል። ከተሜው አባወራ ልጅ ቤተሰብ ያለው ለክፉ ቀን የሚሆን መሰናዶ አድርጓል። እህል አስፈጭቷል። ለመጠጥ የሚሆን ውኃ በበርሜል በጀሪካን አስቀድቷል። ሻማና ክብሪት በፖኮ ተገዝቷል። ማገዶ አስፈልጦ አስከምሯል። በየስርቻው በየመሶብ ቤቱ ደግሞ የጎጃምኛው የትግሪኛው ዘፈን ቀልጧል።

አዲስ አበባ ብዙም ምቾት አልጎደለባትም። የጎጃምን ጭንቀት፣ የወሎን ስጋት የጎንደርን የጎን ውጋት አትሰማም። አታይም። በየእዝማሪ ቤቱና በየሆቴል ቤቱ እስከ ንጋት ድረስ ከበሮ ይደለቃል፣ ይጨፈራል። የአዲስ አበባ ጎበዝ ጥንድ ጥንድ እየሆነ ዳንኪራና ጭፈራውን ያስነካዋል። ከወሎ፣ ከትግራይ፣ ከጎንደር ተፈናቃይ ጋር ተመሳስላ አዲስ አበባን ያጥለቀለቀችው ወያኔ ጠርሙስ ውስኪ አስወርዳ "ሣሣይ ላሎይ! አሃይላሎየ" ስትል ታነጋለች። ብዙ የአዲስ አበባ ሰው የወያኔ ጉዳዩ ቤተመንግሥት ካሉት ሹማምንትና መኳንንት ጋር እንጂ እርሱን የማይመለከት አድርጎ ቆጥሮታል። የመንግሥት ሹማምንት ፋታ በሌለው ስብሰባ በቋፍ ተይዘዋል። ሥራ በዝቷል። ውጥረት ነው። ወዲህ ደግሞ ወደ ቦሌ ግድም የጀመሩትን ቤተመንግሥት የሚመስሉ መኖሪያ ቤታቸውን ለማስጨረስ ይጣደፋሉ። ሚስት፣ ልጅ፣ ቤተሰብ ወደ ውጭ አገር ለመስደድ ቶሎ ለማሻገር ይጣደፋሉ።

መንግሥት በደሴ መስመር ወልዲያን ለቆ ደሴ ላይ ሰፍሯል። በጎጃም መስመር አባይን ተሻግሮ ባህር ዳር አባይ ድልድዩ ላይ የሞት ሽረት ውጊያ ለማድረግ የቆረጠ ይመስላል። የወልዲያ ሹማምንትና የመንግሥት ሠራተኞች ደሴ ላይ ሆነው፤ የደብረታቦር ደግሞ ባሕር ዳር ላይ ከትመው በቅርብ ርቀት የክልላቸውን አስተዳደራዊ ሥራ እንዲሰሩ ተብለዋል። የግብርና ልማት ሠራተኞች ሳይቀሩ የመንግሥትን ጦር እየተከተሉ ገበሬውን በልማት ሥራ እንዲያስተባብሩ ታዘዋል። አገሬው ባላገር ይህቺን የመንግሥት ብልጠት እየታዘበ:-

እንዴት ያለ ነገር ምኑም የማይለይ፣
መሬት ከለቀቁ ወዲያ መንግሥት አለ ወይ?

እያለ በመንግሥት ሹሞች ላይ ያሾፋል።

የክፍለሀገሩ የመንግሥት ባለሥልጣኖችና የመንግሥት ሹማምንት ውስጥ ውስጡን ተባልተው ለዓይን እይታ እንኳ የማይፈላለጉ እየሆኑ መጥተዋል። የፓርቲ ሹሞች በአንደኛ ፀሐፊው መሪነት የርዕዮተዓለም ኃላፊው፣ የኢኮኖሚ ኃላፊ፣ የሕዝባዊ ድርጅቶች ኃላፊ ወዘተ ወዘተ አንድ ጎራ ፈጥረው በመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ ካሉት ባለሥልጣኖች ጋር ተፋጠዋል። የመንግስት ሹማምንት በዋና አስተዳዳሪው መሪነት ቀዳሚ ምክትል አስተዳዳሪውን፣ ምክትል አስተዳዳሪውን የሸንጎ ፀሐፊውንና የየሚኒስቴር ቅርንጫፍ የቢሮ ኃላፊዎችን ይዞ ሌላ ጎራ ፈጥሮ የፓርቲ ሹማምንቶችን ለዓይን ማየት አይፈልግም። በመንግሥት ቢሮዎች ውስጥ የሚገኙት ሹማምንት የፓርቲ ባለሥልጣኖችን የፖለቲካ ታማኝነታቸው የተረጋገጠላቸው "የመሐይም ስብስብ" አድርጎ ይቆጥራቸዋል። የፓርቲ ሹማምንት ደግሞ ብቀጥንም ጠጅ ነኝ ዓይነት የመንግሥት ባለሥልጣናቱን የቢሮክራሲ ጥርቅም አድርገው ይቆጥሩታል። ለፓርቲውና ለሶሻሊስት ስርዓት ታማኝነቱ ያልተረጋገጠው ይሄ የቢሮክራቶች ጥርቅም እነርሱ በሚሰጡት ጥብቅ መመሪያና ቁጥጥር ስራውን ማከናወን አለበት ብለው ያምናሉ። የመመሪያና የትዕዛዝ ዝርዝር ያዥጎደጉዱሉ። ፍጥጫውና ሽኩቻው በመሃላቸው እየከረረ መጥቷል። በአንዳንድ ቦታ ይህ የፓርቲና የመንግሥት ሹማምንት ሽኩቻ በቁርኝትና በቲፎዞ እስከአውራጃ እስከወረዳ ድረስ ይደርሳል።

በወታደራዊ ክፍሎችም ውስጥ እንዲሁ የከረረ እተካራና ሽኩቻ እየተብላላ መጥቶ የሰራዊቱን የውጊያና የዕዝ መስመሩን ግራ አጋብቶ አፍረክርኳል። በሰራዊቱ አደረጃጀት ውስጥ ቁልፍ በሆኑት በዋና አዛዡ፣ በፖለቲካ ኃላፊውና በደህንነት ኃላፊው መካከል የከረረ ጥላቻና መናናቅ ማቆጥቆጥ ከጀመረ ሰንብቷል። የዋና አዛዥነቱን ቦታ የሚይዙት በጄኔራልነት ማዕረግ የሚገኙ ከፍተኛ መኮንኖች ሲሆኑ የፖለቲካና የደህንነት ኃላፊዎች ግን ታማኝ የመስመርና የበታች መኮንኖች ናቸው። የዋና አዛዡን ማንኛውንም ዕቅድና እንቅስቃሴ ለማወቅና ለመወሰን ከዋና አዛዡ ያልተናነሰ እኩል ስልጣን አላቸው።

. . . እንግዲህ መንግሥት ይህን በመሰለው ሁኔታ ተተብትቧል። ባላገር ጀርባውን አዙሮበታል። ወዲህ ደግሞ ወያኔ ተፈናቃይ መስላ በየድርጅቶቹ፣ በየመንግሥት መ/ቤቶቹ፣ በየከተማውና በየአገሩ ተሰግስጋለች። ትሰልላለች። ታሰልላለች። የባላገሩን የልብ ምት፣ እየሰለጠነ ያለውን የባላገር ሰራዊት ብቃት፣ በየወታደራዊ ካምፑ ውስጥ ያለውን የመደበኛ ጦር ብዛት፣ የሚጓጓዘውን ሰራዊትና ትጥቅ አቅጣጫ፣ የብሄራዊ ውትድርና ምልምሎችን የሥልጠና ዝግጅት ታጠናለች።

በዚህ ሁሉ ትንቅንቅ መሃል አጣብቂኝ የገባው ባላገር መውጫውን፣ መላቀቂያውን በየደብሩ ይመክር ይዟል። በጎበዝ አለቃ እየተደራጀ የመንግሥት ሹማምንትን "ወይድ" ለማለት ከጅሏል። አልሞት ባይ ተጋዳይ ለመሆን ቆርጧል። ከየአውራጃው የተመለመለው ሚሊሺያ በተዘጋጀለት መጠለያ ገብቶ ሰልፍ ይረግጣል። ዒላማ ይተኩሳል። ክላሺንኮቭ ጠመንጃ፣ አንዳንድ ተኳሽ አብራራው፣ ቢቢሽ (PPCH) መፍታት መግጠም ይማር ጀምሯል። ልጆቻችን ዘምተው እኛ እንቀርም ብለው ከሰራዊቱ አንለይም ያሉ ጉፍጉፍ ያሉ ሽማግሌዎች በማሰልጠኛው ጣቢያ ተኮልኩለው ሲመክሩ፣ ሲዶልቱ ይውላሉ። አገሬው ባላገር ከደብር የተማከረውን፣ ከወሎ ከጎንደር ከሸዋ ባላገር የተቀባበለውን መልዕክት ለሚሊሽያው ያደርሳሉ። የሚሊሽያውን ስጋትና ምክር ደግሞ ለባላገሩ ያደርሳሉ።

ባሎቻቸው፣ ልጆቻቸውና ወንድሞቻቸው የተመለመሉባቸው ሴቶች በአገልግል ፍትፍት ይዘው፣ በጨርቅ ቢጤ በሶና ቆሎ ቋጥረው፣ በአቁማዳ ጭብጦ ተሸክመው በማሠልጠኛው ጣቢያ ከጉብታው ላይ ተኮልኩለዋል። ጠጉራቸው በአጭሩ የተከረከመ፣ አዳፋ ጨርቅ የለበሱ ባዶ እግራቸውን ከወዲያ ወዲህ የሚንከላወሱ ሴቶች ከመስኩ ላይ ሰልፍ ከሚረግጠው ሰራዊት መካከል የየራሳቸውን ሰው ለማየት እንባ ያቀረዘዙ አይኖቻቸው ይቅበዘበዛሉ። የሠራዊቱ የልምምድ ሰዓት አልቆ እረፍት እስከሚሆንና ተገናኝተው የያዙትን እስኪያቀብሉ ድረስ ከማሠልጠኛ ጣቢያ ፈንጠር ብለው ከጉብታው ላይ ተኮልኩለው ይጠባበቃሉ።

. . . በዚህ መሃል ነበር ባለፈው ዕትም ያጫወትኩዎ የደብረታቦር ግንባር ውሎ ከባላገሩም ከአውራጃ ሹሙም ጆሮ የገባው። የአውራጃ ሹሙ የጦርነቱን አኳኋን ቡናቤት ካገኛቸው ሁለት ባላገሮች ልቅም አድርጎ ሰምቷል። የመንግስት ጦር አመድ በር ግድም ከኋላ ተቆርጦ ወደ ወረታ ማፈግፈጉን አውቋል። ባላገሩም በዘፈን በግጥም እስመስሎ ገበያ ለገበያ፣ በሰው በሰው ተቀባብሎ የደብረታቦርን ግንባር ፍፃሜ በደንብ ሰምቶታል። ወደጀመርነው ጨዋታ ልመልስዎ!

አውራጃ ሹሙ ባላገሮቹን ተሰናብቶ ወደ ማሠልጠኛ ጣቢያው ሲመለስ ሰራዊቱ "እሪምቧ! እሪምቧ! እሪምቧ!" እያለ የሚዘፍነው ዘፈንና ጭፈራ ከርቀት ተሰማው። የመዝናኛ ጊዜ መሆኑን ገምቶ በእርጋታ ወደ ማሠልጠኛው ቀረብ ብሎ ጆሮውን

አቂሞ አዳመጠ። ባላገሩ "እሪምቧ" የሚዘፍን መስሎ የሚባባለውን ልብ አድርጎ ሰማ። የደብረታቦር ግንባር ውሎ ቀድሞ ባላገሩ ጆሮ መድረሱን ተረዳ።

ጎራው ተለብልቦ ይታያል አለቱ፣

የጎበዝ መሄጃው ደረሰ ሰዓቱ።

እየተባለ ከሚዘፈነው ግጥምም የተቀደመ መሆኑን ጠረጠረ። መቀደሙ አበሳጨው። ባላገሩ ውስጥ ውስጡን እንዳች ተንኮል ተመካክሮ መጨረሱን ጠርጥሯል። ይህ የባላገሩ ዱለታና ምክር ምን እንደሆነ አለማወቁ ደግሞ አደጋ እንዳለበት በደንብ ታየው። ከፊቱ የተደቀነው ፈተና ክብደት ተሰማው። ወደማስልጠኛ ጣቢያው ገብቶ የባላገሩን ጭፈራ ካስቆመ በኋላ ወደ ቢሮው አመራ። ከባብዶታል። ልቡ አንዳች ክፉ ነገር ጠርጥሯል። ይህ የባላገር ሰራዊት ሌሊቱን አጥር ገልብጦ የጥበቃ ቀለበቱን ሰብሮ ቢወጣ መመለሻም እንደሌለው በእርሱም ላይ የሚያመጣበትን ዳፋ አሰበ። የአውራጃውን የደህንነት ክፍል አባሎችንና የማሰልጠኛ ጣቢያውን መስተንግዶ ኃላፊ አስጠርቶ ስብሰባ ጀመረ።

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ገደማ በየአውራጃው ሹም ቢሮ አስቸኳይ ስብሰባ ይካሄድ ጀምሯል። አጀንዳ የለም። ውይይት የለም። 'ጓድ' እየተባባሉ መሸነጋገልና መገባበዝ የለም። ሁሉም በየራሱ ነገር በሃሳብ ነጉዷል። ለትንሽ እፍታ ፀጥታ ሆነ። አልፎ አልፎ የአውቶማቲክ ጠመንጃ የተኩስ እሩምታና የሌላም መሳሪያ ተኩስ ይሰማል። ሰሞኑን ገና መሸት ሲል በከተማው ዙሪያ ያለው ባላገር ጥይት እያፈነዳ ፀጥታ ሲነሳ ነው የሚያድረው። ማን? ከማን? እንደሆነ አይለይም ብቻ እንዲሁ ሲተኮስ ያድራል። የአውራጃ ሹሙ ያገኘውን መረጃ በምን መልኩ ለተሰብሳቢዎቹ እንደሚያቀርብ አሰላሰለና ሁሉንም ትኩር ብሎ አያቸው። አካላቸው እንጂ ልባቸው ከእርሱ ጋር እንዳልሆነ ተገነዘበ። ስለደብረታቦር ግንባር የሰማውን ሁሉ እንዳለ መናገሩ ሌላ አደጋ እንዳለው ታሰበው። "የተሰበሰብነው አሳሳቢ በሆነ የአካባቢያችን የፀጥታ ጉዳይ ለመነጋገር ነው አለ።" በልበ ሙሉነትና በባለሥልጣንነት አነጋገር። "እንደምታውቁት አብዮታዊ ሰራዊታችን በየግንባሩ በከፍተኛ ፍልሚያ ላይ ይገኛል። በግንባር የሚካሄደው ጦርነት እንደውጊያው ስልት ወደፊት ገፍቶ የማጥቃት ወደኋላም ተመልሶ የማፈግፈግ ሁኔታ ሊኖር ይችላል። የእኛ ትልቁ ድርሻ የየአካባቢያችንን ፀጥታ ማስጠበቅ ነው። ይኸው እንደምትሰሙት ገና መሸት ከማለቱ አውራጃችን የጦርነት ቀጠና የሆነ ይመስል ባላገሩ ጥይት ሲያፈነዳ፣ ወደ ከተማ አዙሮ ሲተኩስ ያድራል።" በማለት የደብረታቦሩን ግንባር የመንግሥት ሰራዊት የስልት ማፈግፈግ አድርጎ አብራራ። ተጨማሪ፣ ተቃውሞ፣ የተለየ አስተያየት፣ ማብራሪያ ጥያቄ ምንትስ ተባለ። ሁሉም የየበኩሉን ሰነዘረ። አስተያየቶች ተኸኅደጎዱ። የአንዳንዱ ተሰብሳቢ ቀልብ በስብሰባው ላይ ሳይሆን አልፎ አልፎ በሚሰማው ተኩስ ላይ ያረፈ ይመስላል። ከየተኩሱ የመሣሪያውን ዓይነት ለመለየት ጆሮውን አቁሟል።

ዱ . . . ዱ . . . ዱ . . . ዱ
– ይሄ አብራራው ነው።
ዱዱዱዱ . . . ዱዱዱዱ . . . ተረረረረም –
ክላሽንኮቭ አውቶማቲክ
ዱ . . . ዱፍ . . . ዱፍ . . . ዱፍ –
ዲሞትፎር
ጥው . . . ጥው . . . ጥው ጥው . . . ጠ
ጠ ጠ ጠ ጠ ጠው
ቢቢሽ ይላል በልቡ።

"በየምሽት ስለሚሰማው ስለዚህ ተኩስ የደህንነት ክፍሉ ምንድነው የምትሉት?" አለ አውራጃ ሹሙ ወደ ፖሊስ አዛዡ ዞር ብሎ።

"አባሎች አሰማርተናል። ተባባሪ አባሎቻችንንም ከየአካባቢያቸው ያለውን መረጃ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥተናል።" አለ የአውራጃው ፖሊሱ አዛዥ ቆፍጠን ባለ የፖሊስ አነጋገር።

"እስካሁን ካገኛችሁት መረጃ ምን ላይ ደርሳችኋል?"

"ከጠላት ኃይል እንዳልሆነ ደርሰንበታል።"

"ይህን ማለት ብቻውን በቂ አይደለም። ለዚህ ምንድነው ያላችሁ መረጃ?"

"እንዳልኩት መረጃዎቹ ተሰብስበው በመመዘን ላይ ናቸው። ጠቅለል ያለ ሪፖርት እናቀርብበታለን።"

"ጓዶች! ጊዜ የለንም። ፋታ የለንም። ሚስቶቻችሁን ታቅፋችሁ፣ ትራሳችሁን ከፍ አድርጋችሁ ስትተኙ እያደራችሁ መረጃ ማግኘት አይቻልም። ቀን ከሌሊት መስራት ይኖርባችኋል።" አለ የአውራጃ ሹሙ ኩስትርትር ባለ የትዕዛዝ ዓይነት አነጋገር።

"የለም ጓድ! ቀንና ሌሊት እየሰራን ነው። አልተኛንም። ይሄ በየምሽቱ የሚሰማው ተኩስ ከጠላት ኃይል እንዳልሆነ በበቂ ሁኔታ ደርሰንበታል።"

"ኋላ የምንድነው ነው የምትሉት?"

"ሻጭና ገዢ መሣሪያ ለመፈተሽ የሚያደርጉት ተኩስ እንደሆነ ደርሰንበታል።"

"እንዴት?"

"እንደኛ በዚህ አውራጃና በሞላው ጎጃም ከፍተኛ የጦር መሣሪያ ግዥና ሽያጭ እየተካሄደ ነው። ሁለተኛ የተኩሱ ሁኔታ መሸት ሲል ማፈንዳት እንጂ የመልስ ተኩስ የለም።"

"ምን ማለት ነው ይኸ? አገሬው ሸፍቷል ማለት ነው? ለምንድነው ከፍተኛ የጦር መሣሪያ ሽያጭ የሚከናወነው? የሚሸጠው መሳሪያስ ከየት የመጣ ነው?"

"ስለባላገሩ መሸፈት እንኳ የደረሰን መረጃ የለም። ግን በየቀበሌ በየቀበሌው በጎበዝ አለቃ እየተደራጀ ሲማማልና "በማኀተብህ እርጋ" እየተባባለ በየደብሩ ሲመካከር መሰንበቱን አጣርተናል። የሚሸጠው መሣሪያ በአብዛኛው ከግንባር ካፈገፈጉና ከተበተኑ የጦሩ አባላት ላይ የተገኘ ነው። ባላገሩ ሲመቸው በመቀማት ብጨርቃ ጨርቅ በመለወጥም ብዙ የጦር መሣሪያ በእጁ አስገብቷል። ከደብረታቦርና ከጋይንት በኩል በርካታ የጦር መሣሪያ ወደ ጎጃም እየገባ መሆኑንም ደርሰንበታል።"

"በጨርቃ ጨርቅ የተለወጠ ስትል?"

"የተበተኑና ያፈገፈጉ የጦር አባላት ባላገር መንገደኛ መስለው ወደ መሃል አገር ለማለፍ ሲሉ የነፍስ ወከፍ መሣሪያቸውንና ዩኒፎርማቸውን በባላገሩ ጨርቃጨርቅ እየለወጡ ወደ ትውልድ ስፍራቸው እየተመለሱ ናቸው።"

"ጥሩ! በዚህ ላይ የተጠናከረ የመረጃ ስራ ይሰራ። ተጨማሪ የፍተሻ ኬላዎች ማቋቋምና ያሉትንም ማጠናከር ያስፈልጋል። የሚጠረጠሩ መንገደኞችም ቢሆኑ እያስቆማችሁ መፈተሽ ይኖርባችኋል።" ሲል የአውራጃ ሹሙ መመሪያ ሰጠ። የፖሊስ አዛዡም አጀንዳው ላይ በፍጥነት ቃል በቃል አሰፈረው።

"ስለ ሚሊሽያው ሰራዊትስ ምንድነው ያላችሁ መረጃ?"

"ስልጠናው በሚገባ እየተካሄደ ነው። ሰሞኑን የኢላማ አስተኳሾች ስለሚመጡልን የኢላማ ተኩስ እናስተኩሳለን።"

"ሌላስ? ለምሳሌ ጥበቃውን በተመለከተ?"

"የሠራዊቱ ጥበቃ በተጠናከረ ሁኔታ እየተካሄደ ነው።"

"ከዚህ ሌላስ? ሰራዊቱን የሚያሸብሩና ወኔውን የሚሰልቡ ወሬዎች እንዳይሰራጩ ምን እያደረጋችሁ ነው? እነዚህ ሽማግሌዎች በሰልጣኙ ዙሪያ ተኮልኩለው ምንድነው ሲዶልቱ የሚውሉት? ሚሊሽያው ጦር በመዝናኛ ጊዜው፣ በዕረፍት ሰዓቱ፣ በመኝታው ላይ ስለምንድነው የሚያወራው? ስሜቱ ምን ይመስላል? በሰራዊቱ ውስጥ በሚስጢር የተመደቡት ተባባሪ አባሎቻችሁ ምን እየሰሩ ነው? ስንቅ የሚያቀብሉ ሴቶችና አሮጊቶች ለምን በዚህ ሰሞን በዙ? የምግብ መስተንግዶው በቂ አይደለም? ወይስ ሴቶቹ በሚያመጡት ጭብጦና ቆሎ ውስጥ መሳሪያና ጥይት ለሰራዊቱ እያቀበሉ ነው? መጠርጠር ይኖርባችኋል! የደህንነት ስራ እያንዳንዱን ሰው፣ ጥቃቅኗን ነገር ከመጠራጠር ይጀምራል።" አለ የአውራጃ ሹሙ በወኔ እጆቹን እያወናጨፈ።

"ሁኔታዎች ከምንገምታቸው በላይ በፍጥነት እየተለዋወጡ ነው።" አለ የፖሊሱ አዛዡ "በሰራዊቱ ውስጥ የመደብናቸው ተባባሪ አባሎቻችን ሁሉም የመረጃ ሰዎች መሆናቸው ታውቋል። ተበልተዋል። ስለዚህም የምንጠብቀውን ውጤት ያህል ሊያስገኙልን አልቻሉም። በዕረፍትና በመዝናኛ ሰዓት የሚዘፈኑት ዘፈኖች፣ ግጥሞች፣ ሽለላውና ፉከራው ሁሉ የሚሊሽያው የመልዕክት ልውውጥ መቀባበያ ዘዴዎች መሆናቸውን ደርሰንበታል።"

"ይህንን ዘዴ መስበር አይቻልም ወይ?" ሲል የአውራጃ ሹሙ በኃይል አናፈረ።

"አይቻልም ጓድ! በመሰረቱ መስበርም የለበትም። ምክንያቱም ይህንን ዘዴ ብንሰብር ሌላ ዘዴ መፍጠራቸው ስለማይቀር ያንን እስከምንደርስበት ድረስ ነገሮች ከእጃችን ሊወጡ ይችላሉ። በዚህ ዘዴ በሚሊሽያው መካከል የመረጃ ልውውጥ እየተካሄደ መሆኑን ማወቃችን ለእኛ እጅግ ይጠቅመናል። የቅድሚያ እርምጃዎችን ለመውሰድ ያስችለናል።" አለ የፖሊስ አዛዡ በልበ-ሙሉነትና በእርግጠኝነት።

"በዚህ ረገድ የተጠናከረ ስራ መሰራት አለበት። በሚቀጥለው ስብሰባ ሪፖርት ይቅረብ።" አለ የአውራጃ ሹሙ በአጀንዳው ላይ ማስታወሻ እየፃፈ።

"እኛ ችግሮች አሉብን ጓድ!" አለ የፖሊስ አዛዡ ችግሮቹን ለመግለጽ ፊቱን ቁጥር ፊታ እያደረገ የመረጃ ስራ የአንድ ክፍል ስራ ብቻ አይደለም። ያሉን ጥቂት አባሎችና ተባባሪ አባሎች ናቸው። እነርሱም ቢሆኑ የደህንነት ሰዎች መሆናቸው በመታወቁ የሚፈለገውን ያህል ውጤታማ አይደሉም። በመረጃ ሰራተኛነት በቀላሉ የማይጠረጠሩ ተባባሪ አባሎችና ተጨማሪ በጀት ያስፈልገናል። ሰራዊቱ በመዝናኛና በዕረፍቱ ሰዓት የሚያወራቸውን ተረቶች፣ ቀልዶች፣ የሚዘፍናቸውን ዘፈኖችና ፉከራዎቹን በጥንቃቄ እየለቀመ የሚያቀርብልን፤ ሴቶቹም የሚያቀብሉትን ስንቅ በአይነ-ቁራኛ የሚጠብቅ አንድ ኮሚቴ እንዲቋቋም ሃሳብ አቀርባለሁ። በእኛ በኩል ሰዎች እንሰጣለን አለ የፖሊሱ አዛዥ። አስተያየት ተዥጎደጎደ። ተጨማሪ፣ ተቃውሞ፣ የተለየ ሃሳብ፣ አስታራቂ! የሚባለው ሁሉ ተባለ። የኮሚቴው መቋቋም አስፈላጊነቱ ታመነበት።

"ምን እንበለው ይህን ኮሚቴ?" አለ የአውራጃ ሹሙ ወደተሰብሳቢዎቹ አፍጦ።

"የቅኝት ኮሚቴ እንበለው" አለ አንዱ።

"የለም አይሆንም።"

"የማኅበራዊ ግኑኝነት ኮሚቴ ብንለውስ?" አለ ሌላው

"ይህም አይሆንም። በቀላሉ ጥርጣሬ ውስጥ ይወድቃል።"

"የመረጃ ክትትልና አጠናቃሪ ኮሚቴ ቢባልስ" አለ ደግሞ ሌላው።

"የለም እንደርሱማ አይሆንም። በመረጃ ስራ የማይጠረጠሩ አባላት እንደሚያስፈልጉት ሁሉ ስሙም እንዲሁ ከመረጃ ጋር ያልተገናኘ መሆን አለበት።"

"የቻርት ኮሚቴ ብንለውስ?" አለ የአውራጃ ሹሙ አንገቱን ሰገግ ትከሻውን ቀና አድርጎ እየተኮፈሰ። ተሰብሳቢው ሁሉ ራሱን በመነቅነቅ የአውራጃ ሹሙን ብልህነት የሚያደንቅ በሚመስል አኳኋን አዎንታውን ገለፀ።

"ጓድ አንተ የኮሚቴው ሰብሳቢ ትሆናለህ።" አለ የአውራጃ ሹሙ ወደ አንድ ልጅ እግር ወጣት እያመለከተ።

"እኔ የመረጃ ስራ ሙያዬ አይደለም። ምኑን አውቄ ነው ሰብሳቢ የምሆነው?"

"ምንድነው ሙያህ?" አለ የአውራጃ ሹሙ በንቀት ዓይን የጎንዮሽ እያየው።

"እንደሚያውቁት ሶሲዮሎጂ ነው የተማርኩት። በዚህም አውራጃ ስመደብ በሶሲዮሎጂ ኤክስፐርትነት ነው።"

"ተወው ባክህ የአንተን ኤክስፐርትነት! ለእናት አገር ደህንነት ያልሆነ ኤክስፐርትነት ዋጋ የለውም። ለማንኛውም በዚህ ኮሚቴ አንተ ታስፈልገናለህ።"

"የለም ጓድ! ያለ ሙያዬ ብገባ የምጠቅመው ነገር የለም።"

"እስከ መቼ ነው አንተ በሚሰጥህ አሳይመንት ላይ ሁሉ እምቢተኛ ሆነህ የምትዘልቀው? ወይም ለምን እንደኛሀን አትሽፍትም?" አለ ሹሙ በቁጣ ሰውዬውን በማመነጫጨቅ።

"እኔ እምቢተኛ አልሆንኩም። እርስዎም ያውቃሉ። ያለፈቃዴና ያለፍላጎቴ ከዋናው መ/ቤት የእኔ ሙያ በማያስፈልግበት በዚህ አውራጃ ውስጥ ተወረወርኩ። እሺ ብዬ ትዕዛዙን አክብሬ ብመጣ ደግሞ ያለ ፍላጎቴና ያለ ሙያዬ የአውራጃው የዘመቻ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል አደረጋችሁኝ። አሁንም ይሄው ያለሙያዬና ያለፍላጎቴ በቻርት ኮሚቴ ስም የስለላ ስራ እንድሰራ እየታዘዝኩኝ ነኝ። በሙያዬ ሰርቼ decent ኑሮ ከመኖር ሌላ ጣጣ ውስጥ መግባት አልፈልግም።" አለ ልጅ እግሩ ወጣት ብሶትና ምሬት እየተናነቀው።

"ኤድያ! ምኑን ኤክስፐርት ሆንከው!! እየነው አይደል እንዴ እየሰራህ ያለውን! ቂጥህን አሳብጠህ ወንበር ላይ ስትታሽ ውለህ ጥናት እያልክ ወረቀት ስትቀድ መዋልህ አይደል የአንተ ኤክስፐርትነት? እኛም እንዳንተው ጣጣ ውስጥ መግባት አንፈልግም። ለእናት ሀገራችን ስንል ነው የለበለቡት ግንድ መስለን ደርቀን የምንሄደው።" ሲል አፈጠጠበት።

"አይደለም ጓድ! በመጣሁ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንኳ ያካሄድኳቸው የሶሲዮሎጂካል ጥናቶች ወደፊት ለሚካሄዱት ፕሮጀክቶች በጣም ጠቃሚ ናቸው።" አለ ኤክስፐርቱ ራሱን ለመግለጽ እጆቹን እያወራጨ።

"በስንት በኩል እንደ ንፋፊት በጠላት ተወጥረን አንተ ስለሶሲዮሎጂካል ጥናት ታወራለህ?" በንቀት አፈጠጠበት።

"እነዚህ ሶሲዮሎጂካል ጥናቶች እስከዛሬ በዚህ አውራጃ ተሰርተው የማያውቁ ናቸው። ጠቀሜታቸውም አልታወቀም። የውጥረት ሁኔታ ቢኖርም ጎን ለጎን ሌሎችም ስራዎች መካሄድ አለባቸው። ያለበለዚያ ኢኮኖሚው stuck የሚያደርግበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል።" አለ ኤክስፐርቱ ወጣት በመቅርቀር ስሜት

"ተው እባክህ አታውቁም አትበለን" አለና አቋረጠው የአውራጃው ሹም "ታውቃላችሁ ተብለን ነው መንግስት በዚህ ኃላፊነት ላይ ያስቀመጠን እንዳንተ ጥቁር ካባ አድርገን ፎቶ ባንነሳም፣ ዲግሪ ባንጭንም፣ ስራውን ከአንተ ይበልጥ እናውቀዋለን። እኛ ነን እዚህ ያደረስንህ። ያኔ አንተ ተማሪ ቤት ድንጋይ ስትወረውርና ድንች ስታቦካ የእናት ሀገር ዳር ድንበር ለማስከበር ከፀረ-ሕዝብና ፀረ-አብዮት ጋር ስንፋለም ነበር። አታውቁም አትበለን።" አለ የአውራጃ ሹሙ በእልህና በቁጣ እየተንተከተከ።

"አታውቁም አላልኩም። በእኔ ሙያ ለስራችሁ የሚያግዝ፣ የሚጠቅም ጥናት እየሰራሁ ነኝ ማለቴ ነው . . . አለ ኤክስፐርቱ ለማስረዳት የሚጠቀምበትን ቋንቋ በጥንቃቄ በመምረጥ ዓይነት። አውራጃ ሹሙ እንዲናገረው ድል አልሰጠውም። "በቃህ! አንተ የሚመስልህን ተናግረሃል። ለሌሎችም የመናገር ዕድል መስጠት አለብን።

ምንድነው ሌሎቻችሁ የምትሰጡት አስተያየት?" አለ የአውራጃው ሹም ኮስተርተር ባለ የቁጣ ፊት። እዚያ ያለ ተሰብሳቢ ሁሉ ተንጣጣ። ያንን ልጅ እግር ኤክስፐርት እሩምታ አወረዱበት። በቃላት ዱላ ወገሩት።

"ጓድ ሻምበል! በእናንተ ክፍል በኩል የምታቀርቡት አስተያየት ካለ እንስማና ወደ ውሳኔ እንሄዳለን ጊዜ የለንም" አለ ሹሙ።

"በእኛ በኩል ቀዳሚው ነገር ሚሊሽያው ሰራዊት በአፋጣኝ ስልጠናውን አጠናቆ ለግዳጅ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ ነው። እስካሁንም ከስለጠናችሁ በኋላ ትጥቅ ተሰጥቶአችሁ ወደ ቀበሌያችሁ ትመለሳላችሁ በሚል ዘዴ ሰራዊቱን ልናቆየው እንደቻልን ሁላችሁም ታውቁታላችሁ። ሰራዊቱ ይህንን በእጅጉ እየተጠራጠረ መሆኑን ጠቋሚ መረጃዎች አሉን። በመጨረሻም ስልጠናው ተጠናቆ ሰራዊቱ ለግዳጅ ሲንቀሳቀስ ባዶ መሳሪያ ብቻ መታደል አለበት። በዚህ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ትጥቅ ይዛችሁ ወደቀበሌያችሁ ትመላሳላችሁ ስንል ከርመን ለግዳጅ ስናንቀሳቅሰው ሰራዊቱ በእኛ ላይ ተኩስ ሊከፍት ይችላል።"

"እና ምን ይደረግ ጓድ ሻምበል? ችግር ብቻ ሳይሆን መፍትሔውንም ጭምር አብራችሁ አቅርቡ እንጂ?" አለ ሹሙ በጭንቀት!

"ለዚህ መፍትሔው ሰራዊቱን በድንገትና በፍጥነት ለግዳጅ እንዲንቀሳቀስ ከማድረጋችን በፊት ለጥበቃ ወደ ቀበሌው የሚመለስ መሆኑን እንዲቀበለው ማድረግ ነው። በዚህ መካከል በምንም ዓይነት ሁኔታ ሰራዊቱ እጅ ጥይት እንዳይገባ መቆጣጠር ያስፈልጋል።

"በየቀኑ ሚስቶቻቸው እየተሸከሙ እያመጡ በሚያቀብሏቸው ጭብጦና ቆሎ ውስጥ ጥይት ያለመኖሩን በምን ልናውቅ እንችላለን?" አለ ሹሙ ከቅድሙ ይልቅ በጭንቀትና በጥበት። "ለዚህ ስራ አሁን በተቋቋመው የቻርት ኮሚቴ ሽፋን የተጠናከረ የመረጃ ስራ መስራት ይቻላል። ለቻርት ስራ የሚያስፈልግ በማስመሰል ምንም ዓይነት መረጃ ከእጃችን ማስገባት ቀላል ነው። ጓድ ኤክስፐርቱ በዚህ ብዙ ሊረዳን ይችላል። ከቆሎው ዘገን ከጭብጦውም ቆረስ እያደረገ ሴቶቹ ምን እያመላለሱ እንደሆነ ልናውቅ እንችላለን። ለአካባቢው አዲስ በመሆኑና ምሁር መሆኑ በሕዝቡ ስለሚታወቅ ጠቃሚ የመረጃ ስራ ለመስራት ይችላል።" "ፍላጎቱስ ባይኖረኝ . . . እንዴት ነው ነገሩ?" አለ። ኤክስፐርቱ ያደረበትን ጭንቀት ለመግለጽ የፈለገ በሚመስል አኳኋን! "ተው እንጂ ጓድ! ይሄ እኮ የሙያ ስራ ነው። እንዴት ነው ፍላጎት የማይኖርህ? ያለንበትን ወቅት መረዳት አለብህ። ዛሬ በሙያህ እንድታግዘን ነው የተጠየቅከው። ነገ መሣሪያ ይዘህ ልትዋጋ የምትገደድበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል" አለ የፖሊሱ አዛዥ በማግባባት ዓይነት። "ጥሩ ጨርሰናል!" አለ አውራጃ ሹሙ። "አንተ ጓድ! ይሄን አታቁትም የምትለንን የሶሲዮሎጂካል ጥናት ለጊዜው ታቆየዋለህ።

ለአሁን አያስፈልገንም። ከነገ ጀምሮ ጓድ ሻምበል በሚሰጥህ መመሪያ መሰረት ስራህን ታከናውናለህ። ጓድ ሻምበል በእናንተ በኩል መታወቂያና ትጥቅ ይሟላለት" ሲል አጀንዳው ላይ ማስታወሻ በማስፈር ትዕዛዝ ሰጠ። የፖሊስ አዛዡም ትዕዛዙን ቃል በቃል ፃፈው። ልጅ እግሩ ኤክስፐርት የሚናገረው የጠፋው ይመስል ግራ በመጋባት ዝም አለ። ስብሰባው አለቀ። እግረ መንገዳቸውን የሚሊሽያውን የጥበቃ ሁኔታ ለማየት ወደ ማሰልጠኛ ጣቢያው አመሩ። ሰልጣኙ የሚሊሽያ ሰራዊት ራቁን በልቶ ትርክክ ብሎ በሚነደው እሳት ዙሪያ ችምችም ብሎ ተሰብስቦ ይዘፍናል። እስክስታ ይመታል። ይጨፍራል።

ሎሚና ትርንጎ ሞልቶ በአገርህ፣
እምቧይ ታሸታለህ የድሃ ነገርህ።
የሞተውስ ሞተ እዘንልኝ ላለው፣
ቆሜ መሄዴን ነው አለሁኝ የምለው።
ገና ለሚመጣው ለነገው እንግዳ፣
እንዳትዘነጊ አለብን ፍሪዳ።
እሽከም! እሽከም! እሽከም! ወይ ጥጋብ! እሽከም! እሽከም!
ኤዲያልኝ ኤዲያልኝ ኤዲያልኝ ዘንድሮ፣
የሰው ዕቃ ፈጀሁ ልቤ ተሰውሮ።
አንቺ ልጅ አንገትሽ አንገትሽ አንገትሽ፣
የአንገት አንጥረኛ አለወይ ከቤትሽ።
ያቺ ልጅ አንገቷ ደም አለው አንገቷ
የተወለደች ዕለት ሳያጥቧት እናቷ።
እንኳን እኔ ሌባው ጨለማ ለባሹ፣
ባሏም አልጠገባት አብረው እያመሹ።
እስቲ ተነስቼ ልበል ወልቸም ወልቸም፣
አንቺ የእኔን ነገር ትተሸዋል መቼም፣ አንቺ የእኔን ነገር ትተሸዋል መቼም።
እሽከም! እሽከም! እሽከም! እሽከም! እስክስ! ወይ ጥጋብ!
እስክስ! እስክስ! እንዳማማሩ መሞት የለ! ተው በለው! እሽከም! እሽከም! እሽከም!!!

ወደማሠልጠኛ ጣቢያው እየቀረቡ ሲመጡ ውካታውና ጭፈራው በደንብ ተሰማቸው። ቆም ብለው አደመጡት። ገባቸው። የአውራጃው ሹምና የፖሊስ አዛዡ ግንባራቸውን ቋጥረው ጆሮአቸውን አቁመው ሲያዳምጡ ቆዩና ትክ ብለው ተያዩ። እንደተነጋገሩ ያህል ራሳቸውን ነቀነቁ። ተግባብተዋል። ሁለቱም ዞር ብለው ልጅ እግሩን ኤክስፐርት አዩት። ራሱን አልነቀነቀም። የሚሉት አልገባውም። ሻምበሉ ወደ ጆሮው ጠጋ ብሎ አንሾካሾከ። አሁንም ራሱን አልነቀነቀም። የተሰጠው ስራ ቀፎታል። ጭንቀት ውጦታል። (ይቀጥላል)


# ኢትዮወርድ EthioWord

▶ በተሟሉና በማይቀጠሉ (የፊደል ቍርጥራጭ ያልሆኑ) ትክክለኛ የግዕዝ ፊደሎቻችን በኢትዮኤዲት የተጻፉ ጽሑፎችን ለመጀመሪያ ጊዜ በኢንተርኔት ኢ-ሜይል (ስልክ በተጥቃና/attachments) ለመላክና ለመቀበል ችለናል ። Enjoy your Internet *Ethiopic* e-mail typed using EthioEdit or GeezEdit and EthioWin (Ethiopic for Windows). Our novel and enabling programs use the perfectly coded characters distributed on more than two typefaces. These should not be confused with those copying us using incomplete character sets or those that are made out of non-Ethiopic character parts concocted on the screen. We made such Amharic typewriter and disabling methods obsolete many years ago. If your program is not ModEth or EthioWord, it is one of these other types and may not write in even a single style of the Ethiopic characters in any program.

▶ ግእዝኤዲት/GeezEdit - ፎንት በሚቀበሉ የዊንደውስ ፕሮግራሞች ውስጥ በአንድ ፎንት በሁሉም የግዕዝ ፊደሎቻችን በተጥቃ የሚያሠራ ጠምረናል ። Use our single & complete *Geez* font specially in Windows 95 and 3.11 programs which allow font selection. ግእዝኤዲት ለወደፊት ፕሮግራሞችም ነው ።

▶ ኢትዮኤዲት/ EthioEdit - በአንድ ጊዜ በ፮ ዓይነቶች ኢትዮፎኔቲክስ Ethio-phonetics አጻጻፎቻችን እንዲጻፍና በማውስ ጭምር እንዲታረም ፈጥረናል ። For use in powerful programs and computers. Package includes overlay, EthioWin, EthioEdit and GeezEdit. The Price of ModEth (ሞዴት) is $299 while that of EthioWord/EthioWordP range from $99 to $299. ለተማሪ እንቀንሳለን ። (Ref. *Ethiopian Review*, January 1991.)



| Characters | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ | ቧ | በ | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Keys | bu | bi | ba | be | b' | bo | b\ | B | b/ | b] | b[ | b. | b; |

ኢትዮወርድ - ላንዳፍታና (Landafta) ኢትዮጵያን ሪቪው የሚጻፉበትና የሚታተሙበት !

የ ኢ ት ዮ ጵ ያ ኮ ም ፒ ዩ ተ ሮ ች ና ሶ ፍ ት ዌ ር

*Ethiopian Computers and Software*

9781 W. Fremont Pl., Littleton, CO 80123, USA

Tel.: (303) 972-2186 ● Fax: (303) 973-4342 ● (202) 785–1618 ● E-Mail: *Ethiopian@aol.com*





# ቢስቁም ባይስቁም



## እንዲህ ነበር

በቀ.ኃ.ሥ ዘመነ መንግሥት መሬቱን የጊዜው ባለስልጣኖች ቀምተው ከፍተኛ ችግር ያደረሱበት አንድ ሰው በየፍ/ቤቱ ሲንገላታ ሲፈረድበት፣ ሲንገላታ ሲፈረድበት ኖሮ ኖሮ በይግባኝ ከንጉሡ የዙፋን ችሎት ይቀርባል። ንጉሡም እንደሰበር ሰሚው፣ ጠቅላይ ፍ/ቤትና ከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኞች ግጥም አድርገው ፈረዱበት። ሰውዬው የመጨረሻውን ፍትሕ ከእሳቸው አገኛለሁ የሚል እምነት ነበረውና እጅግ በጣም ተበሳጨ። አልሆነለትም። የሀልም እንጀራ ሆኖ ቀረበት። ስለዚህ እንደእብድ አደረገውና "ይግባኝ ይግባኝ" እያለ እዚያው ችሎቱ ፊት ቆሞ ይጮሃል። ንጉሠ ነገሥቱም ተገረሙና "ከእኛ ወዲያ ለማነው ይግባኝ የምትለው?" ይሉታል። ሰውዬውም "ለእግዚአብሔር ነዋ! ለእግዚብሔር!" ይላቸዋል!! ንጉሡም የበለጠ በመገረም "እኛንስ ያነገሰን ማነው?" ይሉታል። ሰውዬውም ምን ይቀርብኛል በሚል ድፍረት "የፍትሕ አምላክ ቀብቶ ቢያነግስዎትማ ፍርድዎ ይህን አይመስልም ነበር" አላቸው ይባላል።

* * *

በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት አንድ ወታደር ወደ አንድ የገጠር መንደር ጎራ ይልና የአንዲት አሮጊት የነበረች ዶሮ አርዶ ይባላል። በዶሮአቸው መበላት የተበሳጨት አሮጊት ዶሮዋ የቀፈቀፈቻቸውን ጫጩቶች በእንቅብ ይዘው አፄ ቴዎድሮስ ፊት ቀርበው "አቤት" ይላሉ። ንጉሡም ትንንሽ ጫጩቶች በእንቅብ ሞልታ ከፊታቸው የቆመችዋን ባልቴት ተመልከተው "ምን ሆነሻል ይሏታል?" ሴትዮዋም "ወታደርዎ እናታቸውን አርዶ በላብኝ። እነዚህን ጫጩቶች እንዴት አድርጌ ላሳድጋቸው ይረከቡኝ ጃንሆይ!" ይላሉ። አፄ ቴዎድሮስ በነገሩ ተበሳጭተው ያን ወታደር ያስጠሩታል። እምነት ክህደቱን ይጠይቁትና ያምናል። "በል እንግዲህ እንደጀመርከ እነዚህንም ብላቸው" ይሉታል። የንጉሡ ብስጭት ለነፍሱ ያስፈራው ወታደርም እነዚያን ጫጩቶች ከአሮጊቷ ተቀብሎ ንጉሡ ፊት ቆሞ ቅርጥፍ አድርጎ በላቸው ይባላል።

* * *

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ የማትለያቸው ከፊት ለፊታቸው እምትሄድ ድንክዬ ውሻ ነበረቻቸው። ውሻይቱ በንጉሡ ላይ ክፉ የሚያስብን ሰው እያነፈነፈች በሽታ ታውቃለች ስለሚባል ወደ ንጉሡ ፊት የሚቀርቡ ባለሥልጣኖች ሁሉ ውሻዋ ወደ እነርሱ ስትቀርብ እጆቻቸውን አጣምረው በትህትና አንገታቸውን አቀርቅረው ከአሁን አሁን ትጮህብኝ ይሆን? እያሉ ይጠብቋታል አሉ። ታዲያ አንድ ቀን በቀልደኛነታቸው የሚታወቁትን ሚኒስትር አቶ ይልማ ደሬሳን ከባለሥልጣኑ መካከል ለይታ ትጮህባቸዋለች። እርሳቸውም በውሻዋ ሁኔታ ተገርመው "እባክሽ አንቺ ውሻ ሰው ያላሰበውን አታሳስቢ" አሉዋት ይባላል።

* * *

በደርግ ዘመነ መንግሥት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት በባሕርዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ካድሬና ሠራተኞች ግንባር ፈጥረው ሥራአስኪያጁንና ሌሎች የፋብሪካውን ኃላፊዎች ለማባረር ግርግር ይፈጥራሉ። የክፍለሀገሩ የደርግ አባል ሠራተኞቹን ስብሰባ ይጠራና ሁኔታውን ለማብረድ ይሞክራል። በዚህም ጊዜ የደርግ አባሉ ምሁራንን አዋቂዎችንና ሙያተኞችን ለማጥፋት የሚደረገው ዘመቻ መቆም እንዳለበት፣ አገር በመሃይማን ልትመራ እንደማትችል ንግግር ያደርጋል። ሲናገር ቆይቶ ጣቱን ወደ አንድ ወዛደር ጠቆመና "ለምሳሌ አንተ ስንተኛ ክፍል ደርሰሃል?" ብሎ ይጠይቀዋል። ወዛደሩም "አምስተኛ ክፍል ነኝ" ብሎ ይመልሳል። የደርግ አባሉም "የ5ኛ ክፍል ትምህርት ይዘህ ሥራ አስኪያጅ ልትሆን አትችልም። እርምህን አውጣ" ይለዋል ወዝአደሩን። አንድ ሌላ ወዛደር እጁን አወጣና "ደርግ ዓለም እኛስ መሐይሞች ነን አምስተኛና ስድስተኛ ክፍል ለመሆን እናንተ ደርጎቹ ስንተኛ ክፍል ናችሁ?" ብሎ የምፀት መልስ ሰጠው ይባላል።

* * *

## የአለፈው ሰንጠረዥ መልስ


የአለፈውን ሰንጠረዥ በትክክል መልሰው የላከችልን ሥርጉት ረታ ከL.A. ብቻ ናት። ጎበዝ!



## ያለፈው ሰንጠረዥ መልስ

# ሰንጠረዥና ጨዋታ

የአሁኑ ሰንጠረዥ ጥያቄውም መልሱም በአማርኛ ነው። የላኩልን ሰይፉ መኩሪያ ከአትላንታ ናቸው።



### ወደ ጎን

1. "ምንጊዜም ፊልፐስ" ብሎ ያለው
9. ተመገብ
10. አራት ስሙኒ
11. እንሂድ (በጣልያንኛ)
13. የዛፍ ዓይነት
14. የቤተክርስቲያን ዜማ ደራሲ
16. ማገዶ እንጨት
17. አዋቂ
19. አጋምና ____
20. በእግዜር አምሳል የተፈጠረ
21. ካቲካላ
22. የወንድ ስም
23. ____ ማማ
26. ተናገር
27. ከሰንበት በፊት
28. የሚሞክር
29. ____ ና ቀንበር
31. ተጠያቂ
32. እምቢ አልልም
33. ዋጋው ተወደደ
34. በጣም ነጭ ጤፍ
35. የታወቀ የኢትዮጵያ በረኛ
37. ዝርዝር
39. ሥራ
40. እባጭ
42. ለሀጭ
43. ምጥ

### ወደ ታች

2. የአይን ጥቁሩ
3. አቧራ
4. ____ ሶዶ (የድሮ መጠሪያ)
5. ሞልቃቃ
6. የጳውሎስ ኞኞ አምድ
7. ለዛ
8. የኢየሱስ ክርስቶስ እናት
11. ከኢትዮጵያ ቅኝቶች አንዱ
12. ጄኔሬተር
15. ደደብ
18. የድሮውን መቀየር
19. ተሳካለት
22. የተከለከለ ሰዓት
24. የሚያመናቅር
25. ስም አጥፊ
28. ትምህርት ቤት
29. የጥላሁን ገሠሠ የቆንጆ ምሳሌ ዘፈን
30. ጠቅል
35. ተናዳፊ
36. መኖሪያ
38. ትላ____
41. የሽንት ከረጢት

### ይህንንም ይሞክሩ

ከዚህ በታች ያሉትን የእንግሊዝኛ ቃላት (A) ከአማርኛ ትርጉማቸው (B) ጋር ያዛምዱ።

**A**

1.cycle
2.distortion
3.menopause
4. copulation
5. Fertilization
6. axis
7. tactic

**B**

ሀ. ሩካቤ
ለ. ምህዋር
ሐ. ዑደት
መ. ስልት
ሠ. ዝንፈት
ረ. እርጠት
ሰ. ጽንሰት

መልሶቻችሁን ላኩልን።

# የላንዳፍታ መጽሔት ደምበኛ ይሁኑ

ለ6 ተከታታይ እትሞች

| | | |
|---|---|---|
| U.S. | $16.00 | (including postage & handling) |
| Canada | $22.00 | (including postage & handling) |
| Europe & Asia | $30.00 | (including postage & handling) |

የሚላክሎት በመጀመሪያ ደረጃ ፓስታ አገልግሎት ነው።
በአካባቢዎ ገበያ ላይ ከመዋሉ በፊት ይደርስዎታል።

## የላንዳፍታ መጽሔት የደምበኝነት ቅጽ LANDAFTA SUBSCRIPTION FORM

NAME ______________________________

ADDRESS ______________________________

CITY ________________ STATE ________ ZIP ____________

PHONE ( ______ ) ________________

<u>ያለፉትን እትሞች</u> ማዘዝ ከፈለጉ ይህንኑ ይጥቀሱ
ክፍያው ከነመላኪያው ለእያንዳንዱ እትም $ 2.50 ነው።

ለጓደኛዎ በሽልማት መልክ ለመላክ ከፈለጉ ከዚህ በታች ያለውን ይሙሉ።
Please, send my gift subscription to the following person.
NAME ______________________________

ADDRESS ______________________________

CITY ________________ STATE ________ ZIP ____________

PHONE ( ______ ) ________________
አባክዎን ክፍያዎን በመኒ ኦርደር ወይም በቸክ በአድራሻችን ይላኩ።
*Please, send money order or check payable to LANDAFTA.*

LANDAFTA
P.O.BOX 49301
ATLANTA, GA 30359

# አባይ ምግብ ቤት

## Abbay Restaurant



| | |
|---|---|
| ከእሁድ እስከ ሐሙስ | ከ 11:30 a.m. እስከ 11:00 p.m. |
| ዓርብና ቅዳሜ | ከ11:00 a.m. እስከ 12:00 midnight (ራት) |
| | የመዝናኛ ፕሮግራም እስከ 2:00 a.m. |



የተለያዩ ባህላዊ ምግቦቻችንን ይወዳሉ።
ብቅ ይበሉና እናስተናግድዎት።

በዕረፍት ቀናት ምሽት
የመዝናኛ ፕሮግራሞች ይኖሩናል።
ደስ ሲላችሁ እኛንም ደስ ይለናል፤
ስለዚህም በመስተንግዶአችን እናስደስትዎታልን።

## AUTHENTIC ETHIOPIAN RESTAURANT



Have a spicy authentic Ethiopian dinner
and stay for the cultural entertainment on weekends.



3375 # 1050 Buford Highway
Atlanta, GA
(404)321-5808

# MRA'G TRAVEL

## ሚራኘ የጉዞ ወኪል

*International - Business - Leisure - Cruise*


ለአለም አቀፍና
ለአገር ወሰጥ ጉዞዎ አለንልዎ!

Excellent Service!
Special Fare!
Group Fare!

ገነት ፈቀደ
ፕሬዚዳንት
Genet Fekede
*President*

አስተማማኝ ጉዞ ወደ

አዲስ አበባ
አስመራ
ጆሀንስ በርግ
ቴላቪቭ
ኢየሩሳሌም
ፍራንክፈርት
ለንደን


92 Piedmont Ave N.E
Atlanta, GA. 30303
(404)577-4404 Fax (404)222-9305





# ካሊፎርኒያ ማርት በአትላንታ

## CALIFORNIA MART IN ATLANTA

2080 CHESHIRE BRIDGE ROAD
ATLANTA, GA 30324
(404)320-6747 - (404)320-9082

**ቁርስ** ፉል፤ ግንፍልፍል፤ ያበሻ ዳቦ፤ እምባሻ

**ምሣና እራት** ክትፎ፤ ጥብስ፤ ጎረድ ጎረድ፤ የጥብስ ፍርፍር፤ የበግ አልጫ ፍትፍት

በተጨማሪ እንጀራና ሥጋ እንሸጣለን።

ORDER FOOD
TO GO!!

### የተለያዩ የምግብ ሸቀጦች መደብር

ESPRESSO
CAPPUCCINO

በርበሬ
ሚጥሚጣ
ሽሮ
ቅንጨ
ምስር
ጤፍ
ቡና

እጣን
የተነጠረ ቅቤ
አዋዜ
ጌሾ
የወጥ መከለሻ
ቡላ ዱቄት
ልዩ ልዩ ቅመማ ቅመሞች

ይደውሉልን ወይም ይጎብኙን!!

Mail Order Available
Please, call for Arrangements